# 7

የንጉሡ ክፍል ምንም ዓይነት የተለየ ነገር የለበትም። ምናልባትም፣ ሉዊስ 14ኛ ሲለውጡት የፈለጉትም ለዚሁ ይሆናል። ክፍሉ የእንግዳ ማረፊያ እንዳይሆን በጣም ትንሽ ነው። በተለይም ሦስት ታላላቅ የመግቢያ በሮች ያሉት ስለሆነ የግል ፅህፈት ቤት እንዳይሆንም እጅግ ከሚሰፋው ከጋለሪ ዴስ ግላሴስ ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ነው። ሽጋ ነው የሚለው አባባልም ክፍሉ ለጉራ ያመቻል ለማለት ነው። ይህ ሁሉ ሆኖ የሚጋንን ግርማ የለውም። ንጉሡ ትንሽ ራቅ ብለው ተቀምጠዋል። በተመስጦ ከሚያስቡት ጉዳይ አንፃር ሲታዩ፣ በደስታ የተሞሉ ወይም እንደ ስመጥር ገናና ሰው በዚያች ትንሽ ቦታ ሊሆን እንደሚችለው፣ እጅግ ጠንካራውና ሃያሉ፣ በርግጥም እዚያ መኖርም በዙሪያቸው ያለው ሁሉ በጉጉት እንዲደመጥ የሚያደርግ አይነት አይደለም። ንጉሡ እዚያ የተገኙት እንደ ሃብታም፣ በአንድ አነስተኛ የለምኝ ሰብሰብ ውስጥ ሲኖር ከሚታየው መደነቅ በማይልቅ መልኩ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እርግጥው፣ ባለሦስት ጠርዝ የሆነውና ነጫጭ ላባዎች ባሉት ባርኔጣቸው በቀላሉ ይለያሉ። ሌሎች ሰው ስራሽ ፀጉራቸውን አጥልቀዋል።

ንጉሡ የተቀመጡበት ወንበር የመኖሪያ ቤት መቀመጫ መልክ ያለው ባለመደገፊያ ሲሆን፣ ዋር ዳሩ ግን በሚያብረቀርቅ የጌጥ ምስማር የተከፈፈ፣ ጥቁር ቆዳ ሆኖ ባሦስት ተሽከርካሪ እግር ላይ ጉብ ያለ ነበር። በመቀመጫው ኋላ ያሉት ሁለቱ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች፣ ለንጉሡ ነፋስ ለማራገብ ለቆሙት ጥንድ የስዊዝ ዘቦች አመች ሲሆኑ በፊት ለፊት ያለው አንዱ ተሽከርካሪ፣ ንጉሡ ራሳቸው ወደፈለጉት አቅጣጫ ሊያንቀሳቅሱት እንዲችሉ ተደርጐ እጀታ ተበጅቶለት በብረት ንጣፍ ላይ የተያያዘ ነው። ከዚህ እንዲያግዛቸው ተብሎ በተዘጋጀላቸው መሣሪያ የበለጠ የንጉሡን አካለ ደካማነት፣ የሚያሣጣው፣ ሌላ ነገር የለም። አንድ እንደጣሆት የሚታሰብ ሰው በሃይሉ ብቻ ልዕለ ሰው ተደርጐ እየታሰበ ሣለ፣ ... እንግዳና ውስብስብ የሆነ ባለሦስት ተሽከርካሪ እግር ላይ ሆኖ ደካማነቱ ሲታይ ...ያውት ያ የዛሰት እምነት በንኖ ይጠፋል።

ንጉሡ ቅዝቃዝ፣ ፃንችክ ያሉና በድን ባለግርማ መስለው ቀርበዋል። የአኳኋናቸው ቀለል ማለት የተዛሣሥ፣ ያልተደሰቱና ስሜታቸው የተጐዳ መሆኑን ይናገራል። ለጆን ባፕቲስት እንዲህ ባለ በንህናት ስብሰባ ውስጥ መግባት የመጀመሪያው አጋራሞቱ ነበር።



ንጉሡ፣ በተለይም ካይሮ፣ የቆንስላውን ጽህፈት ቤት በማድመቅ የሚገኘውን የቀለም ቅብ ስዕላቸውን ግልፅ ባልሆነ መልክ ይመስላሉ። ጆን ባፕቲስት አሁን ከፊት ለፊቱ የሚያየውንና ያንን ስዕል አነፃፀረ። በርሱ ግንዛቤም፣ ሠዓሊው፣ የንጉሡን አምሣያ ስዕል ሣይሆን፣ መንፈስንና ልብን ሊማርክ የሚችል የገዛዱን ዓለም ነፀብራቅ ነበር የሣለው። ምክንያቱም፣ በስዕሉ ላይ ፈንጣጣ የወጋጋው፣ የቀላው አፍንጫቸውና በአንገታቸው ላይ ያለው የተንጠሰጠሰ ቋት የመሰለ ትርፍ ነገር ተዘልሏል። በአጭሩ፣ ስዕሉን እንዲታደስ ያደረገው ሙሴ ዴ ማይሌ ስህተት ሠርቷል። ምክንያቱም ተፈጥሮ ራስዋ፣ ከሰዓሊው ይልቅ የተሻለ አድርጋ ባስቀመጠችው አካል ላይ አስጠሊታ የቀለም ጠብታዎች እንዲያርፍበት ተደርጓል። በንጉሡ ዙሪያ ከተሰበሰቡት መካከል፣ ፍሌዛውት በጠርዝ በኩል መቆሙን ጆን ባፕቲስት አስተዋለ። ሌላ ረዥም ሰው ከጐኑ፣ ነገር ግን ለንጉሡ ቀረብ ብሎ ቆሟል። ምናልባትም ቻንስለር ፖንቻርትሬይን ሣይሆን አይቀርም። በዚያ ቦታ ተገኝተው የነበሩት፣ ከዝቅተኛው ወንበር ጐታች ስዊሣዊ ድረስ የነበሩት ሁሉ፣ ንጉሱን በመከረጅ የባለስልጣንነት ስሜትን ተላብሰዋል። ሁለቱ አኳኋኖች በጣም ስለሚመሣሰሉ፣ ሌላው ቀርቶ በፍትህ መዛበት የተቆጡ፣በሃፍረተ ቢስ የአዲሶቹ መጪዎች ጣልቃ ገብነት የተናደዱ ይመስላሉ።

ጂስዊቶቹ በተለየ የትህትና መልክ ጐንበስ አሉ። እንዲህ ያደረጉት የሰው ልጆች ሙሉ በሙሉ መሸነፍንና መስገድ የሚገባቸው ተጠቃሚ ለሚያደርጋቸው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው ከሚል እሳቤ ነው። ጆን ባፕቲስት፣ የሰላምታ አቅርቦቱ በቅፅበት የሚከናወንና የሚያልፍ መሆኑን በማስታወስ ወለሉ ላይ እስኪነጠፍ ድረስ ዝቅ አለ። ይህ አይነቱ የሰላምታ አቀራረብ የጊዜው ፋሽን ባይሆንም ከልብ የመነጨ ስለነበረ፣ በንጉሡ ነገስቱ ፊት እንዲያ በመጉበጡ የማያፍርበትና የማይፀፀትበት መሆኑን የሚያሣይለት ነበረ።

ሥነስርዐቱ ካበቃ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ያህል አጠቃላይ የማመንታት ሁኔታ ነበር። ጆን ባፕቲስትም በበኩሉ በክፍሉ ውስጥ በጉልህ የሚታይ ጡጥረት እንዳለ አስተዋለ። ይህ ውጥረት ካህናቱንና ፖንሴን፣ በንጉሡ ዙሪያ ካለው ቡድን በጥቂት ጫማዎች ርቀት በሚለየው ቦታ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ይስተዋላል። ወዲያውኑ ህምህምታው በክፍሉ ውስጥ ያለውን አየር ልክ በአንድ የበጋ ቀትር ላይ በነጐድጓድ ውስጥ ሊፈጠር እንደሚከማች የመብረቅ ሃይል ሊሰማ በሚችል መጠን ሞላው።

«ጃንሆይ» በማለት ወደ ሚያስፈራው ስብስብ፣ አባ ቾይዝ ብቻቸውን በድፍረት ተራመዱ። «ወደ ምሥራቅ ሳለን ተልዕኮ ሃላፊ የሆኑትን አባ ፍሌኡሪአን ታውቋቸዋላችሁ።

በዛሬው ዕለት እጅግ በመታመማቸው ምክንያት በመካከላችሁ ሊገኙ ባለመቻላቸው አዝነዋል። ይሁን እንጂ የቱርካውያን አገዛዝ ውስጥ ከሚገኙት አገሮች መካከል በተለይም በግብፅ፣ እኛን በመወከል ከባድ ሃላፊነት ተሸክመው ያሉትን አባ ፕላንቴይንን ሳቀርባቸው ታላቅ ክብር ይሰማኛል»

አባ ፕላንቴይንም ሰፊውን ግንባራቸውን እንደገና አንድ ጊዜ ዝቅ አደረጉና እጃቸውን ልባቸው ላይ አሣረፉ።

«እናም ግርማዊነትዎ በአርቆ አሣቢነትዎ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚደረገው ተልዕኮ እንዲንቀሣቀስ ያዘዙትና የረዱትም ከዚህ አገር የተንቀሳቀሰ ነበር» ሲሉ የንጉሡ የንስሃ አባት ቀጠሉ። «በዚህች ያልታደለች የክርስቲያን አገር ውስጥም ጥሩ መሠረት ለመያዝ ድጋሜ ሙከራ ተደርጓል። እንዳለመታደል ሆኖ በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ፣በተሣሣተ አስተሣሰብ፣መናፍቃን በሚል ሰበብ ብዙ ወንድሞቻችን ተጨፍጭፈውበት ነበር። ልዑላን ሆይ፣ሕዝቦች ከስህተትና ከማይምነት ካልተላቀቁ በስተቀር ለዘለዓለሙ ተፈርዶባቸው፣ ተኮንነው፣ እንደሚቀሩ በማወቅ የኛ የሃይማኖት ሥርዓት ያከናወናቸውን እጅግ ከባድ ጥረቶች ታውቃላችሁ። መልካም ፈቃዳችሁ ቢሆን ስትመኙት የነበረውን ተልዕኮ በተመለከተ አባ ፕላንቴይን ጥቂት መግለጫ ይሰጣሉ»

ንጉሡ፣ የአረንጓዴውን ጃኬታቸውን እጅጌ ሰብሰብ አድርገው በመዳፋቸው መሃል በትንሹ አሣሉ። ምንም እንኳ እንቅስቃሴው በጣም ፈጣንና አይን የማይገባ ቢሆንም፣ ንጉሡ የአፋቸውን የቀኝ ዳርቻ በእጅጌአቸው ጨርቅ ጠርዝ ሲጠርጉት ተመለከተ። ከንፈራቸውም በዚያ አቅጣጫ ጣል በማለቱ አፋቸው ሙሉ በሙሉ አልተከደነም።

«አባ፣ ይናገሩ። በዚህ ጉዳይ ላይ ትልቅ ፍላጐት አለን።» አሉ ንጉሡ

«ጃንሆይ» አሉ አባ ፕላንቴይን ግንባራቸው እየቀላ። «ይህን ጀግንነት የሚጠይቅ የሃይማኖታችንን ተስፋ ወደዚያ እሩቅ አገር ለማድረስ የወጡት በአሁኑ ሰዓት በዚህ ዓለም የሌሉ መሆናቸውን በሐዘን መግለፅ ይገባኛል። በዚያ ፈታኝ ጉዟቸው ላይ እግዚአብሔር ወደራሱ ጠራቸው። መስዋዕትነታቸው ግን እንደመታደል ሆኖ በከንቱ አልቀረም። የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት ቀሪዎቹን መልዕክተኞች በታላቅ አክብሮት ተቀብለዋቸዋል። ንጉሡ ነገስቱ ለካቶሊክ እምነት በሚገባ ዝንባሌ እንደነበራቸው ገልፀው፣ አሁን ግን ሊቀላቀሉ እንደማይፈልጉ አጥብቀው ተናግረዋል። ከዚህም በላይ በግርማዊነትዎ መማረካቸውንና በዓለም



ላይ ሃያሉ የክርስቲያን መሪ መሆንዎን ተቀብለዋል። አክብሮታቸውን ለመግለፅም እስከ ካይሮ ድረስ አንድ የመልዕክተኛ ቡድንና በራሱ ሕዝብ መካከል ደረጃው ባይታወቅም አምባሣደር ሊባል የሚችል ሰው ልከው ነበር»

«እንግዲያውስ ሰውዬው አሁን እዚህ ለምን የለም» አሉ ሉዊስ 14ኛ

«ጃንሆይ፣ እኛም ልናመጣቸው ከልባችን ፈልገን ነበር። ነገር ግን ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው፣ አውሮፖዊ ተወላጅ ያልሆነ ሰው፣ ወደ አውሮፖ እንዳይጓጓዝ ቱርኮች ብዙ እንቅፋቶችን ይፈጥራሉ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አምባሣደሩ የመጡት ብቻቸውን አልነበረም። አጅበው የመጣውና አሁን እፊትዎ የሚያዩት ሙሴ ፖንሴ ነበር»

አባ ፕላንቴይን ወደ ጆን ባፕቲስት ዞር አሉ። በክፍሉ ውስጥ ቀደም ሲል ሰፍኖ የነበረው ውጥረት እንደገና አገረሸበት። የዚህ ሁሉ ማዕከላዊ አትኩረት እርሱ እንደሆነ ጆን ባፕቲስት ተገነዘበ።

«ሙሴ ፖንሴ፣ በምስራቅ ሜዲቴራኒያን ጣቢያዎች የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ይሠራል። በአሁኑ ጊዜ መኖሪያው ካይሮ ውስጥ ነው። ለግርማዊነትዎ ቀደም ሲል የገለፅኳቸው ነፍሣቸውን ይማረውና አባ ዴ ብሬቬደንት፣ ወደ አቢሲኒያ ጉዟቸውን ያደረጉት ከርሱ ጋር ነበር። ያን ጊዜ ንጉሠ ነገስቱ ታምመው ስለነበር አውሮፖዊ የመድሃኒት አዋቂ እንዲያያቸው ጠይቀው ነበር። በዚህም መሠረት በሙሴ ፖንሴ አማካይነት አቢሲኒያውያን፣ ንጉሥ እያሉ ወደሚጠሯቸው መሪያቸው ዘንድ የመድረስ ዕድል አገኙ። ከዚያም፣ ከዚሁ ከሙሴ ፖንሴ ጋር የአቢሲኒያውያን መልዕክተኞች የመልስ ጉዞ አደረጉ»

ይህን ተናግረው አባ ፕላንቴይን ወደ ኋላ ተራመዱና ጆን ባፕቲስትን ተመለከቱ። ሉዊስ 14ኛም በተራቸው ዐይኖቻቸውን ወደ ሐኪሙ ወረወሩ። የንጉሡ ከፍተኛ ባለስልጣን አጃቢዎችም እንደመሪያቸው አደረጉ። ጊዜው ደረሰ።

ጆን ባፕቲስት፣ ለአመል ያህል ወደፊት ተራምዶ ከወገቡ ጐንበስ ካለ በኋላ ቀጠለ።

«ጃንሆይ፣ የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት ለግርማዊነትዎ እንዲያደርሱት የላኩትን መልዕክት፣ አምባሣደሩ እዚህ ሊገኙ ባለመቻላቸው እኒያ ከፍተኛ ገዥ፣ በዚህ ቤተመንግስት እንዲሰማላቸው የፈለጉትን መልዕክት የማቅረብ ሃላፊነት በኔ ላይ ወድቋል። በዚህም ላይ ማከል የምፈልገው፣ ንጉሠ ነገስቱ፣ ግርማዊነትዎ መልስ እንደሚልኩላቸውም ትልቅ ተስፋ

እንዳላቸው ነው:: እኔም ሕይወቴን እንደገና አደጋ ላይ የሚጥል እንኳ ቢሆን፣ የግርማዊነትዎን መልስ ይዤ ለመሄድ ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ ከፊትዎ እገኛለሁ::

«የተሰጠህ መልዕክት ምን ነበር?» ሲሉ ንጉሡ ጠየቁ

«ጃንሆይ:: የተሰጠኝን መልዕክት እናገራለሁ:: ነገር ግን ግርማዊ ንጉሠ ነገስት መልካም ፈቃድዎ ከሆነ የአቢሲኒያው ንጉስ ባዶ እጄን እንዳልሰደዱኝ ለመናገር እፈልጋለሁ:: የንጉሡ ግዛት እጅግ ሃብታም ነው:: ምድራቸው ማዕድናትና እንቁ የሞላበት ነው:: እንስሣት የሞሉበት ደናቸው ሊታመን ከሚችለው በላይ እጅግ ለም ነው:: ንጉሡ፣ ወዳጅነታቸውን ሊገልፁላቸው የሚችል ከሆነ በማለት ለፈረንሣይ ንጉሥ የላኩላቸውን ስጦታ . . . »

በዚያ ቦታ በነበሩ ሰዎች መካከል ጉርምርምታ ተፈጠረ:: የንጉሡ ዓይን ግን ትክ እንዳሉ ነበሩ::

« . . . ያላቸውንም አድናቆት እንድገልፅ ጠይቀውኛል» ካለ በኋላ ጆን ባፕቲስት በጣም ፈጠን ብሎ «የዚህን ሃብት እጅግ ውብ ናሙናዎችንም እንዲቀበሉ ልከውኛል»

«መልካም» አሉ ሉዊስ 14ኛ «ገፀ በረከቶቹ የታሉ?»

ዓይኖቹ በአስተናጋጆቹ እግሮች ስር በነበረው ሣጥን ላይ አረፈ::

«ጃንሆይ፣ ንጉሠ ነገስቱ አምስት በቅሎዎች ላይ የተጫነ የወርቅ ዱቄት ሰጥተውን ነበር:: ከዚያም በሌሎች አራት በቅሎዎች ላይ የተጫነ ዝባድና እጣንም ጨምረው ነበር:: ከዚያም በላይ ዛጐሎችና በአለም ላይ በሌላ ቦታ የማይገኝ አሥር ከረጢት ሙሉ ድንቅ ጣዕም ያለውን ቡና ልከው ነበር:: ይህ የመጀመሪያው ጭነት ነው:: ይህን ተከትሎ ሙሉ በሙሉ ያልተዳቀሉ፣ ግርማዊነትዎን በእጅጉ ሊያስደስቱ የሚችሉ ቁመናቸው የሚያምር ድንኩላዎች ነበሩ:: እነዚህ ፈረሶች በማንኛውም አይነት መልክአ ምድር ላይ እንደልባቸው መጓዝ የሚችሉ ነበሩ:: ንጉሠ ነገስቱ፣ እነዚህ ፈረሶች በውብ ኮርቻዎች እንዲጫኑና እንዲለጐሙ ይፈልጉ ነበር:: ከእነዚህ ፈረሶች ጐን፣ ከንጉሡ ዘቦች መካከል እጅግ ጠንካሮችና በዚያ ከፍተኛ አምባ ምድር ላይ ማንኛውንም ዓይነት ነገር መቋቋም ይችላሉ የተባሉ ስምንት ምርጥ አቢሲኒያውያን ወታደሮች ይራመዱ»



ጀስዊቶቹ ቀስ በቀስና ሳይታወቃቸው ጆን ባፕቲስት እየተናገር ሣለ እርሱን ሳለማየት ወደኋላቸው አፈገፈጉ:: ቀጥ ብሎ ቆሞ አንዳንድ ጊዜ የሁሉም የበላይ የሆኑትን ንጉሠ ነገስት፣ አንዳንዴም በዙሪያቸው የሚገኙትን አዳማጮች ላይ ዐይኖቹ ያርፋሉ:: በልበ ሙሉነት ድምፅ ስለሚናገር ለአፍታ ያህል በክፍሉ ውስጥ የነበረው ሹክሹክታ ረጭ አለ:: ወርቅ የተጫኑት በቅሎዎች፣ አሽብርቀው የተዘጋጁት ፈረሶችና የወጣት አቢሲኒያውያን ወታደሮች ሰልፍ ክፍሉን ከአንድ ዳርቻ ጀምሮ እየተጓዘ በመሙላት ወደ ሌላው ዳርቻ ዘልቆ ወደ ጋለሪ ዴስ ግላሴስ በመግባት ከአይናቸው የተሰወረባቸው መሰላቸው::

«ከበስተኋላችን» በማለት ጆን ባፕቲስት ቀጠለ::

«ሰልፋን በማጀብ የጀርባ ጠባቂዎቻችን በመሆን የታሰሩበት ሰንሰለት የብር ቃጭል ታስሮለት ሲከተሉን የነበሩት ዝሆኖች ተብለው የሚታወቁት ግዙፋን እንስሳት ነበሩ:: የነዚህ ዝሆኖች ጥርሶች የአንድ ሙሉ ሰውን ሃውልት ማሠራት የሚያስችል ርዝማኔም ነበራቸው::»

ፖንቻርትሬይን ወደ ንጉሠ ነገስቱ ጆሮ ዝቅ ብሎ የሆነ ቃል ሹክ አላቸው:: ይህ አነስተኛ እንቅስቃሴ በዚያ ክፍል ውስጥ የነበረውን የተመሰጠ ማዳመጥ አወከውና ንግግሩ ተቋረጠ::

«በእጭሩ» ሲሉ ንጉሡ አቋረጡና «የተናገርከው ሁሉ በዚህ ሣጥን ውስጥ ነው እንዴ?»

ምፀታዊ ጉርምርምታ ከአጃቢዎቹ አካባቢ ተቀሰቀሰ:: በፊቶቻቸውም ላይ ሰይጣናዊ ፈገግታ ብቅ አለ::

«በጥቂቱ፣ ጃንሆይ፣ በተወሰነ መልኩ አዎን»

እያደገ የነበረው ጉርምርምታ ፈነዳ:: ውሃ በእሣት ላይ ሲፈስስ የሚፈጠረውን የጭስስታ ድምፅ አይነት ሣቅ ተከተለ::

«አዎን» ሲል ጆን ባፕቲስት ትልቆቹንና ቀን ዓይኖቹን ወደ ሉዊስ 14ኛ በማቅናት ደገመው:: «ጉዞው የያዝናቸውን ብዙ ድንቅ ነገሮች ወስዶብናል:: የአየር ጠባዩ ድንኩላዎቹን ገደላቸው:: አብረውን የመጡትን አቢሲኒያውያን ቁርኮች ወረሷቸው:: ወርቁ፣ዛጐሎቹና እጣኑ ተሰረቁብን»

ወደ ሣጥኑ አንድ ርምጃ ተጠጋ

«ጃንሆይ፣ ይህን ለመቀበል ያጠራጥር ይሆናል። ነገር ግን የአቢሲኒያው የበላይ ገዥ እርስዎን ለማክበር የፈለጉበት ይህ እፁብ ድንቅ ነገርና የኔን ትረካ የሚያረጋግጠው ይህን ነው»

አስቀድሞ አጃቢዎቹን የብረት መፈልቀቂያ አስይዟቸው ነበረ። ጆን ባፕቲስት፣ በፊቱ ምልክት በመስጠት ሣጥኑን እንዲከፍቱት አዘዛቸው። ንጉሡ፣ ስዊሣውያን ዘቦቹ ወደፊት ጥቂት ርምጃዎች ወንበራቸውን እንዲያሽከረክሩላቸው ምልክት ሰጡ። የማንቀሣቀሻ ዘንጋቸውን በመጠቀም በግራ በኩል ሊታይ የሚችለውን ለማየት፣ራሣቸውን በስያፍ አስቀመጡ። ሁለቱ አጃቢዎች ሣጥኑን ለመክፈት በሚጥሩበት ጊዜ በክፍሉ ውስጥ የሚጠበቀው ፀጥታ ሰፈነ። በዚያን ሰዐት ይሰሙ የነበሩት ድምፆች በምድጃው ላይ ይንተገተግ የነበረው የግንዲላ እሣት ነበልባልና ሣጥኑ ሲፈለቀቅ በሚስማሮች ላይ የሚሰማው መንሣጠጥ ብቻ ነበር። በመጨረሻም የሣጥኑ ክዳን ተከፈተ። ጆን ባፕቲስት፣ አጃቢዎቹ ወደ ኋላ እንዲሉ ካመለከታቸው በኋላ የሣጥኑን ክዳን በአንድ በኩል አስቀመጠው። ይታይ የነበረው አንድ ቀለሙ ቡኒ የሆነ የረጠበ የናይለን ጨርቅ፣ የሆነ የተወጠረ ነገር ሸፍኖ ነው። ጆን ባፕቲስት ጨርቁን አንስቶ ሲጥለው የቀረው ሁሉ ቁልጭ አለ።

ለአፍታ ያህል ቆም አለና በመቀጠልም በሁለት እጆቹ የሣጥኑን ስፋት ያህል ነገር ጨበጠ። ከፍ አድርጐ ሲይዘው ክባዱ ነገር በሰበት ሃይል ድጋፍ ተዘረጋጋ። አረንጓዴ፣ ፈዛዛና አስጠሊታ ነገር ነበር። የዝሆኑ ጆሮ በሻጋታ ቅርፅ የማይታወቅ ነገር መስሏል። ሲዘረጋ፣ ነጣ ያለ ደቃቅ፣ የተበላሸ ዱቄት የመሰለ መርዛማ የደመና ብናኝ ፈሰሰበት። አስጠሊታ መልክ ያላቸው ነፍሣት በገጠማቸው ድንገተኛ ድንጋጤ በየአቅጣጫው እግሮቻቸው፣ ክንፎቻቸውና አንቴናዎቻቸው የረዷቸውን ያህል እየዘለሉ ተፈተለኩ። በዚያ ክፍል ሁሉ ውስጥ፣ በሚያስፈራ የመንጋ ብዛት ተፈተለኩ።

በነገሩ የመበስበስ ሁኔታ ጆን ባፕቲስት ነፍሱን ሣተ። ዙሪያውን ሁሉ በተስፋ መቁረጥ መልክ ተመለከተ። የሚያደርገው ቢያጣ ከፊት ለፊቱ የሚገኘውን ብል ያነከተውን ጨርቅ ማራገፍ ሲጀምር ታምኮ የከረመውን ቆሻሻ ወደ አየር ውስጥ ናኘው።

ለአፍታ ያህል የመደነቅ ሁኔታ የነበረበት የቤተመንግስቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት አጀብ በሁካታ ተተረማመሠ።

«ንጉሡን! ንጉሡን! ያገር ያለህ!» ሲል አንድ ድምፅ ጮኸ። ፖንቻርትሬይን ይመስላል። «በዚህ ውስጥ ፈፅሞ እንዲተነፍሱ እንዳታደርጓቸው»



ስዊሣውያኑ ዘበኞች የንጉሡን ወንበር አሽከርክረው ወዲያውኑ ወደ ሰገነቱ በሚያደርሰው በር በኩል ይዘዋቸው ወጡ።

«ዘብ! ዘብ! ዘብ ጥሩ!» ሲል ሌላ ድምፅ ጮኸ

«ሐኪም»

በዚያ የተሰበሰበው አጀብ ሁሉ ጆን ባፕቲስትን ትቶ ሸሸ። እርሱ ግን ብቻውን ቅርንጫፈ ብዙ በሆነው ተንጠልጣይ የሻማ መብራት ሥራ ተገትሮ ቀረ። ሌሎቹ በየጥጋጥጉ አራት ትንንሽ ስብስብ ሰርተው ይታያሉ።

የሆነ አንድ ሰው «መርዝ» ሲል ተናገረ። ይህ ቃል እንደተሰማ በቤተመንግስቱ አጃቢ አባላት ዘንድ የማይረሳ ድንጋጤን በመፍጠሩ፣ እያንዳንዱ አፍንጫ ወዲያውኑ በመሃረብ ወይም እጅጌ ላይ በተንጠለጠለ ጨርቅ ውስጥ ተቀበረ። ዘቦቹ በሩን በርግደው ወደ ክፍሉ ውስጥ ገቡ። ስድስት የሚሆኑ ሰዎች በያዙት የመስኬቶ ጠመንጃ ሰደፍ ጆን ባፕቲስት በእጁ ላይ የነበረውን ደስ የማይል ሽታ ያለበትን ገዳይ ነገር እንዲጥል እጆቹን በመምታታ ተረባረቡበት። ግርግዳው ላይ የነበረውን መጋረጃ በጥሰው ጥለው ሣጥኑንና ሌላውንም ሁሉ ነገር ጠቅልለውበት ወደ እሣቱ ውስጥ ጣሉት። ቤቱም እንዲናፈስ ተደረገ። በስብሰባው ላይ የነበሩትም እርቆ አሳቢ የሚባሉ አጃቢዎች፣ ጆስዊቶች ከቆይታ በኋላ እንዲወጡበት በተፈቀደላቸው ጋለሪ ዴስ ግላሴስ በኩል አለፉ።

ንጉሡን ለማየት ክፉኛ ተጨንቀው የነበሩት አባ ዴ ላ ቾይዝ፣ ንጉሡ ነገስቱ ለደህንነታቸው ሲባል በመጨረሻ ላይ ወደ ተወሰዱበት ክፍል ገቡ። ፋጐን የተባለው የንጉሡ ሐኪም፣ በተነነው ነገር ሣቢያ ምንም የመርዝ ምልክት እንደሌለ አስረዳ። ለጥንቃቄ ሲባል ግን አንድ ጉድጓዳ ሣህን የፈላ የአህያ ወተት አዘዘ። ጆስዊቱ ሲደርሱ፣ ፖንቻርትሬይን ከማማከሪያው ክፍል አስቀድሞ ሄዶ ነበር። ላ ቾይዝ፣ ከንጉሡ ነገስቱ እግር ስር ወድቀው ይቅርታ መለመን ጀመሩ።

«ይተዉ» አሉ ሉዊስ 14ኛ «ይነሱ አባቴ። ይህ ምንም ማለት እንዳልሆነ ያረጋግጣል። ከኔ ይልቅ ስዊሳውያን ጠባቂዎቼ በጣም ፈርተው ነበር። እኔ ግን በዚህ ወንበር ላይ እስረኛቸው ሆኜ . . . »

«ጃንሆይ በሆነው ነገር ሁሉ በጣም አዝናለሁ»

«የሚያመጡልኝን ገፀበረከት ለኔ ከማቅረብዎ በፊት ይመልከቱት» አሉ ንጉሡ በትህትና በመጠኑም የምፀት ቅላፄ ባለው አነጋገር።

«ማየትማ . . . »

«ይህን አጋጣሚ እዚሁ ላይ እናቁመው።» አሉ ንጉሡ አቋርጠው። «ያውቃሉ፣ ክፉ ነገር ይመጣል ብዬ እሰጋ ነበር። ሰውዬው የሚታመን አይመስልም። ከየአቅጣጫው ጠንካራ ጥርጣሬዎችን ሰምቻለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰውዬው አስመሳይ አጭበርባሪ ነው ብለው ብዙዎች ፈርተው ነበር። እርስዎንም የነገሩኝን ሁሉ ሰምቼ ነው ልቀበለው የተስማማሁት»

«ጃንሆይ፣ ድርጊቱ ጥሩ እንዳልሆነ እኔም እስማማለሁ። ነገር ግን በኛ በኩል ሰለሰጠው መግለጫ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ እንኳ አልነበረንም»

«አባ፣ እርስዎ ቅዱስ ሰው ነዎት። የዚህን ጋኔን ማንነት በማጋለጥም፣ከፊት ለፊትዎ ከሚቆም ሥጋ ከለበሰ ወስላታ ይልቅ እርስዎ ይበልጥ የሰለጠኑ ይሆናሉ።»

ንጉሡ፣ ጋኔን የሚለውን ቃል ሲጠቅሱ፣ ለንስሃ አባታቸው እየተናገሩ ነበርና ድንገተኛ የሆነ እንቅጥቃጤ ያጋጠማቸው ጊዜ ትዝ አላቸው። እናም አሁን በአዒው አትኩሪት ላይ የፍርሃት ጥላ ለአመል ያህል ሲያጠላባቸው፣ አባ ዴ ላ ቸይዝ ተመለከቱ

«ንግግርዎ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥረት እንዳደርግ ያደርገኛል» አሉ ጀስዊቱ በትህትና

«አያስፈልግም። በርስዎ ላይ ያለኝ እምነት ይቀጥላል። የርስዎን የሃይማኖት ሥርዓት እንደማይደንቅና ከመቸውም የበለጠ እምኜ መቀበሌን እንዲያውቁ። ቻይናን በሚመለከት፣ ፔኪንግ የሚገኘው መልዕክተኛችሁ ሙሉ ድጋፍ እንዲያገኝ አዝዣለሁ።»

«የተቀደሰ ተግባር ነው»

«አቢሲኒያን በተመለከተ፣ ስድስት ሰዎች ግን ወደዚያው ለመላክ ዕርዳታዬን ጠይቀዋል። ልክ ነኝ?»

«አዎን፣ ጃንሆይ»

«ፈቅጄልዎታለሁ። ነገር ግን ሕዝባዊ ጉዳይ እንዳያደርጉት»

«ዕድሜ ይስጥልኝ ግርማዊ ሆይ»



«ይህን ተጓዥ የተባለ ሰው በተመለከተ ግን» ሲሉ ንጉሡ ቀጠሉ። «አስቀድሞውኑ ሊወሰድ ይገባው የነበረውን እርምጃ አሁን ወስጃለሁ። ሰውዬው፣ በዕውቅ ምሁራን አወያዮች፣ እውነቱን ይናገር እንደሆነና እንዳልሆነ ይፈተሻል። እነዚህ ምሁራን፣ ሰወዬው አታላይና አስመሳይ አለመሆኑን ከተስማሙ በኋላ የሚለውን እንሰማለን።»

«የአካሄድ ሥነ ስርዓቱ በጣም ተገቢ ነው፣ ጃንሆይ። እኔ ግን፣ ይህ የምሁራን አወያይ የሰውዬውን ጉዞ እውነተኛነት እንደሚመሰክርለት ርግጠኛ ነኝ»

«እስቲ እናያለን» አሉ ንጉሡ

«እንግዲያው፣ አባቶቻችን ሳይዘገዩ ወደ አቢሲኒያ መጓዝ ይችላሉ»

«ደስ ካለዎት ነገ ይችላሉ» አሉ ንጉሡ። ጀስዊቱ፣ ለመውጣት ነፃ መሆናቸውን ለመግለፅ ከጠረጴዛቸው ላይ ምልክት የሚሰጡበትን የቆዳ ማህደር አያነሡ።

አባ ዴ ላ ቸይዝ፣ በረዥሙ የመተላለፊያ ክፍል አድርገው ተመለሱ። አብረቅራቂው የሻማ ማብሪያ የጠርሙስ ድንጋይ፣ ጥቁር ነፀብራቅ ይታይበታል። በውጭ በኩል ቀኑ ቀለል ብሏል። ፀሐይ በመጥለቅ ላይ ስለሆነች ከሰዓት በኋላ የነበረውን ደመና ነፋሱ ጠራርጐታል።

አሻቢ አድማጮችን እንዲህ ባለ የተቀናበረ ዘዴ፣ የሰሙየውን ዕቅድ እንዲቋረጥና ዓላማው እንዳይሳካ ማድረግ ብልህነት ነው ሲል ፖንቻርትሬይን አስቦ ነበር ሲሉ ጥቁር ቀሚስ የለበሱት ሰው እየተጣደፉ ሲሄዱ አሰቡ። ንጉሡ እኛን እንዲጠነቀቁን እንዳሳሰባቸው ሁሉ ደካማ የሆነ አጋጣሚ ሲደርስም፣ እንዲሁ ሌሎችን አስጠንቅቋቸው ነበር። በመጨረሻ ግን ተሸናፊ ሆነ። ግርማዊነታቸው ስላሳዘኑን ይቅርታ ጠይቀው፣ የጠየቅነውን ሁሉ ፈቅደውልናል።

ወደዘቦቹ ክፍል በር ሲደርሱ፣ ይህ ፖንሴ የተባለ ሰው ጥሩ አድርጐ ቢያገለግለንም እንደ ጅል ነበር ሲሠራ የነበረው። ከዚህ በኋላ በርሱ ላይ የምንተማመን ባንሆንም በእርሱ ዝና ላይ የሚፈፀም ማንኛውም ጥፋት በኛ ላይ ሊንፀባረቅ ስለሚችል ልንከላከልለት ይገባናል።

# 8

የመጨረሻው የአምስት ሰዓት ደወል ከመደወሉ በፊት፣ ሰረገላው በቅዱስ ኢዩስታቼ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ቆመ። ሌ ቢዩ ኖሬ አበገብ፣ ባልፀዱ መስኮቶች ዘልቆ ከሚታየው ደብዛዛ የሻማ ብርሃን በስተቀር ጉዳናው ድቅድቅ ባለ ጨለማ ውስጥ ነበር።

ጆን ባፕቲስት ወጥቶ በሩን ዘጋው። በቀጥታ ወደመዝናኛው በማምራት ፊንታ የአማካሪውን በር ለመቆርቆር በጋሪው በኩል ዞሮ ሄደ።

«ምን?» ሲሉ፣ አባ ፕላንቴይን የሰረገላውን በር በከፊል እየከፈቱ አንሾካሸኩ። «እዚያ ትንሽ ሆቴል ውስጥ አትኖርም ማለት ነው?»

«እንደሚያዩት» አለ ጆን ባፕቲስት በሩን በመቆርቆሪያው ሁለት ጊዜ እየመታው።

በመጨረሻም በሩ ተከፈተ። አማካሪው ራሣቸው ባትሪ ይዘው መጡ። አባ ፕላንቴይን ደነገጡ። በራሣቸው ጋሪ ጥላ ውስጥ ራሣቸውን ደበቁና ነጂው ፈረሶቹን እንዲገርፋቸው ምልክት ሰጡት። ከሁለተኛው ጋሪ ውስጥ ሁለት ዘቦች ወረዱ። ከጨርቅ በተሰራ ባርኔጣ ተሸፍነው መስኬቶ ጠመንጃ ይዘዋል።

«ፈጠን ብለህ ግባ» ሲሉ የተከተሰውን አጃቢ ያላዩት ሣንግራይ አንሾካሸኩለት።

«ብቻዬን አይደለሁም» ሲል ወደተከተሉት ሁለት ወታደሮች እያመለከተ ጆን ባፕቲስት ተናገረ።

«በንጉሡ ትዕዛዝ መሠረት።» አለ አንደኛው ለአማካሪው «ከዚህ ሰው ጐን እንለይም። ለመሆኑ ከርስዎ ጋር ነው የሚኖረው?»

«እኔ እስከማውቀው ድረስ» አሉ ሳንግራይ

«እንግዲያውማ ለኛም ጭምር አንድ ትንሽ ክፍል ሊያዘጋጁልን ይገባል»

አማካሪው፣ ፓንሴ እንዲያልፍና ዘበኞቹም እንዲከተሉት ካደረጉ በኋላ በራቸውን ቀረቀሩ። የአዳራሹ መተላለፊያ በረዶ ሆኗል። ነገር ግን፣ ሣንግራይ ለወታደራዊ ሰዎች ብዙም ደንታ ሣይኖራቸው የሌሊቱን ማረፊያቸውን በዚያ እንዲያደርጉ ጋበዟቸው። ከዚያም ጆን



ባፕቲስት በእሣቱ ዳር ሆኖ ወደሚጠብቃቸው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ። ሁለት ትላልቅ ግንዶች ደስ በሚል ሁኔታ እየተንጣጡ ይንበለበላሉ።

«በአንድ ሰዓት አካባቢ ትመለሣለህ ብዬ ገምቼ ስጠብቅህ ነበር» አሉ አማካሪው ዝቅ ባለ ድምፅ። «ይሁን እንጂ ድጋሚ አላይህም በሚል ተስፋ መቁረጥም ጀምሬ ነበር። ነገ ወደ ፓላስ ሮያሌ ወይም ወደ ቅዱስ ክላውድ ሄጄ ስላንተ ዜና ለማግኘት እሞክራለሁ እያልኩ ነበርኩ»

ጆን ባፕቲስት ባለመደገፊያው ወንበር ውስጥ ዝልፍልፍ ብሎ ወደቀ። እጆቹንና እግሮቹን ወደ እሣቱ ዘረጋቸው። አይኖቹ ባዶ ነበሩ። ሣንግራይ ካዩት ጊዜ ሁሉ አሁን እጅግ በትካዜ ላይ መሆኑ ይታወቃል። ወዳጁ ስላስገደዱት ምንም እንኳ በፊቱ ላይ የሚነበብ ነገር ባይኖርም፣ ወጣቱ ሰው ከንጉሡና ከአጃቢዎቻቸው ጋር የነበረውን ታሪክ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ተረከላቸው። ከዚያም ወደ እስር ቤት መወሰዱን ገለፀላቸው። በተለይም ራሱን መድሃኒት ቀማሚ ነኝ ብሎ ስለተናገረ መስኬቶ ጠመንጃ ያነገቱት እስረኛ ነው ብለው አምነዋል። ሙሉ በሙሉ እንዲናዘዝም መደብደብ ጀምረውት ነበር። «ለንጉሡ ያመጣሁላቸውን ንፀበረከት እንዲመረመር አምጡት፤ እናም እናንተ የምትገምቱት ነገር ጨርሶ እንዳልሆነ ታያላችሁ» በማለት ጆን ባፕቲስት ነግሯቸው ነበር።

ይህን ከሰሙ በኋላ፣ የዘቦቹ አለቃ፣ ሣጥኑን እሣቱ ውስጥ በመወርወራቸው የወንጀሉ ማስረጃ መጥፋቱን ተገነዘበ። አንዳች የቀረ ነገር ቢኖር አንድ በአንድ ከእሳቱ ውስጥ ተለቅሞ እንዲወጣ አዘዘ። የሣጥኑ እንጨት ነድዶ አልቋል። ይሁን እንጂ በአመዱ ስር ብዙ ጥብቅብቅ ያሉ የጆሮ ቁርጥራጮችን ለማግኘት ቻሉ። አንድ ለስላሣ ፀጉር ያለው ውሻ ይህንን ቁራጭ እንዲቀምሰውም አመጡ። ውሻው የተጠበሰውን ስጋ ተንገብግቦ ዋጠው። እንዲያውም ድጋሚ የሚፈልግም መሰላቸው። ሙራድ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው በማጣፈጫ ቢሠራ ምግቡ ለጤና አዋኪ አይደለም።

በመጨረሻም ጆስዊቶቹ ከአንድ ፀሐፊ ጋር ተመለሱ። ጠመንጃ አንጋቾቹ ተጠርጣሪውን እንዲለቅቁትና በተማሩ ሰዎች እስኪመረመር በአይነቁራኛ እንዲጠብቁት መመሪያ ሰጧቸው። ከዚህ በኋላ የሚታዩ ብዙ ሥርዓቶች አሉ። ዘቦቹ አንድ ጊዜ ከተመረጡ፣እስኪዘጋጁ ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። በመጨረሻም ሁለቱ ጋሪዎች በዚያ ቀዝቃዛና ጨለማ ሌሊት ከፓሪስ ወደ ቬርሣይለስ ተጓዙ።

«ኧረ! እንግዲያው ከዚህ ያለፈ የለም ማለት እኮ ነው» አሉ ሣንግራይ፣ ታሪኩን ሰምተው ሲያበቁ እየሳቁ።

ጆን ባፕቲስት ትከሻውን ሰበቀ

«ይህ በቂ ይመስለኛል»

«አዎን እንዳልከው በቂ ነው። ያጋጠመውም ጥፋት በጣም መጥፎ አይደለም። ያንን የሻገተ የዝሆን ጆሮ ይዘህ ቆመህ በነበረበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ እንደገና ንገረኝ እስቲ . . . »

መሣቅ ጀመረ። ሲጀምር፣ ወዳጁን ላለማስቆጣት በጥንቃቄ ነበር የጀመረው። በኋላ ግን ያለፉት ሰዓታት በሣንግራይ ላይ ያሣደሩት ስጋትና ስቅዞ የመያዝ ሃይላቸው እየለቀቃቸው መጣ። የመመጠን ችሎታው ጠፍቶባቸው ባሪያ እስኪሰነጠቅ ድረስ ከልባቸው ሣቁ። መላ ሰውነታቸው በውቅያኖስ ማዕበል እየተርገፈገፈ ያለ እስኪመስል ድረስ ሣቁ። ዘቦቹ ጆሮአቸውን በሩ ላይ ለጥፈው ያዳምጣሉ። ጆን ባፕቲስት ራሱ ተደንቆ በግልፅነታቸው አውካካ። ብዙ ካወሩና ከብዙ ድግግሞሽ በኋላ፣ እንባዎቻቸውን ከአይኖቻቸው ላይ በመጥረግ ተረጋጉ።

«ያው ያው ነው። ሁሉንም ነገር አጥቻለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት እንደገና ወደ ቁምነገሩ እየተመለሰ።

«አይመስለኝም።» አሉ ሳንግራይ፤ ተንፈስ ለማለት የሰደሪያቸውን ቁልፍ እየፈቱ። «እንዲያውም እንደ እውነቱ ከሆነ በተቃራኒው ነው። የዚያ ዝሆን ጆሮ ሕይወትህን አድኗታል። ለአጭር ጊዜም ቢሆን ወህኒ እንድትወርድ ወይም በነዚያ ረገኙም ጆልባዎች ላይ ቀዛፊ እንድትሆን በባርነት ስትጉላላ ይታየኝ ነበር»

አማካሪው በድጋሚ ሃዘንና ትካዜ ውስጥ የገባውን ጆን ባፕቲስትን ሲያስተውሉት «ሆኖም ግን» ቀጠሉ። «ሳከናውነው አስቤ የተንቀሣቀስኩበትን ነገር ሁሉ አጣሁት»

«ኦ! ውድ ወዳጄ፣ ነገም ሌላ ቀን ነው። እንዲህ ያለውን ማላዘንህን ለመስማት ስሜቴ ዝግጁ አይደለም። ምክንያቱም ሲበዛ ታጋንነዋለህ። የምመክርህ፣ከዚህ ስሜታዊ የሙከራ ዕለት ጉዳይ በኋላ፣ ዛሬ ማታ ለሁለታችንም እጅግ አስደሣች ስሜትን ከፈጠረልን ከዚህ ሞቅ ያለ ሣቅ አለመሸሽ ብቻ ነው። ወደ መኝታህ ሄደህ በሕይወት መኖርህን ብቻ አስበው። ይህ እውነታ ደግሞ በተለይም የሚፈትን ጉዳይ በገጠመን ዕለት፣ መጨረሻ ላይ ሲሆን የመደነቅና የእርካታ ምንጭ ሊሆነን ይገባል»



ይህን ካሉ በኋላ ጆን ባፕቲስትን እንደ አባት አቀፉት። ባኂፉን ይዘው ወደ መኝታ ቤቱ በመምራት መልካም ለሊት ለእንግዳቸው ተመኙለት።

የሚቀጥሉት ቀናት የባሱና የሚያስፈሩ ተከታታይ መጥፎ ወሬዎች የሚመጡባቸው ሆኑ። በመጀመሪያ የቤተመንግስቱ ሹማምንት በዚያው በቤተመንግስቱ ውስጥ አናፈሱት። ከዚያም ጋዜጦቹ በከተማው ውስጥ ነዙት። የዚያን ደስ የማይል ሽታ የነበረውን ነገር ትክክለኛ ምንነት የሚያውቅ ማንም ስላልነበረ፣ ፖንሴ፣ ንጉሡ ፊት ቀርቦ ለመታየት ድፍረቱ ነበረው። ወሬው እንደ አስቂኝ ጉዳይ ሣይሆን፣ አንድ ተንኮለኛ እንዳከናወነውና በንጉሡ ሕይወት ላይ እውነተኛ ሙከራም ሊፈፀም ይችል እንደነበረ ተደርጐ ተነዛ። እጅግ መጥፎው አሉባልታም፣ በጆን ባፕቲስት ላይ ተሠራጨ። በግልፅ አስመሣይ፣ አታላይ፣ ተብሎም ተወነጀለ። ሴራውም፣ በጀስዊቶች ጠላቶች በምስጢር ተራገበ። የነዚህ ሴረኞች ዓላማ ወጣቱን ተንኮለኛ በትንሹ ለመክሰስና የተባባሪዎችን ዝናና ክብር ግን ለመጉዳት የታሰበ ነበር። ነገር ግን፣ የጀስዊቶቹ ደረጃ ከፍ ያለና የማይደረስበት ስለሆነ በጭቃው ውስጥ እንዲጐተት የተፈረደበት እርሱ ሆነ።

ጆን ባፕቲስት በፍጥነት ይጀመራል ብሎ ተስፋ ያደረገበት የፍርድ ሂደት፣ከብዙ ሣምንታት በኋላ እንደሚሆን ፕሮግራም ወጣለት። ጉዳዩን ለመስማት ብቃት ያላቸው ከሕዝብ የተመረጡ ምሁራን መሰብሰብና፣ ሥረ-ነገሩንም ለማጥናት ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። አዝማሚያዎች ሁሉ የሚያመላክቱት፣ምርመራው ሊጀምር የሚችለው ከጥምቀት ዓመት በዓል በኋላ ነው።

በመጨረሻም፣ ንጉሡ ጥያቄአቸውን ተቀብለው እንደፈቀዱላቸው፣ ጀስዊቶቹ፣ ለጆን ባፕቲስት ነገሩት። ይህ እውነታ፣ እርሱ በዋና ከተማው ውስጥ ከታሰረበት ጉዳይ የተለየ መልክ ተሰጥቶት ነበር። ስድስት ጀስዊት ካህናትን የያዘ አንድ የመልዕክተኛ ቡድን በሚቀጥለው ሣምንት መጀመሪያ ላይ ጉዞውን ይጀምራል። በዚህ ቡድን ውስጥ አንድ ሐኪም፣ አንድ የእፅዋት ሊቅ፣አንድ ጥላን ነጻፊና አንድ የሥነ ከዋክብት ተመራማሪ አሉበት። ከነዚህ መካከል ሦስቱ መልዕክተኞች የመጡት በክፍላተ ሃገራት ከሚገኙ ገዳማት ሲሆን፣ ሁለቱ ከፍልስጤም እና የቀረው አንዱ ከአስቱሪየስ ናቸው። የእየሱስ ማህበረሰብ እነዚህን ሚሲዮናውያን ሁሉ ከያሉበት ቦታ በቀጥታ በማጓጓዝ እስክንድሪያ ውስጥ እንዲገናኙ

ያደርጋቸዋል። ይህ ማለት እነዚህ ሚሲዮናውያን፣ ፈረንሣይ ውስጥ አይሰባሰቡም ማለት ነው። ይህ መጥፎ እድል እንደሆነ ካህናት አባቶች ይገምታሉ። ምክንያቱም፣ አስቀድመው ከፖንሴ ሊያገኙት የሚችሉትን ጠቃሚ ምክር አያገኙም ማለት ነው። ይሁንና ካይሮ ከደረሱ በኋላ ግን፣ ፖንሴን ባለማግኘታቸው ያጡትን ሁሉ በጉዞው ላይ አብሯቸው እንዲመለስ ከሚያደርጉት ከሙራድ ያገኙታል።

ያለርሱ ፈቃድ አርመናዊውን ሊገለገሉበት እንደማይችሉ፣ ጆን ባፕቲስት ሊቃወም ፈልጐ ነበር። ይሁንና እነዚህን ሰዎች ከዚህ እንቅስቃሴአቸው የሚገታበት ምንም መንገድ እንደሌለው ወዲያውኑ ተገነዘበ።

የታህሳስ ወር እየተጋመሰ ነው። የክረምቱ የቀን ርዝመት አጭርና ጨለማ ሆኖ፣ ከሌሊቱ የማይለይበት ወቅት ደረሰ። ሻማዎችና ጧፎች ባለማቋረጥ ይበራሉ። የፖሪስ ከተማ ነዋሪዎች ከምድጃቸው አጠገብ በሰንሰለት የታሰሩ ይመስል እዚያው ይውላሉ። የርሱ ጉዳይ በተጀመረበት አዲስ አቅጣጫ ሳቢያ፣ ጆን ባፕቲስት ስሜቱ በጣም ስለተጐዳ ያለበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ጭራሽ አጨልሞ ተመለከተው። ለንጉሡ የገባላቸውን ቃል ኪዳን ለማክበር እየፈለገ ሣለ፣ ይኸው በግማሽ ምዕተ ዓመት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጀስዊቶች ወረራ ወደ አቢሲኒያ ሲንቀሣቀስ፣ ለዚህም ሃላፊነት ተሰማው። በአሊስ ልብ ውስጥ ፍቅርና ተስፋ እንዲያብብም ተደፋፍሮ ነበር። ይሁን እንጂ አሁን ካለበት ሁኔታ የሚወጣበት ምንም ተስፋ ስለሌለው በርሷ ውስጥ ለማይፋቅ ስቃይና ቅሬታ መነሻ ይሆናል። እንዲያውም ስሙን አጭበርባሪና ሰዎችን የሚያሳዝን ምትሃተኛ አድርገው ስለበከሉበት ከበፊቱም የባሰ መከራ ውስጥ የወደቀ መሰለው።

ሣንግራይ በበኩላቸው፣ የቻርትሬሱን መስፍን፣ በፖላስ ሮያሌ ውስጥ እንዳገኟቸውና ስለጆን ባፕቲስት ሽንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱ እንደሰሟቸው በመንገር ሊያስደስቱት ሞከሩ። ጭውውታቸው፣ ጆን ባፕቲስት፣ በንጉሡ ህይወት ላይ ስለቃጣው መከራ፣ ንጉሡ ባሉበት ቦታ ያልታወቀ ሰይጣናዊ ነገር እያወዛወዘ ከውስጡ መርዛም ትናኝ እንዲወጣ ስለማድረጉ ወደሚለው ርዕስ ዞረ። «እንደተለመደው አጕቴ በማያስፈራ ነገር ሁሉ ይፈራል» አሉ መስፍኑ እየሳቁ። «ከአቢሲኒያ ምን ሊቀበል ነበር የጠበቀው? የስዊስ የጊዜ መለኪያ ሰዓት እንደሆነ አይጠረጠርም» ይህን ድንገተኛ መልካም አስተያየት ከሰሙ በኋላ እማካሪው፣ መስፍኑን ወደ አንድ ጥግ በመውሰድ፣ ፖንሴ የርሣቸው እንግዳቸው መሆኑን ነገሯቸው። መስፍኑም፣ ጆን



ባፕቲስትን ለማግኘት የጓጉ መሰሉ። ይህን አይነቱን ቅርርብ ምን መልካም ነገር ሊያስገኝ እንደሚችል አሁን ፈጥኖ ለመናገር ቢያስቸግርም ቅሉ፣ ቢያንስ የተስፋ ጭላንጭል ፈንጥቆላቸዋል።

ከዚህ ታሪክ ጆን ባፕቲስት ምንም አይነት ማፅናኛ ያገኘ አልመሰለ አለው። ባለማቋረጥ በአፖርታማው ውስጥ ባለው የእሣት ማንደጃ አጠገብ ቁር እንደተሰኘ ይቆያል።

«እንግዲያው ለምን አትፅፍም» አሉት ሣንግራይ በመጨረሻ ላይ ትዕግስታቸው እያለቀ። «አዎን፣ ፃፍ፣ አንድ ሰው የትም ለመሄድ ሳይሆን፣ ብቻ እንዲሁ ወደፊትና ወደኋላ በመራመድ እየተንቀሣቀሰ ብርድ እንዳይገድለው ሊያደርግ ይችላል። አንድ ጊዜ ትውስታዎችህን ሁሉ ሰብስብ አድርገህ፣ ያየኸውንና ያከናወንከውን ሁሉ ታሪክ ብትናገር ለዳኞችህ የምትመልስላቸውን ሁሉ በእርግጠኝነት ልትነግራቸው ትችላለህ።»

ጆን ባፕቲስት ይህን ምክር ተቀበለ። ሲጀምር ትጋቱ እምብዛም ነበር። እያደር ግን የራሱን ትውስታዎች በመፃፍ ውጥኑ ውስጥ ይበልጥ እየተማረከ መጣ። በክረምቱ፣ በከተማዋ የመከራ ሃሣቦች ውስጥ ከመዋኘት ይልቅ፣በአቢሲኒያውያን አምባ ምድር ላይ የቆየባቸውን ብሩህ ቀናት፣ በፈረስ ላይ ሆኖ ድኩላን መከተል፣ የንጉሡ ጠባቂዎች የወርቅ ጋሻቸውን አንግተውና የነብር ቆዳቸውን በትከሻቸው ላይ ለብሰው ማየት ጭንቀቱን አቀለለለት። ጐንደር በቅመማት ገበያ ውስጥ መዘዋወር ጀመረ። ቀረፋውንና ቀዩን በርበሬ ማሽተት ቀጠለ። ምሽቱ ገና ለዓይን ያዝ በሚያደርግበት ድንግዝግዝ ሰዓት፣ ጅቦች ሲጮሁ መስማት ቻለ። ሴቶች በጐኑ ሲያልፉ ረዘም ላለ ጊዜ ኮስተር ያለ እይታ ሲወረውሩበት፣ ዐይኖቻቸውም በቅፅበት ነጭና ጥቁር እየሆኑ ሲያንፀባርቁበት ታየው።

በአፖርታማው ቤቱ ውስጥ ባለው በእሣቱ ዳር ተቀምጦ ከንጋት እስከ ምሽት ይፅፋል። ዘቦቹ በመኖሪያ ቤቱ በር ላይ ያለባቸውን ጥበቃ ተራ በተራ በመግባት ሥራቸውን አቀለሉት። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ቀኑን ሙሉ ሳያዩት ይውላሉ። ከዚያች ከተጐሣቆለች ሻንጣው ውስጥ አቢሲኒያውያን የሚለብሱትን ከጥጥ የተሠራ ልብስ ከነጠባብ ሱሪውና በጥንት ዘመን ሮማውያን በትከሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉት የነበረውን አይነት በቀጭኑ በባለቀለማት ክሮች የተጠለፈ የአንገት ልብሱን አወጣ። እነዚህን ልብሶች ከኢትዮጵያ በርግጠኝነት ለምን እንዳመጣቸው ባያውቅም ለሆነ ሰው በስጦታ ለማቅረብ አስቦ ነበር። አሁን ግን እርሱ ራሱ በክፍሉ ውስጥ ስለለበሳቸው ተደሰተባቸው። በወገቡ ላይ ለፈረንሳዩ ንጉሥ እንዲሰጥ ታስቦ

የነበረውንና፣ ጂስዊቶች እንዳይሰጥ የከለከሉትን ቀቡቶ ታጠቀ:: እንደ አቢሲኒያውያን ከለበሰ በኋላ ጆን ባፕቲስት ለጉዳዩ ይበልጥ መቅረቡ ተሰማው:: አለባበሱን፣ ንጉስ እያሱ ሲለያቸው የሰጡትን የወርቅ ሰንሰለትና በአንገቱ ላይ የሚያንጠለጥለውን አልማዝ በማጥለቅ የተሟላ አደረገው:: እኒያ በርቀት ቦታና በአጠራጣሪ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ንጉስ፣ የወዳጅነታቸውን ማረጋገጫ እንዲሆኑ የሰጡትን እነዚህን ዕቃዎች ያዘና ሁሉም ነገር በሕይወቱ ላይ ጥርጣሬን ለማጫር በተነሳበት ጊዜ፣ ጆን ባፕቲስት በትጋት የመንቀሳቀስ ነገር ተሰማው:: የቀን ህልሙንም በተሟላ የትረካ ዘዴ ስላሰፈረው፣ ከለበሰው ነጭ ልብስ ጋር የተጣጣመ ነበር:: ሳንገራይም፣ ከእንግዳቸው ጋር ምግባቸውን አብረው ሲበሉ በዚህ ዓይነት የተሟላ ትጥቅ ሆኖ ማየትን እየለመዱት መጡ::

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ሙሴ ራኦል፣ አንድ በድንገተኛ የሚጥል ሕመም የተያዘን እንግዳ፣ በአስቸኳይ አይቶ እንዲመረምር ጆን ባፕቲስትን ጠራው:: የጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕዛዝ፣ ጆን ባፕቲስት ከንጉሣውያን ቤተሰብ እስከራቀ ድረስ በዘበቴዎች እየታጀበ እንዳይወጣ የሚከለክል አልነበረም:: በመጠጥ ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ይህን ነጭ ለብሶ የወርቅ ቀበቶ ታጥቆ፣ በሁለት ጠመንጃ አንጋቾች ታጅቦ የመጣውን ወጣት ሰው እንደተመለከቱ፣ ሁሉም እንደ አንድ ሰው ከመቀመጫቸው ላይ ብድግ አሉ:: ግራ የተጋቡት ጠጪዎች፣ ሳይታሰብ አንድ ልዑል ከምሥራቅ በበራሪ ምንጣፍ ላይ ሆኖ የመጣና ንጉሡም ለክብሩ ሲሉ በንቁ ወታደሮች እንዲታጀብ ያደረጉት ሳይሆን አይቀርም ሲሉ አሰቡ:: በሆቴሉ ውስጥ እራታቸውን በመብላት ላይ የነበሩ ነጋዴዎች ይህን የመሰለ ድንቅ ሰልፍ፣ ባረጀው የደረጃ መውጫ ላይ ደርሶ ከነርሱ አንዱን ለመጐብኘት መምጣቱን ሲመለከቱ ይበልጥ ተገርመዋል:: በኋላ እንደታየው፣ ጆን ባፕቲስት ለሰውዬው የሚያደርግለት ምንም ነገር የለም:: ነጋዴዎች ወደነበሩበት ክፍል ሲገባ፣ ሕመምተኛው በባዕረ ሞት ሲንፈራገጥ አገኘው:: ሐኪሙ ለቅቆ ሲወጣ፣ እስከራት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደታችኛው ፎቅ ተወሰደ:: ተመልካቾች ሊሆን የሚችለውን ሁሉ ዝቅ ባለ ድምፅ ይወያያሉ:: ብዙዎች የቻብሊሱን የወይን ገበሬ በመደገፍ ቆሙ:: ይህ የወይን ገበሬ፣የነጋዴዎቹ ጓደኛ በጉዞው ዘመን በአንድ ራቅ ባለ ቦታ ሃይማኖቱን እንደለወጠ ስለሚታመን፣ ለሟቹ የመጨረሻውን ፀሎት ፍትሀት ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ነጭ የለበሰ አንድ እንግዳ ቄስ ተገኝቷል ሲሉ አወሩ::

የለበሰውን ለብሶ አንድ ጊዜ ከቤት ወጣ ስላለ ይህንን አለባበስ ዳግመኛ የማያደርግበት ምክንያት እንደሌለው ጆን ባፕቲስት አሰበ:: ሙሴ ራኦል፣ ውይይት ለማድረግ የሚቀርብለት



ጥያቄ በረከተ:: እርሱም ጥያቄዎችን ለማርካት በመቻሉ ደስተኛ ሆነ:: ጆን ባፕቲስትም ድሆችን ብቻ ለማየትና ምንም ክፍያ ላለመቀበል ተስማማ:: ስለርሱ ያለውን እውነታ በዚያ አካባቢ ቀስ በቀስ እየታወቀ መጣ:: ሕዝቡም፣ እርሱ በአጠገባቸው ሲያልፍ፣ ሁልጊዜም ከሰዓት በኋላ ቀደም ይልና ከፅሁፉ ላይ አረፍ ለማለት ፣ ረዥም ቁመናው በነጭ የአንገት ልብስ ተሸልሞና በሁለት የንጉሡ ወታደሮች ታጅቦ በየሰርጡ መንገድ ባሉ ደሣሣና ጉስቁላ ቤቶች ውስጥ በሕመም የሚያሰቃይ ልጅ ለማየት ሲወጣ ሲያዩት መደነቃቸውን ተው::

የርሱ ጉብኝት በሚወስደው በማንኛውም የፖሪስ ክፍል ውስጥ፣ ነዋሪዎች በቀላሉ «አቢሲኒያዊ» እያሉ በመጥራት በመንገድ ላይ ባገኙት ቁጥር በወዳጃዊ መንፈስ ሰላምታ ይሰጡታል::

# 9

"ባንተ አስተሣሰብ ቅብዐ ቅዱስ ምን ይመስላል?" በማለት በአንድ ትልቅ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ እግሮቹን በአንፃሩ ከተቀመጠው ከሙሴ ማቼ እግሮች ላይ አመሳቅሎ የተቀመጠው ሙሴ ዴ ማይሴ አስቸጋሪውን ጥያቄ ያቀረበው ዝቅ ባለ ድምፅ ነበር።

"ክቡር ሆይ፣ ማለት የምችለው … እርግጠኛ ሆኜ ባላውቀውም … ሳስበው ያው ዘይት ይመስላል" .

"ደህና" አለ ቆንስሉ ትንሽ እንደመቆጣት ብሎ "ግን ምን አይነት ነው ፣ መጠኑስ ፣ በምን አይነት ጠርሙስ ውስጥ ነው የሚቀመጠው"

"እ፣ ጥቂት ብቻ ነው የሚወሰደው፤ ግንባር ላይ መቀባት … ጥቂት ደግሞ እጆችን መቀባት"

"በእጭሩ፣ አንተም እንደኔው በአንድ ጀልባ ውስጥ ነን ማቼ" አለ ሙሴ ዴ ማይሴ ከተቀመጠበት ተለይቶት እየተነሣ "ምንም የምታውቀው የለህም"

"ምንነቱን ለማወቅ አጠያይቃለሁ" አለ ፀሐፊው በሚያስቆጣ ሁኔታ

"ምንም አልክ፣ ምንም ለውጥ አያመጣም፣ ካፑቺኖች ያውቁታል። እስቲ ለመሆን ሌላ ልጠይቅህ። ለመሆኑ ለነርሱ ይህን ነገር ማነው የሚያቀርብላቸው?"

"ወንድም ኢብራሂም የሚባሉ ሶሪያዊ መነኩሴ ናቸው። ለውዬው፣ የኮፕቲኩ ፓትሪያሪክ ስለሚያውቋቸው ይህን ቅብዓ ሜሮን ከርሣቸው እንደሚያገኙት ይናገራሉ"

"መቼ"

"ካፑቺኖች ተዘጋጅተው ሲያበቁ"

ሙሴ ዴ ማይሴ ብድግ ብሎ ቀመና ክባድ ባርኔጣ አጠለቀ። የታህሣስ ወር፣ ካይ ውስጥ ቀዝቃዛ ሊሆን ይችላል። ምድረበዳው ርቀት ባይኖረውም፣ ደሣሣዎቹ ቤቶ የተሠሩት የበጋውን ተናካሽ የአየር ጠባይ እንዲቋቋሙ ብቻ ተደርገው ነው። ቆንሲሉ፣ አሁ አሁን ሰው ሰራሽ ፀጉሩን አውልቆ አያውቅም። እንዲያውም ቁልቁል የወረደውን ረዥ ጫፉን በደረቱ ላይ በማሳለፍ ቅዝቃዜውን ይከላከልበታል።



"እንዲህ ከሆነ፣ እኔ እንደሚገባኝ ካፑቺኖች፣ ለአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት፣ ለንግስና በዓሉ ቅብዓ ሜሮን ሊያቀርቡለት ነው። የዚህን ዓይነት ሁኔታ የተከናወነው ደግሞ ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት ነበር።። ልክ ነው?»

«አባ ፖስኳል፣ ምንም ልዩነት አያመጣም ይላሉ። አቢሲኒያውያን ከቀረው አለም ራሣቸውን አግልለው ስለሚኖሩ፣ ግልፅ የሆነ ዕቅድና ዘዴ ወይም ተስማሚ መሣሪያ የላቸውምና የራሣቸውን ይጠቀማሉ። ይሁን እንጂ፣ ቅብዓ ሜሮን ስለሌላቸው ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ቅር እንደተሰኙ ናቸው። የሆነ ሰው ይህን የንግስና ሥርዓት ማስፈፀሚያ ዘይት ቢያቀርብላቸው ባለታላቅ ውለተኞች ይሆናሉ። ከአስራ አምስት አመት በኋላም እንኳ ቢሆን ሌላ የሥርዓተ ንግስ በዓል በጋለ ስሜት ያደርጋሉ»

ይህችን አነስተኛ ንግግር ካደረገ በኋላ፣ ሙሴ ማቼ ከፍ ባለ ድምፅ አሣለ።

«ጭቅጭቃችንን ለመቋጨት ስንል እንለፈው፤ ለመሆኑ አባ ፖስኳልን ሳያቸው አለመቻሌን ምን ብለህ ነበር ያስረዳሃቸው?» አለው ቆንሲሉ።

«ክቡር ሆይ፤ እርስዎ ይሻላል ብለው እንደነገሩኝ ጤና እንዳልሆኑ ነው የነገርኳቸው»

«አመኑህ ታዲያ?»

«እጠራጠራለሁ። ሆኖም ግን ነገ ተመልሰው ይመጣሉ። ክቡርነትዎ እንድነግርዎ ከፈቀደልኝ ሰውዬው የሚተው አይመስለኝም። እንዲያውም እርስዎ በገንዘብ ሊረዷቸው ቃል እንደገቡላቸው ይናገራሉ»

«ይህ የሚያበሳጭ ነገር ነው። ካፑቺኖች ቅብዓ ሜሮን እንዲያደርሱ በማለት ስጉዟቸው የምሰጣቸው የገንዘብ ድጐማ ሰበብ የለኝም። ይህንኑ ገልጨ ወደ ቬርሣይለስ መፃፍ አለብኝ» አለ ቆንሲሉ በንዴት

ትከሻውን ነቀነቀ

«እውነቱን ነው። ሁሉም ነገር ባልተለመደ መልኩ አሣሣቢ እየሆነ ነው። እነዚህ ቀሣውስት ሰላማቸውን ይዘው ቢቀመጡ ይሻላቸው ነበር። በሌ ኖይር ዱ ሮሉ የሚመራውና እኔ እስከማምነው ድረስ ትንሽም እንኳ ቢሆን ጥቅም ያለውን የራሣችንን ኤምባሲ ስኬት ስጋት ላይ እየጣሉት ነው»

«ምናልባት ከነርሱ ዘመቻ ጋር የኛንም ቀላቅለን አንድ ኤምባሲ ማድረግ ከቻልን?»

«ምነው! ጨርሶ የማሰቢያህን ነገር ጥለኸዋል?» አለው ቆንሲሉ።

የተቆጣበትን ምክንያት ሊያብራራ ሲል በጽህፈት ቤቱ በር ላይ በሚገባ የማይሰማ አነስተኛ ማንኳኳት ተደረገ። ፀሐፊው በሩን ለመክፈት ፈጥኖ ሄደና አንድ ትንሽ ጥቅል ይዞ ተመለሰ።

«ከእስክንድሪያ የመጣ ፖስታ ነው፣ ክቡር ሆይ»

ሙሴ ዴ ማይሊ፣ ደብዳቤውን ከሙሴ ማቹ እጅ በጉጉት ወሰደበት። ፖስታው የታሸገበትን ሲባጐ በሚንቀጠቀጡ ጣቶች በጠሰውና ይዘቱን ማንበብ ጀመረ። ከፖንቻርትሬይን የተፃፈ ምንም ነገር የለበትም። ይልቁንም ከፍሌሃውት አጭር ደብዳቤ አለ። ቆንስሉ፣ ፖስታውን ከፍቶ በመጣደፍ ሲያነበበው አሁንም አሁንም፣ ድምፅ ያስማል። ፖንሴ፣ ከንጉሡና ከአጃቢዎቻቸው ጋር የመገናኘቱን፣ ውኀቤቱንና የሚጠብቀውን ፍርድ ፍሌሀውት ተርኮለታል። ከዚህም በተጨማሪ በሚስጢር መጠበቅ ያለበት መሆኑን ጠቆም በማድረግ፣ የስድስቱን ጀስዊቶች መምጣትም ገልፆለታል።

«ርጉም!» አለ ቆንሲሉ «ሊሆንስ ይችላል? የመጨረሻዎቹን ነበር አይተናል ብለን ስናስብ የነበረው። ግን አሁንም ገና ሌሎች ስድስቶች ሊመጡ ነው»

የደብዳቤው ቀሪው ክፍል እጅግ ታላቅ ደስታ ስለ ሰጠው፣ ለሙሴ ማቹ ከፍ ባለ ድምፅ ማንበቡን ሊገታው አልቻለም።

«ይልቅስ ይህንን አዳምጥ... የጀስዊቶች ተልዕኮ ከቆንስላው ሙሉ በሙሉ ነፃ እንዲሆን ሚኒስትሩ አዝዘዋል። በተጨማሪም ለክብርነትዎ ያላቸውን አድናቆት የሚገልፁበት በቂ ቃል ማግኘት ያልቻሉት ሙሴ ዴ ፖንቻርትሬይን ለአገሪቱ የፖለቲካና የንግድ ግብ ሲባል የራሳችንን ኤምባሲ መላክ ብንችል ስላለው ጠቀሜታ ንጉሡን አሳምነዋል... እንዲህ ነው ትልቅ ሰው! እንዲህ ነው የወንድ ልጅ! ... ለዚህ ተልዕኮም፣ ሙሴ ሌ ኖይር ሮውሌ ተስማሚ መሆኑን ሚኒስትሩ ያረጋገጡ ይመስላል። ስለዚህም ሳይውል ሳያድር መሄድ ይችላል። የቀጣዩ ቆንሲል ሻንጣ፣ ይህን ጉዞ ለማሣካት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ለማሟላት አስፈላጊውን ገንዘብ ይይዛል። ፊርማ ፍሌሀውት»

ባርኔጣውን አራግፎ፣ ሰው ስራሽ ፀጉሩን አንጋድዶ ቆንሲሉ ወንበሩ ላይ ዘጭ አለ።

«አየህ ማቹ ... ሁሉ አድሮ ነገር ሁሉ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ተመለሰ። ኤምባሲ ... ተነስ ሂድና ሌ ኖይር ዱ ሮውሌን ፈልግልኝ»



«አሁን ቤት ውስጥ ያለ አይመስለኝም» አለ ሙሴ ማቹ

« ፈልገው»

መፈለጉ አስቸጋሪ ነገር አይደለም። ወጣቱ ዲፕሎማት ቁማር ወዳድ ስለሆነ ሁል ቀን ከሰዓት በኋላ ነጋዴ ባሏ የሞተባት ሴት ቤት በመሄድ ካርታ ይጫወታል። ዱ ሮውሌን ከማግኘቱ በፊት፣ ሰውዬው አንድ ዘመን ላይ ሀብታም ነበር። ሙሴ ማቹ ወጣቱን ዲፕሎማት ከቁማር ጨዋታው ላይ በመከራ አስነስቶ ቆንሲሉ ዘንድ አመጣው።

«ወዳጄ የምነግርህ መልካም ዜና አለኝ» አለ ቆንሲሉ ፍልቅልቅ እያለ

እውነት፣ እንኳንም ጥሩ ሆነ፣ ከምጫወትበትና አንድ ሺ ሊቭሬ በቀላሉ ሳሸንፍ ከምችልበት ቦታ ነው ያስጠራኝ ሲል ዱ ሮውሌ አሰበና በትህትና ጐንበስ አለ።

«እባክህ ተቀመጥ። ዜናው እንኳ ግራ የሚያጋባ ነው። ሚኒስትሩ አንተን በአቢሲኒያ አምባሳደራችን እንድትሆን ሹመውሃል»

በወጣቱ ዲፕሎማት ፊት ላይ አራት ወይም አምስት አይነት ስሜቶች ሲለዋወጡበት ውስጡ ግን ይጨፍር ነበር። እንደተሰመደው ምን እያሰበ እንደሆነ መናገር አስቸጋሪ ነው።

«እንደ እውነቱ ከሆነ ሲበዛ የሚያስደነግጥ ነው» አለ በፈገግታ።

ይህ ለአለባበሱና ለቁንጡ የሚጨነቅ ሽሙንሙን፣ ስሜቱ በጣም የተነካ ከመምሰሉ በስተቀር ሌላ የለም። በርግጥ ወደቆንስላው ለመድረስ ሲጣደፍ ያቋረጠው ጭቃማ ጐዳና በስተቀር በካልሲው ላይ እንኳ የሚታይ ነገር የለበትም።

«መቼ ነው ከዚህ የምነሣው?» ሲል ጠየቀ

«አ! እንዲህ ያለ ትጋት፤ እንዲህ ያለ ጥድፊያ ፤ ከፈለግህ ደስ ብሎህ ጥቂት ጊዜ ሰንብት። ገንዘብ የሚደርሰው በሚቀጥለው የገንዘብ መላኪያ ጊዜ ነው። ሁሉም ነገር በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርበታል» አለው ቆንሲሉ በደስታ፣አንዳችም እንከን የሌለበት መሆኑን በማሰብ፣

«ጥቂት ቀናት?»

«ከዚያም በላይ፣ ጥቂት ሣምንታት። ሁሉም ነገር በሰላም ከተከናወነ፣ ምናልባት እንዘልና ስድስት ሣምንት ወይም ስምንት ሣምንት»

«ድንቅ ነው! እስ ዱ ሮውሴ፣

«ዝም ብለን በጭፍን እንድትሄድ አንፈልግም ። ስላንተ ብዙ እናስባለን ውድ ወዳጄ። መንገዱን ለሚያደምቁ ጀብደኞች ትንሽ ልምምድ ማድረጉ ጥሩ ነው። ከዚህም በላይ እውነተኛው ኤምባሲ ሌሎች እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ያስፈልጉታል። ለምሣሌ የከበሩ ንፀበረከቶች ፣ ጠባቂዎች ... »

በጉዞው ጉዳይ ላይ ጥቂት ዝርዝር ነገሮችን ተነጋገሩ። ሰዓቱም በቆንስላው ውስጥ ቀደም ብሎ የሚቀርበው የእራት ጊዜ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሴ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ሁለቱ ብቻቸውን እንዲሆኑ በማለት ፀሐፊውን እንዲወጣ ጠየቀው።

«ከዚህ ከመነሣትህ በፊት ልታከናውናቸው ወይም ልታዘጋጃቸው የምትፈልጋቸውን ግላዊ ጉዳዮች የሉህም?» በማለት ከዱ ሮውሴ ጋር ብቻቸውን መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ቆንሲሉ ጠየቀ።

ይህ ወጣት ዲኘሎማት ይህን ወቅታዊ ሁኔታ በመጠቀም ለሴት ልጁ ያለውን ፍላጐት ይገልፅ ይሆናል ሲል ቆንሲሉ አስቦ ነበር። በጭውውታቸው ወቅት በእያንዳንዱ ዕድል ላይ ቆንሲሉ ሳይሣሣት በተዘዋዋሪ መንገድ ጉዳዩን ደጋግሞ ይጠቅስለት ነበር። ይሁን እንጂ፣ አንድም የዱ ሮውሴ አስተዳድግ ባልተለመደ አኳኋን ቁጥብ ስላደረገው (ቆንሲሉ እንደፈራው) ይሁን፣ ወይም ወጣቷ ሴት ልታስደስተው ባለመቻሏና ራሷን ማራኪ አድርጋ ባለማቅረቧ፣ አንዳችም ውጤት ሳያገኝበት ቀረ።

«የለም፣ ክቡር ሆይ፣ አላስብኩበትም» አለ ዱ ሮውሴ በፊቱ ላይ የመገረም ሁኔታ እየታየበት በእርጋታ።

ፈረሰኛው ሄክቶር ሌ ኖይሬ ዱ ሮውሴ፣ በወራሾች መካከል ሊከፋፈሉት የሚችሉት አንዳችም ነገር ሳይኖር፣ ለረዥም ዘመናትም ምንም ሣይኖራቸው፣ ነገር ግን የብኩርና ወራሽ ነው ተብሎ፣ ሥርዓተ ሕጉን በጥብቅ ሥራ ላይ ያዋለ የቤተሰቡ ሶስተኛ ልጅ ነበረ። ያደገውም፣ ሴንሊስ አጠገብ በሚገኘው በቤተሰቡ መኖሪያ ግንብ ውስጥ ቻል ተብሎ ነበር። በቤቱ ውስጥ ከግርግዳ ጫፍ እስከ ጥግ አስጠሊታና አስቀያሚ ሆኖ ያለው ሁሉ፣ ከቅድመ አያቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው። በዚያ ሕንፃ ግንብ ውስጥ ሊዘነጉ ከቶም የማይችሉት



የባህል መገለጫ መሣሪያዎች፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የነበሩት የከፍተኛ መደቦች ማዕረጐችና ስኑጥበቦች በሕፃኑ አዕምሮ ውስጥ ጥንድ መልክ ይዘው እንዲከዳችው አድርገውታል። ምንም እንኳ ለረዥም ጊዜ በፍቅር ያደገበት ቦታ ቢሆንም፣ እነዚህ ነገሮች ቤተሰቡን ጉዳት ላይ የጣሉ ናቸው። ወጣቱ ዱ ሮውሴ፣ እያንዳንዱን ጌጥና እያንዳንዱን የውበት መግለጫ ቁሣቁስ የማየት ልምድ አዳብሮ ነበር። በታላቅ ማስተር የተሠራን የሸራ ስዕል፣ በግድግዳ ላይ ለሻማ ወይም መብራት ማስቀመጫ ተብለው የሚሰሩ የነሐስ ጌጦች፣ ሥጋጃዎችን ፣ የፈረሰኛ ጉራዴዎችን ሁሉ እንደሸቀጥ በግድግዳ ወይም በሆነ ቁሣቁስ ላይ ሲቀመጡ፣ የግድግዳውን ወይም የእቃውን ስንጣቂ ለመደበቅ፣ የእይጥ ጉድጓዶችን ወይም የሻገቱ ቦታዎችን ከእይታ ለመሰወር ሲባል ነው። ገበሬዎች፣ ፈረሰኛው እያሉ ይጠሩታል። ምክንያቱም ከታላቁ ልጅ በስተቀር ከቤተሰቦቹ ሊሰጠው የሚችል ምንም ዓይነት የሹመት ስም የለም። ስለዚህ ፈረሰኛው፣ ከሕፃናት የገበሬ ልጆች ጋር እንደልቡ በነፃነት ለመንቀሣቀስና በየአደን ቦታው ሁሉ ለመሄድ ይፈቀድለት ነበር። ወጣቱ የመሣፍንት ዘር፣ እነዚህ ዋጋ የለሽ የሚባሉ ወጣቶች ከርሱ ይልቅ የተሻሉ መሆናቸውን አወቀ። በአጭር ጊዜ ውስጥም የሁለቱ ዓለሞች ጥበበኛ ሆነ። በውጭ ትንኮለኛ ፣ ጨካኝና አጭበርባሪ ነው። ይህ ደግሞ የመኖሪያው መሣሪያ ሆነለት። በመኖሪያው ግንብ ውስጥ ደግሞ ጥሩ የግርማ ሞገስና የትህትና ምሣሌ ሊሆን የሚችል ሆነ። በዚህም የተነሣ በዚያ ቤተሰብ ውስጥ ሊያገኝ ከሚገባው መብት ባለፈ ጥቂት ልብስና ምግብ ከሴቶች በበለጠ ይሰጠው ጀመረ። ከዚህም በላይ ገና ከልጅነቱ ለስላሳ ገላና ለሸቶ ዓለማዊ ፍቅር ስላዳበረ በሴቶች መዳበስንም ይሻ ነበር።

የግል አስተማሪ የነበረው ታላቅ ወንድሙ ብቻ ቢሆንም፣ እርሱ የወንድሙን ደብተሮችና ትምህርቶች በመገልበጥና በመኮረጅ በቂ ዕውቀት አግኝቶ ለመስፍኑ ዱክ ዴ ቬንደሜ፣ ፀሃፊያቸው ሆነ። ለዚህ ቦታ ብቁ መሆኑም በዚህ ትንሽ በር ወደ ሰፊው ዓለም ገባ። ነገር ግን በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲህ ያለ ዕውቅና ያስገኘለትን ባለሚልነት በቁማርና በአስረሽ ምችው ያበላሸው ጀመረ። እንዴት ባለ የማታለያና የማጭበርበር ዘዴ ተጠቅሞ እንደሆነ ባይታወቅም፣ ለማገልገልና ማንኛውንም መጥፎ ተግባር ለማከናወን በማመልከቱ፣ በፖለቲካ መሪው በሙሴ ቶርሲ ትዕዛዝ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጠረ። የዚህን ቅጥር ምስጢር አለማወቁ ግን ይመረጣል። ከዚህ በኋላ ሮዉሴ ለጥቂት ጊዜ በዲፕሎማሲው ሥራ ላይ ዓይኑን እንዲገልጥ ተደረገ። ባህሪውን ቢያሻሽል እንደሚጠቀምበት፣ በውጭ አገር የመኖር ዕድል ደግሞ ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት ላለው ጠንካራ ፍላጐት እንደሚረዳው አመነ።

በቆንሲል ማዕረግ ወደ ሮቤታ ተላከ። ሮቤታ ወደብ በመሆንዋ ከበቂ በላይ የንግድ እንቅስቃሴ ቢታይባትም በምስራቅ ሜዲተራኒያን ከሚገኙት ጣቢያዎች ሁሉ፣ አነስተኛ ክፍያ የሚደረግባት ነች። እርሱ ግን ደመወዙን በቀላሉ እጥፍ ማድረግ እንደሚችል ለራሱ ነገረው። ያሰበውንም ወዲያውኑ ጀመረ። እንደ ደረሰ ምንም ሳይቆይ፣ በእነክን የለሽ ጥሩ ስሙ ሳቢያ፣ ሚስትና ለመሥሪያ ቤቱ የሚሆን ሕንፃ ተሰጠው። ለማንኛውም ዓይነት ዓላማና ተግባር ሁለት ነገሮችን ታደለ።

የሚያጋጥሙ ነገሮችን ስርዓት ሳያጠብቁ ከማከናወን አስቀድሞ፣ በበቂ ሁኔታ ማሰብ ጠቃሚ ነው። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የተከበረ እኩያና የሚመጥን ሰው ስለሆነለት፣ ለሴት ልጁ የሚጠይቀው የጥሎሽ ጉዳይ ላይ ሊጣደፍ ይችላል። ዱ ሮውሌ ደግሞ ፈጥኖ ለመታሰር አይቸኩልም። በአሁኑ ሰዓት የርሱ ትልቁ ፍላጎት አቢሲኒያ ነች። ስለ አቢሲኒያ የሚያውቀው ትንሽ ቢሆንም፣ በተደጋጋሚ ወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዮችና ቅመማ ቅመም እንደሏት ተነግሯል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ባልተለመደ ከፍተኛ ጉጉት የፈረንሣይን ኢስት ኢንዲያ ካምፓኒ፣ ወደ አቢሲኒያ ለማስፋፋት እቅድ አውጥቷል። ይህን ያደረገው ዱ ሮውሌ ከርሱ ይልቅ ለሌላ ሰው ለማገልገል ይሄድብኝ ይሆናል ከሚል የተሣሣተ ሀሣብ በመነሣት ነው። ይህ ፈረሰኛ ግን ይህን የሚያደርግ አይደለም። ምክንያቱም እርሱ በበኩሉ የራሱን ሀብት ማግኘቱን እንጂ፣ ትክክለኛ ነገር በመስራት በራሱ ላይ መሰናክል እንዲፈጠርበት ሀሳቡም የለውም። ወዲያውም በውስጡ የተፈጠረውን ጥርጣሬ ሲገነዘብ፣ በርሱንቱ ኮራ። ይሁን እንጂ በራሱ መንገድም እንኳ ቢሆን፣ ይህ አስተዋይ ሰው ህልመኛ ነው። አገኘዋለሁ ብሎ ስለሚያስበው ሀብት የሚታወቅ ነገር የለም። ነገር ግን ልክ የመጀመሪያዎቹ እስፓኒያውያን አሜሪካ ውስጥ እንዳደረጉት ወይም ፈረንሣዊው ኘርኒስ፣ በማላሬኔ ደሴቶች ላይ እንዳደረገው የርሱ የግሉ የሆነ ግዛት ዘውድ ይመሠርታል። እርሱም፣ መጠነ ሰፊ በሆነ ሀብት ላይ ንጉስ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ደግሞ ማዳሞዜል ዴ ማይሌ ልትመጥነው ስለማትችል ፈራ። ስለዚህም የንግስታትን ልዕልቶች አለመ። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ፈጣን ውሣኔ ላይ ለመድረስ ምንም አልተቸገረም። መጀመሪያ ጉዞው ይደረግ። ከዚያ በኋላ ጥያቄው የሚቀጥል ከሆነ ጋብቻውን ማድረግ፣ ሲል ደመደመ።

ይሁን እንጂ ይህ እቅዱ፣ አሊስ በውስጡ ቀስቅሳበት የነበረውን ጠንካራ ስሜት ሊያሸንፍ አልቻለም። ከአንድ ሣምንት በኋላ እንዲህ ሲል ለራሱ ተናገረ። እርግጥ ነው፣ ጋብቻው



የሚማርከኝ አይደለም። ሆኖም ግን ከዚህች እርብትብት ሕፃን ጋር ለመደሰት ማንኛውንም ነገር እከፍላለሁ።

እንዳለመታደል ሆኖ አሁን እርሱም ያለው በቤተሰቦቹ የአገር ቤት ግንብ ውስጥ አይደለም።የቆንሲሉም ሴት ልጅ፣ እንዳፈቀደው ሊያንከባልላት እንደሚችላት የገበሬ ልጅ አይደለችም። አስቀድሞ በሕግ ሊያገባት ይገባል፣ ይህን ደግሞ አይፈልገውም። ቆንሲሉ በተዘዋዋሪ ያቀረበለትን ያልተነገረ ስጦታ እርሱም አድበስብሶ ለማለፍ ስላልፈለገ ከመውጣቱ በፊት ከልጅቷ ጋር ወሲባዊ ስሜትን የሚቀሰቅስና ምንም ዓይነት ቃል ኪዳን የሌለበት የጨዋታ ጊዜ የሚያገኝበትን ዘዴ ፈለገ። ሲከታተላት ቆይቶ፣ ቀስ በቀስ አንድ ዕቅድ ነደፈ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የርሱን ኢምባሲ መክፈት እንዳረጋገጠለት፣ ወጣቷ ወይዘሪት የሆነ ቦታ ላይ አንድ ምስጢራዊ ፍቅር እንዳዳበረች ድ ሮዉሌ ርግጠኛ ስለሆነ የታሰበውን ጋብቻ እንደርሱ ሁሉ፣ በእርስዋም ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ይሆናል። ለዚህ ባለጌ ሰው ይህ መፅናኛው ሆነለት። ለሌላ ሰው ያላትን ፍቅር፣ ተባባሪዬ ነው ብሎ ዱ ሮውሌ የመዘገበው ሙሴ ማቼ፣ ፈጥኖ ስሙን ነገረው። ይህ ለሌላ ሰው ያላት ፍቅር፣ እርሱ እንደተገነዘበው በጣም ጠንካራ ስለሆነ፣ ምናልባት የራሷን ስሜት እንድትከተል ያስገድዳት ይሆናል። እርሱ ደግሞ ልምድ ያለው ሰው በመሆኑ፣ ይህን ጉዳይ በብልሀት ወደራሱ አቅጣጫ መመለስ ይኖርበታል።

ከገበታው ላይ ብድግ ብላ ነፍሷን ስታ በመውደቋ፣ ከእይታ ከተሰወረች ከብዙ ቀናት በኋላ፣ አሊስ ተመልሣ ብቅ አለች። ዱ ሮውሌ፣ በሄደችበት ሁሉ በዓይኑ ይከተላታል። ሙሴ ዴ ማይሌ ምንም እንዳላስተዋለ እያስመሰለ ውስጡ በደስታ ሞላ። ልጁን ግን፣ ንፅህናዋን ባለመጠበቋና እንግዶቻቸውንም ባለማስተናገዷ መውቀሱን ተያያዘው። ታዲያ አሊስ የአባቷን ወቀሣ ተቀበለች? ወይስ ደግሞ ተፈጥሮአዊው ውበቷ ፣ ላላ ተደርጐ የተሠራው ፀጉርዋ፣ ተራው ልብስዋና ሆን ብላና ምክንያት ፈጥራ ታምሜአለሁ ከማለቷ በስተቀር፣ የተሟላው ጤንነትዋ፣ የደግኖችን ስሜት አላነሣሣም ይሆን? አይናፋርነትዋና ፍርሃትዋ እውነተኛውን የዱ ሮውሌን ስሜት አጋግሎ ምንኛ ዘንድ ለመድረስ እንደገፋፋው፣ ማለትም ይህን ባህርይ በወሲባዊ ግንኙነት ፍላጐት ለመለወጥ አላነሣሣውም?

ከቆንሲሉ ዕህፈት ቤት የኢምባሲ ሹመቱን ገና ተቀብሎ ሲወጣ፣ ፈረሰኛው፣ አሊስን በደረጃው ላይ ስትወርድ አያት። ወደ ሙዚቃው ክፍልም በፍጥነት ተከተላት። እርስዋ ግን በፒያኖው ላይ የነበረ አንድ የሙዚቃ ድርሰት ዕሑፍ በፍጥነት አነሣች።

ዱ ሮውሴ፣ ይህን ተግባር በማስመሰል እንኳ ቢሆን ሊያረጋግጥ አልቻለም። በቀጥታ ወደ ወጣቷ ዘንድ በመሄድ ፊት ለፊትዋ ሙሉ በሙሉ ተጋርጦ ተገተረ።

«ላንቺ የሚሆን መልካም ዜና አለኝ» አለ። የትንፋሹ ሙቀት ግንባሯ ላይ እስኪሰማት ድረስ አፉን ወደርስዋ በጣም አስጠግቶ

«ተነስቼ ልሄድ ነው»

«ግን ... እንዴት ያለ በጣም መጥፎ ዕድል ነው»

ከዚህ በፊት ፈፅሞ ተነጋግረው አያውቁም

«እውነትሽን ነው? ስለይሽ እያየሽ ሀዘን አይሰማሽም?»

አሊስ መልስ አልሰጠችም። በዚያ የዝምታ ቅፅበት ውስጥ ግን እጅግ ፈጣንና ጥልቅ የሆነ ለውጥ ተሰማት። ይህ ሰው፣ በሩ በጣም እሩቅ በሆነበት በዚህ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ እንዲህ ሲቀርባት፣ ፊቷ መቅላትና ትንፋሽዋ ቁርጥ፣ ቁርጥ፣ ቁርጥ ማለት ጀመረ። ወዲያውኑም እንደገና በምሽት ያደባ ሰው እንዳገኛት፣ እንደተከታተላት፣ ቁርጭምጭሚቷ እንደተሰበረባት፣ ውሾችም መጮህ እንደ ጀመሩ ታያት። በዚህ መሀል የጊዛው ነፃነትዋ ወዲያውኑ ትዝ ሲላት የሻምላው ብርታት፣ የፈርስዋ ኃይል፣ የሽጉጥዋ የፍንዳታ ድምፅ በአንድ ላይ ተሰማት። ብድግ አለችና ፊት ለፊት ተጋፈጠችው።

«ምን ትፈልጋለህ?» አለችው በሰማያዊዎቹ አይኖችዋ አጠንክራ እያየችው።

«እኔ በጭራሽ ሳልፈልግ ሌሎች እኔን ወክለው ይፈልጉልኛል። አንቺ ከምታስቢው የተለየ አላስብም፣ እንጋባም» አላት ዱ ሮውሴ

«ለመወሰን በመቻልህ በጣም የተደሰትክ ትመስላለህ»

ቀረባት። እርሷም ወደኋላ አላፈገፈገችም ሲቀርባት በውስጧ የተቀሰቀሰው ጥልቅ ስሜት የፍርሃት አልነበረም።

«እየወሰንኩ አይደለም፣ አውቃለሁ» አለ።

«ምንድነው የምታውቀው»

«ሣልነካ መቆየት እፈልጋለሁ። አንቺ ግን ሣትነኪ የቆየሽ አይደለሽም»

«እና ምን ይሁን?»

«እናማ ጋብቻ የሚሉትን ነገር እንርሣውና፣ እንዲሁ አንቺ እንደምታደርጊው፣ ፍቅራችን ይቀጥል። እናም ደግሞ እንራራቅ ...»

አይኖችዋ በፍርሃት አልተቁለጨለጉም



« . . . ለመደሰት» አላት ከንፈሮችዋን በከንፈሮቹ እየቆለፋቸው። እርስዋም ልታደርገው በምትችለው ፍጥነት አላመለጠችውም።

በኮሪደሩ በኩል የእግር ዱካ ይሰማል። አሊስ ረጋ ብላ የሙዚቃ መሣሪያው አጠገብ ተቀመጠች። ዱ ሮውሴ፣ ወንበር ይዞ በሌላኛው አነስተኛ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ጥግ ተቀመጠ። ማዳም ዱ ማይሌ፣ ሻር ብትን እያለች ስትገባ፣ ሁሉቱንም በፍቅር የጦፉ ወፎች ስትመለከታቸው፣ ሙሉ በሙሉ በባሏ ሀሣብ ውስጥ በመሆን ተደሰተች። እራት አብረዋት እንዲበሉም ወደገበታው ጋበዘቻቸው።

በገበታው ላይ ቆንሲሉ፣ ጨዋታው እንዳይቀዘቅዝ በማድረግ ሲያቆየው፣ በቅርቡ ከተፃፉት ጋዜጦች ላይ ያለውን ዜና ነገራቸው።

« ፖንሴን በተመለከተ» አለ ሰባለቤቱ፣ «መቼም በደንብ ታውቂዋለሽ፣ ያ መድሃኒት ቀማሚ . . . » ማቼና ዱ ሮውሴ በማንኪያቸው ላይ አሻግረው አሊስን ተመለከቷት

« . . . ይህ አስልቺ ሰው ንጉሱን ሊያያቸው ይፈልጋል። እንዳሰበውም አገኛቸው። ግርማዊነታቸው ግን እጅግ ብልህ ስለሆኑ በርሱ የሚታለሉ አልሆኑም። ታዲያ ይህ ቀን ያገኘው፣ ታሰሮ ፍርድ እየጠበቀ ነው»

በአሊስ በኩል አንዳችም እንቅስቃሴ የለም። አንዳችም የማጉረምረም ድምፅ፣ ወይም ሊያጋልጣት የሚችል በሀይል አየር የመሣብ ነገር የለባትም። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ አሊስ፣ ጊዛ ውስጥ፣ በወንዙ አጠገብ፣ በረገረጋሞቹ የሰንበሌጥ አጥሮች ስር ነበረች። በነዚያ ጥቂት ቀናት ያገኘችው ጥንካሬ በውስጧ ተደብቆ አለ። ከተመለሰችበት ጊዜ ጀምሮ የዚያን ያህል በታላቅ ነፃነት እንዳልኖረች ሁሉ፣ ነገሮች በትክክል እየተከናወኑ ናቸው። የታመመች ወይም የደነገጠች ትንሽ ልጃገረድ እንደምታደርገው ከዱ ሮውሴ አምልጣለች። ይህን ሁሉ ያደረግችው፣ ጆን ባፕቲስትን በመጠበቅና የወደፊቱን ሕይወታቸውን በአደጋ ላይ ላለመጣል ብላ ነበር። አሁን ግን መታሰሩን ሰማች። እንግዲህ ለመንቀሳቀስ ተራ ድርሻው የርስዋ ነው። ነፃነትዋን ወደ ሕግ መጣስ መለወጥ ያለባት እርስዋ ነች። ፍላጐትዋን ወደ ሃይል መለወጥ ያለባት እርስዋ ነች። ስለሆነም ከዚህ በኋላ አንዳችም ነገር ከራስዋም ይሁን ከሌሎች የምትፈራው ነገር አይኖርም። እናም ሁሉንም መሰናክል በጣጥሣ ታልፋለች።

ፈረሰኛው ዱ ሮውሴ፣ ትመጣለች ብሎ ይጠብቃት ስለነበረ፣ ከእኩለ ሌሊት ትንሽ አለፍ እንዳለ ተሾልኮ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባች።

# 10

ጆን ባፕቲስትን ለመመርመር ከምሁራን የተመረጡት ሰዎች፣ ማንግራይ ከገመቱበትና ከአዲሱ ዓመትም ጥቂት ቀደም ብለው ተሰበሰቡ። ቬርሳይለስ ውስጥ የዚህ እጅግ ልዩ የሆነ ታሪክ የሚነገርለት የውጭ አገር እስረኛ ቆይታ መራዘም፣ እየዋለ እያደር አስቸጋሪ መሆኑ ይታወቅ ጀመር። ጉዳዩ እስከመንግስት ምክር ቤት ድረስ ሲቀርብ ፣ንጉሡ ራሣቸው የተፋጠነ ርምጃ እንዲወሰድ አዝዘዋል። ፖንሴ፣ በርግጥም አታላይና አጭበርባሪ ከሆነ በፍጥነት ቢቀጣ ጥሩ ነው። ነገር ግን መልካም ሰው ሆኖ፣ በርግጥም የንጉሡ መልዕክተኛ ከሆነ እንደስድብ ሊቆጠር የሚችለውን ጉዳይ በጣም በአጭሩ ማድረጉ የተሻለ ነው።

ከሕዝብ መካከል የተመረጡ አራት ምሁራን ዳኞች አሉ። ሁለቱ የዩኒቨርሲቲ ሰዎች ሲሆኑ፣ ሁለቱ ደግሞ ከካህናት መካከል ናቸው። አራቱም ሰዎች በጥንታዊ ታሪክ፣ በቋንቋዎች ትምህርትና ጥናት የዕውቀት ዘርፍ የታወቁ ምሁራን ስለሆኑ ትምህርታቸውን ሊፈታተን የሚችል አንድም ሰው የለም።ምንም ይሁን ምን እነርሱ የሚሉት ታምኖ ተቀባይነትን ያገኛል። እነርሱ ብዙም አይናገሩም። ቢናገሩም በተቻለ መጠን ክስተር ባለ ድምፅ ነው። በሌላ መልክ፣ በነርሱ አስተያየትና ትምህርት ውስጥ ባልተካተተ ወይም በተለየ አስተያየትና ትምህርት ላይ መርዛቸውን ይተፋሉ።

እነዚህ ከሕዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች፣ ለፖንሴ ጉዳይ ጠላቶች ናቸው ማለት ጉዳዩን ማጣጣል ይሆናል። እውነተኛው ነጥብ፣ ፖንሴ፣ ንጉሡን ያስቀየማቸው መሆኑንና፣እነርሱ ደግሞ ንጉሡን ለማስደሰት መፈለጋቸው ነው። ከዚህም በላይ፣ ስለዚህ ተጓዥ ስለተባለው ሰው ያዳመጡት ፕሮፖጋንዳ፣ አስተሣሰባቸው በርሱ ላይ ተቃራኒ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ይሁን እንጂ በታዋቂነታቸውና በዝነኛነታቸው ምክንያት በቀላሉ ተፅዕኖአቸውን ያሣድራሉ።

በመጀመሪያው ችሎት ላይ ሲቀርብ፣ ጆን ባፕቲስት ንጉቶ ነበር። ማንግራይ፣ ከነጭ ጥጥ የተሠራውን ልብስ እንደ ትንኮሣ ሊቆጠርበት ስለሚችል፣ እንዳይለብስ መክረውት ነበር። በዚህም የተነሣ የተለመደውንና ተቀባይነት ያለውን የሱፍ ልብስ ለብሶ ሄደ። የፊት ለፊቱ ተቃውሞ በሶርቦኔ ውስጥ በሚገኝ አንድ ትልቅ ክፍል ውስጥ ተጀመረ። የክፍሉ ግድግዳ በተቀረፀና በወርቅ በተለበጠ እንጨት ያጌጠ ነው። ተመራጭ ዳኞች የተቀመጡት ከእንጨት



በተሠራ መድረክ ላይ ሲሆን፣ ፕሮፌሰሮች የመምህርነት መለያቸውን፣ ቀሳውስቱም የክህነት ካባቸውን ለብሰዋል። ተጠርጣሪው፣ ከፊት ለፊት ከመድረኩ በታች ተቀምጧል። ጠባቂዎቹ፣ በግራና በቀኝ በኩል ሆነው ይከታተሉታል። ከበስተኋላው ባሉት ሁለት ተርታ መቀመጫዎች ላይ፣ አነስተኛ ቁጥር ያለው የችሎት ታዳሚ ሲገኝ፣ ከነዚህ መካከል ዓይኑ እየሸሸው ያለውን ፍሌሀውትን፣ ከሶስት ሌሎች ጀስዊቶች ጋር ታጅበው አባ ኘላንቴይንንና ሌሎች እንግዶችን ጆን ባፕቲስት ተመለከተ። ክረምት በመሆኑ ምክንያት ክፍሉ ቀዝቃዛ ነበርና አድማጮች ሊያስላቸው ይቃጣል።

ሁሉንም ሰው ያስጨነቀው ሥርዓት፣ የፍርድ ቤት ያልሆነውን ሥራ የፍርድ ቤት ማስመሰል ነበር። ሂደቱ፣የአንድ ሰው እውቀት መገመቻ የባለሙያ ሥራ ነበር። ጥያቄው ጆን ባፕቲስት በርግጥ ወንጀል መፈፀሙን ለማረጋገጥ ሳይሆን፣ ጆን ባፕቲስት እስካሁኑ ተመልሻለሁ የሚለውን ጉዞ፣ በርግጥ አከናውኖታል ወይ የሚል ነው። እንደዚሁም ደግሞ ግልፅና ያልተደበላለቀ የእውነታ ምርመራው፣ ሌላ ገፅታ ቢኖረውስ የሚለው ነው። ጆን ባፕቲስት ሐሰተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ ይኸው ተመልክቶ በፍርድ እንዲወሰንበት ወደ ማረፊያ ቤት ይተላለፍና እዚያ ሰዎች እውነቱን እንዲናገሩ የሚደረግበት ሌላ ዘዴ አለ።

የምርመራው ሂደት እየተከናወነ እያለ አጠራጣሪ ነገሮች ግልፅ ነበሩ። የምርመራው አጣሪዎች «ተከሣሽ» ስሙን፣ ትውልዱንና ሥራውን «ፈቃደኛ ከሆነ» እንዲገልፅ ጠየቁት። ይሁን እንጂ የምርመራ አጣሪዎች ፕሬዚዳንት፣ ይህን ጥያቄ ባይመልስ አዳጋች እንደሚሆንበት በራሱ አነጋገር አስረዳው።

«ስሜ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ ይባላል። ወላጆቼን አላውቃቸውም። የተወለድኩት ግሬኖብል ውስጥ ሰኔ 17 ቀን 1672 ዓ.ም ላይ ነበር። ላለፉት ሦስት ዓመቶች ያህል ካይሮ ውስጥ እፅዋት በመሰብሰብ ስራ ላይ በመሠማራት ኖሬአለሁ»

ፕሬዚዳንቱ፣ ከፊት ለፊት ያሉትን ወረቀቶች ፈተሹቸው። የፍርድ ሂደቱ ፀሐፊ፣ በመድረኩ ጠርዝ ላይ በብዕሩ ሲጨረ።

«እንዲህ ከሆነ ወደ አቢሲኒያ ተጉዣለሁ ብለህ እየገለፅክ አይደለም እንዴ?»

«እየገለፅኩ ሣይሆን እያረጋገጥኩ ነው»

«እንዲህ ከመሰለ ጉዞ ተመልሰናል እያሉ በጉራ የሚናገሩ ጥቂት ክርስቲያኖች በዛሬው ዘመን እንዳሉ ታውቃለህ?»

«አውቃለሁ፤ እኔ ግን ጉራ አልናገርም» አለ ጆን ባፕቲስት

«ታዲያ እስከዚያ ድረስ የተጓዝከው ንጉሡ ፊት ለመቅረብ ነበራ::» አለ ሌላው በጣም ሽማግሌ ሆኖ ፊቱ የገረጣውና የአስቀያሚ እሮጌት የሚንቋቋ ድምፅ ያለው መምህር::

«ለዚህ ተልዕኮ ሀላፊነቱን የሰጡኝና ያዘዙኝ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገስት ራሳቸው ናቸው»

«እናውቃለን፣ እናውቃለን» ሲል ፕሬዚዳንቱ አንድ አብድ የሆነን ሰው በምናብ ከሚፈጠሩ የቅዠት ሀሳቦች ስቃይ የሚያፅናናው ይመስል:: «እስቲ ከዚህ አጠቃላይ ሀሳብ ወደሌላ ሀሳብ እንሸጋገር:: የምንጠይቅህን የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ፈቃደኛ ሁንልን:: አባ ዡሌት ሊጀምሩ ይፈልጋሉ ይመስለኛል»

«ጌታዬ» አሉ ከሌላው ጋር ሲታዩ ወጣት የሚመስሉ፤ አጥንታም ፊትና በአፋቸው ግራና ቀኝ ጥልቅ መስመር ያላቸው ቄስ «የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገስት የሚኖሩበት ከተማ ስሙ ማን ይባላል?»

«ጐንደር ይባላል፣ አባቴ»

«ፊደላቱን መጥራት ትችላለህ?»

ፖንሴ፣ የከተማውን ስም ፊደላት ለይቶ ጠራ:: በካህኑ ጥያቄ መሠረትም ስለከተማው መጠነኛ ገለፃ ሰጠ:: አራቱ ሰዎች፣ ፖንሴ የሚናገረውን አሁንም፣ አሁንም በዓይኖቻቸው እየተጠቃቀሱና በቃላቶቹ ላይ አሽሙራዊ አስተያየት እየተለዋወጡ በጥንቃቄ ያደምጣሉ::

«ስመሆኑ ዶን አልቫሬዝን ታውቀዋለህ?»

«የለም፣ የትም ቦታ አግኝቼው አላውቅም?» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ስሙን ለማስታወስ እየሞከረ

«ዶን አልቫሬዝ ሞቷል» አለ ፕሬዚዳንቱ በንቀት ፈገግታ «የተከበረ ጀስዊት፣ ታላቅና የሚታመን ምሁር ነበር:: የአቢሲኒያውያንን ሕይወትና አኗኗር በውስጣቸው ሆኖ ለአስር ዓመታት ስለቆየ፣ መረጃ ትቶልን አልፏል»

«ባነበበው በጣም እደሰት ነበር» አለ ፖንሴ::

«ብታነበው ትጠቀምበታለህ» አለው ቢጫው ምሁር «የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አንተ እንዳልከው ጐንደር ሳይሆን አክሱም መባሉንም ትማር ነበር»



«ከዚህም በተጨማሪ» ሲሉ ወጣቱ ካህን ቀጠሉ:: «በአገሪቱ ሌሎች ከተሞች አለመኖራቸውን፣ ሕዝቡ ሁሉ በየመሬቱ ላይ እያረሰ እንደሚኖርና ንጉሡ ራሳቸውም ከአንዱ ሰፈር ወደ ሌላው ሲጓዙ እንደሚኖሩም ታውቅ ነበር»

«ይቅርታ፣ ይህ የተገፈው የቅርብ ጊዜ መግለጫው አይደለም:: አገሪቱ መንደሮችና ከተሞች የሞሉባት ነች:: ጐንደር የተመሠረተችው ጀስዊቶች ከለቀቁ በኋላ ነው:: ምክንያቱም ንጉሠ ነገስቱ አንድ ቦታ የፀና ቤተመንግስት ስለፈለጉና አክሱምችን ስላላመኗቸው ነበር:: በመጀመሪያ ላይ እርግጥ ነው፣ የኛ የፈረንሣይ ነገስታት ይከተሉት የነበረውን ዓይነት ሥርዓት ነበራቸው:: በቀዳማዊ ፍራንሲስ ጊዜ ቤተመንግስቱ ከቦታ ቦታ ይዘዋወር ነበር:: በኋላ ፖሪስ ላይ ረጋ:: አሁን በመጨረሻም ቬርሣይለስ ሆነ:: ይህ የመጨረሻው ለውጥ በጣም በቅርብ ጊዜ የተከናወነ በመሆኑ ለምሣሌ ከአስር ዓመት በኋላ ወደ ፈረንሣይ የተመለሰ መልዕክተኛ የከተማውን ስም ላይጠቅስ ይችላል»

«ማብራሪያህ የሚያጓጓ ነው» አለ ምሁሩ «በኛ በራሳችን አገር ታሪክ ላይ ተመስርተህ ተጉገፎ እይቼዋለሁ የምትለውን አገር መልክ ለመገንባትና ለመቀባባት ካደረግከው ይልቅ እኛ የተሻለ እናሳምር ነበር»

ጆን ባፕቲስት መቃወም ጀመረ:: ፕሬዚዳንቱ አሰመግባባታቸውን አቋርጦ ሌላ ጥያቄ ጠየቀ:: ከዚህ አጭር ምልልስ፣ የምርመራው አጠቃላይ መንፈስና አዝማሚያ ምን እንደሚመስል መለኮት ይቻላል:: ዝርዝሩን አሁን ማስፈር ፋይዳ የለው:: ምክንያቱም ምርመራው ከሁለት ሰዓት በላይ ጊዜ ፈጅቷል::

ተጠርጣሪው፣ በጠባቂዎች ግራና ቀኝ ተከብቦ፣ ምሽት ላይ ወደቤት ተመለሰ:: ሣንግራይ፣ ትዕግስታቸው ተሟጦ ይጠብቁት ነበር:: ከሴ ቢዩ ኖይር የመጣው ትኩስ መጠጥ ጠረጴዛው ላይ ሆኖ እንፋሎቱን ያወጣል::

«እናስ?» አሉ አማካሪው::

«የምናገረውን አንዱንም ቃል አያምኑም:: እነርሱ የሚያውቁት ነገር ሁሉ፣ አቢሲኒያን ከስልሣ ዓመት በፊት ትተዋት ከወጡት ጀስዊቶች የተገኘ ነው:: በጀስዊቶች አገላለጽ ላይ ተመስርተው ስለሆነ በዚያች አገር ከንግስት ሣባ ጊዜ ጀምሮ አንዳችም የተለወጠ ነገር የለም:: እነዚህ የአዕምሮ ዘገምተኞች፣ ግማሽ ምዕተ አመት ምንም አይደለም በማለት ድርቅ ይላሉ:: በነርሱ መፃህፍት ውስጥ ያልተጠቀሰውን ነገር ሁሉ የፈጠራ ነው ይላሉ::»

ጆን ባፕቲስት የዕለቱን ውሎ ለወዳጁ እጥር ምጥን ባለ ሁኔታ ነገራቸው።

«ከዚህም በተጨማሪ የአቢሲኒያውያንን ሀይማኖት አውቀው እንደሆነም ጠየቁኝ። ስለዚህ ነገር የማውቀው እንደሌለኝ ነገርኳቸው። ይህን በተመለከተ አንደኛው በነዚህ ሕዝቦች ካህናት መሠረት የክርስቶስ ባህሪያት ስንት ነው? ሲል ጠየቀኝ። እዚያም በቀጥታ ይህን አይነት ጥያቄ ቀርቦልኝ እንደነበረ ነገርኳቸው። እንዲህ ከሆንና ከኛ ሀይማኖት ጋር እረጋግጠህ ከመለስክላቸው ይገድሉህ ነበር ሲል ፕሬዚዳንቱ ተቃወሙ። «እኔም፣ ቁርጥ ያለ መልስ አልሰጠኋቸውም። ይህም ምክንያት አለው። ምክንያቱም መልሱን አላውቀውም። በስነ መለኮት ትምህርት ላይ ዕውቀቴ አናሣ ስለሆነ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ ጠየቅኋቸው። ያዳነኝም ይኸው ማይምነቴ ነው። ሰል መለስኩለት»

«ጥሩ! እጅግ በጣም ጥሩ፣ አንበሣ ሆነህ ነው የተፋለምካቸው» አሉ ሣንግራይ

«ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ በሁሉም አቅጣጫ በተመረዘ ጦር እየተወጋ እንዳለ አንበሳ ማለት ነው። የሚገርምም፣ የሙራድን ስም የአቢሲኒያውያን ስም ሣይሆን የቱርካውያን ስም ነው የሚለውን መሠረት በማድረግ የርሱን ሕጋዊነትም ጠይቀውኛል። እውነት ነው፣ ሰውዬው አርመናዊ ነው። ታዲያ አርመናዊ ሆኖ ነው ንጉሡ ዲፕሎማታቸው እንዲሆን የሾሙት አለኝ፣አንደኛው አላዋቂ ቄስ። ለመሆኑ ነገስታት ከመቼ ወዲህ ነው ከጠላታቸው አገር አምባሣደር መምረጥ የጀመሩት? አለኝ። ሳስረዳው ሞከርኩ። የማቀርባቸውን ነጥቦች ሁሉ ማዳመጥ አልፈለገም»

«ተስፋ መቁረጥ የለብህም» አሉት ሣንግራይ። «የመከራከሪያ ነጥቦችህ ላይ በርታ። ባይስማማህም እንኳ የተሻለ ዳኝነት አግኝ። እኛም ከበስተጀርባ ስላንተ ጉዳይ እያወራን ነው። እንዲያውም እውነቱን ልንገርህና አንድ ጥሩ ዜና አግኝቻለሁ። የቻርትሬስ መስፍን፣ አንተ ከሶስት ቀናት በፊት የሰጠኸኝን የእጅ ፅሁፍህን ለማንበብ እሺ ብለዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሚኖራቸው አቋም በሚቀጥለው ሣምንት መጀመሪያ ላይ ይደርሰኛል። ሰውዬው፣ በንጉሡ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ አነስተኛ ቢሆንም አምነው ለሚነሱበት ጉዳይ የሕዝብን አስተያየት ለማሰባሰብ ከፍተኛ ችሎታ አላቸው»

«እንደሚመስለኝ በእኔ ጉዳይ ላይ ተቀጣጥሎ እየነደደ ያለው እሣት፣ የመጨረሻው ሃይሉ ላይ የደረሰ ይመስለኛል» አለ ጆን ባፕቲስት ምርር ብሎት።



የሚቀጥለው ዕለት እሁድ ነው። የምርመራው ጥያቄ ረቡዕ ይቀጥላል። ጆን ባፕቲስትን ለማየት፣ ሳንግራይ በአስር ሰዓት ላይ መጡ

«ለአንድ መንፈሣዊ ሰባኪ ሚና፣ ምንም ያህል መውደድ እንደሌለኝ ታውቃለህ» አሉት ዝቅ ባለ ድምፅ «እነዚህ ሁለት ጠባቂ መላዕክቶችህም ባንተ ላይ ሳያቋርጡ ሪፖርት እንደሚያደርጉ አይጠረጠርም። በርግጥ ከኔ ጋር በመኖርህ አንዳንድ ነገሮች አይስማሙህም። ነገር ግን ወደ ቤተክርስቲያን ባለመሄድ፣ ጥፋቶቹን ሁሉ ከዚያ ጋር አታያይዝ»

ጆን ባፕቲስት፣ ያስጠጉትን ተንከባካቢውን ምክር ተቀብሎ፣ አጃቢዎቹን መርቶ፣ ለአስራ አንዱ ሰዓት የፀሎት ስነ ሥርዓት ወደ ቅዱስ ኢዮስታቼ ቤተክርስቲያን ሄደ። ስለቅዳሴ ምንም የሚያውቀው ነገር ስለሌለው ማይም ነው። በጥቁር ሰማያዊው ባለቀስት ቅርፅ ጣሪያ ላይ በሚታየው የታህሣስ ወር ደካማ ብርሃን፣ እፎይታና መደመም አገኘ እንጂ የሚሰማውን መዝሙር እንኳ፣ረጋ ያለ ድምፅ አድርጐ ነበር የሚያስበው። የዚያን ወቅት የአየር ሁኔታው፣ የልጅነት ጊዜውን አስታወሰው። አላውቃትም የሚላትን፣ ነገር ግን ምስኪን የቤት ሠራተኛ የነበረችና ዲቃላ ልጅዋን እንዳታሳድግ፣ አሳዳሪዋ የከለከሏትን እናቱ፣ ትዝ አለችው። የወላጅ ጉዳዩ ሲነሣ ለመሆኑ የማን ዲቃላ ነበር?

ይህን ጨርሶውንም ሣያውቅ ይኖራል። በርግጥ አንድ ህፃን ቤተሰቡን ማወቅ ካልቻለ ዓይኖቹ ሁልጊዜም ወደ አንድ የታላላቅ ሰዎች ግንብ መመልከቱ አይቀርም። በዚህም የተነሣ ምንሴ፣ የአንድ ንጉስ ወይም መስፍን ዝርያ እንደሆነ እንጂ የማንም ምስኪን ልጅ እንዳልሆነ ያምናል። ነገር ግን በትክክል አባቱ ቤሣቤስቲን የሌለው፣ ጭራሽ ከሁሉም የባሰ መናጢ ድሃ ነው። ምናልባትም የክፉ ወንጀለኞችና ነፍሰ ገዳዮች መሪ ይሆናል። ምናልባትም የመጨረሻው ለጋስ ሰው ይሆናል። ወይም ማንኛውንም አደገኛ ተግባር ለማከናወን ፍርሃት የሚሉት ነገር ያልፈጠረበት ሰው ይሆናል። ምናልባትም ጨርሶ ሊሸነፍ የማይችል ሽፍታ የነበረ ሰው ይሆናል። የሰማዩ አባታችን ሆይ፣ አንተ ማነህ? እነዚህ ቃላት ለጆን ባፕቲስት በእውነቱ ምንም መልክና ቅርፅ አያሣዩትም። እንዲያው አንድ ልዩሰብአዊ ፍጡርን ብቻ ያሳስቡታል። እርሱ የሚታየው፣ አንድ ባህርያቱን በያንዳንዱ እንቅስቃሴው ላይ እንዳሻው መለወጥ የሚችል አይነት ሰው አድርጎ ነው። ሰማያት፣ ለአባት የለሽ ልጆች እና ናቸው። ወይም ደግሞ በአባት የለሽ ልጆች ከመጠን በላይ የተሞሉ ስለሆኑ፣ ለተጨማሪ ልጅ ቦታ የላቸውም።

ፖንሴ፣ ገና ከጨቅላነቱ ጀምሮ አስራ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ያሳደጉት በገጠር የሚኖሩት ሴት አያቱ ነበሩ:: አዛውንቷ ኑሯቸውን የሚደጉሙት ቅርጫት እየሠሩ ነበር:: በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት የሴቶች ስዕሎች ሁሉ ከርሱ የተዋሱትን ብርሃን መልሰው ያንፀባርቁበት ነበር:: ወንድ አምላክን በማምለክ ፈንታ ሴት ጣኦትን ቢያመልክ ኖሮ፣ ጳጳስ ሊሆን የሚችልበትን ሃይል ያገኝ ነበር:: ይህን በተመለከተ ከርሱ ሊሻል የሚችል ማንም እንዳልነበረ ትዝ ሲለው ለራሱ ፈገግ አለ::

የቅዳሴ ስነስርዓቱ ሲካሄድ እንደ አስፈላጊነቱ ጆን ባፕቲስት ይቀመጣል፣ ይቆማል፣ ወይም ይንበረከካል:: በያንዳንዱ የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ለውጥ፣ በቀዝቃዛው የድንጋይ ወለል ላይ ያረፉት ወንበሮች ይንዛጠጣሉ:: በቁርባን ጊዜ፣ በካህኑ እጠገብ ቆሞ የነበረው ዲያቆን አንዲት ትንሽ ቃጭል ሲያንቃጭል ድምፁ በቀዝቃዛው አየር ውስጥ የደወል ያህል ተስተጋባ:: ተንበርክኮ የነበረው ጆን ባፕቲስት፣ ከአፉ ውስጥ ጭጋግ የመሰለ እንፋሎት ሲወጣ ይመለከታል:: ጭንቅላቱን ትንሽ ቀና ሲያደርግ አንዱ ገጨው:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ማን መሆናቸውን እንኳ ሳታጣሩ በፊት ወዲያውኑ፣ ለዘለዓለም ሳትለወጡ እንድትኖሩ የሚፈልጉ ዓይነት ሰዎች ናቸው::

ዓይኖቹ አንድ ታላቅ ነገርን ያገኙ ይመስል ብልጥጥ ብለው ሣለ፣ ተንበርክኬአለሁ ሲል አሰበ:: አዎን! ወደ ኢትዮጵያ ስመጓዝ ይህን ኃላፊነት ከተቀበልኩበት ጊዜ ጀምሮ እንደተንበረከክሁ ነኝ:: ወይም ደግሞ ምናልባት አሊስን ካየኋት ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ፣ አንድ ነው:: ነፃ ሰው ነበርኩ:: በላዬ ላይ ስተጫነብኝ አንድም ባለስልጣን ተሸንፌ አላውቅም ነበር:: ቆንሲሉም ቢሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ሣየው፣ ወደኔ የመጣው እርሱ ነበር እንጂ፣ እኔ ወደርሱ አልሄድኩም:: በአንድ ዛፍ ስር አረፍ ብዬ እንዲያ ላደረግሁለት ሰው አሁን አቤቱታውን በማዳመጥ ውለታ ነበር የሠራሁለት:: እንዲያ ላደረግሁለት ሰው አሁን ተንበርክኬ እገኛለሁ::

ቄሱ ምልክት ሲሰጡ፣ ተንበርክኮ የነበረው ሁሉ ብድግ ብሎ ቆመ:: ከበስተኋላው ጠመንጃ አንጋች አጃቢዎቹም ብድግ ሲሉ መሣሪያቸው ሲንኳኳ፣ ጆን ባፕቲስት ሰማ:: እርሱም እንደሚመቻቸው ሆነላቸው::

ይኸው አሁን ደግሞ ተነስቼ ቆሜአለሁ:: ይህንንም ያደረግሁት ስለታዘዝኩ ነው:: ተቀመጥኩም፣ ቆምኩም ሁልጊዜም እንደተንበረከክሁ ነኝ:: ይህ ደግሞ ሽንፈት ነው:: ቆንሲሉ



ራርቶልኝ ሴት ልጁን ይሰጠኛል ብዬ እጠብቃለሁ:: ንጉሡም የመሣፍንት ዘር ብለው እንዲመርቁኝ እጠብቃለሁ:: እነዚህ ምሁራኖችም አስተያየታቸውን እንዲሰጡ እየጠበቅሁ ነኝ:: እነዚህ ደግሞ ሲወነጅሉኝ ነው:: ንጉሡም ሲረዱኝ የሚያደርጉት አንዳችም ነገር የለም:: ቆንሲሉም ሴት ልጁን ይከለክለኛል:: ይህ ሁሉ ሲሆን የምንበረከከው በሚያፈቅረኝ ሕዝብ ፊት ሳይሆን፣ በነዚህ እጅግ መጥፎ ባለሥልጣናት ፊት ነው:: ከዚህ ሁሉ የሚከፋው ግን፣ እኔ ይህን አለማመኔ ነው:: የመሣፍንት ወገን ተብሎ በአንድ ንጉስ ውዳሴ ማግኘት ሌሎችን ለመጫን ከሆነ፣ ይህን ክብር ነው ብዬ አልቀበለውም:: ይህም ሃይማኖት ከሌለው የተሻለ ነው ብዬ አላምንም:: ማንም ሰው እምነቱን በራሱ ፍላጐት ሊመራ መቻሉን ባምንም፣ ቤተክርስቲያን በሰዎች አስተሣሰብ ላይ፣ በተለይም በኔ ላይ ሥልጣንዋን እንድሽከም እንድታስገድደኝ ፈፅሞ አልቀበልም:: ይህም ሆኖ ግን ይኸው ተንበርክኬ እኖራለሁ::

ካህኑ ቡራኬ ሰጥተው ካሳረጉ በኋላ፣ ምዕመኑ እጆቹን በየኪሱ ውስጥ እየወሸቀ ተጣድፎ ወጣ:: ምእመናኑ ሲወጡ ግን በሃሣብ ጭልጥ ብሎ፣ በሁለት ታጣቂዎች ይጠበቅ የነበረውን ወጣት ተመለከቱት::

ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው፣ ቆንሲሉ ፊት ስለተንበረከክሁ ነው:: ያለጥርጥር ሁሉም ነገር ከዚሁ የሚመነጭ መሆኑ ግልፅ ነው:: ጥድቀቴ የጀመረው ያን ጊዜ ነው:: ነፃነቴን አሣልፌ የሰጠሁበትና የካድኩበት ጊዜ በትክክል ያን ጊዜ ነበር:: አባት፣የሴት ልጁን ፍላጐት ተቀብሎ፣ አይዞሽ ግፊበት ይላታል ብዬ ሳስብ ነበር:: አንዲት ሴት አፈቀርኩ ብዬ ለራሴ እያረጋገጥኩ እያለሁ፣ የርሷን መኖርና ነፃነትዋንም እየካድኩ እንቀሣቀሣለሁ:: የአሊስንና የኔን ሕይወት፣ በዚያ ክብር በሌለው አባቷ እጅ ውስጥ ጥዬዋለሁ:: ስለዚህም ተዋርጃለሁ:: ተንበርክኬአለሁ::

«የለም» አለ አንዱ ታጣቂ ወዲያውኑ

ጆን ባፕቲስት እንደማፈር ብሎ ይህን የመጨረሻ ቃል ጮክ ብሎ መናገሩን ተገነዘበ::

ወደ አቅሉ ከተመለሰ በኋላ «ኑ ጌቶቼ፣ ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊቃድ ፊት ሁልጊዜም ዝቅ ማለት አለበት» አላቸው::

ከዚያም ከክብር ተከታዮቹ ጋር እብስ አለ::

ይህ ሃሣቡ የሚያስከፋ ቢመስልም፣ በጆን ባፕቲስት ላይ ግን ከባድ ተፅዕኖ አሣደረበት:: እዚህ ውስጥ ከተዘራች ሀዋስ የሚበቅልና መላውን መፃኢ ተግባራቱን ሁሉ የሚቀይርበት አዲስ መንገድ፣ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ራሱን ያሣውቃል::

«ነፃነት ሲጠየቅ የሚችል ነገር ሳይሆን የሚወሰድ ነው» ሲል በዚያን ዕለት ምሽት ለሣንግሬይ ነግሯቸዋል።

ከሚቀጥለው ዕለት ጀምሮ ይህን ውሣኔውን ሊተገብረው ተዘጋጀ።

ከሦስት ቀናት በፊት ተከናውኖ የነበረ ሁኔታ ዛሬ ታላቅ ሆነ። ጆን ባፕቲስት፣ የምርመራ ሰዓቱ ደርሶበት እያለ እንኳ ሕመምተኞችን መጐብኘቱን ቀጥሏል። በርግጥም፣ ወጣ ሊያስብሉት የሚችሉት ሰበቦቹ እነዚህ ብቻ ናቸው። ዘበኞቹ፣ እርሱ ሕመምተኞቹን ለማከም እስከሚሄድበት ቤት መግቢያ ድረስ ይከተሉትና ወደ ውስጥ ግን ሳይገቡ ይቀራሉ። በአንዳንድ ሕመሞች ላይ የሚነገረው ነገርና እርሱም ሕመሞቹን አጣርቶ እንደክብደታቸው አስቸኳይ ሲሆኑበት ሙሴ ራኦል እንደ ፀሐፊ ያገለገለዋል። በተለይ በዚያ ዕለት፣ ማለትም ምርመራው ከመስማቱ ከሦስት ቀናት በፊት፣ ጆን ባፕቲስት የሚሠራውን ሁሉ፣ ሙሉ በሙሉ ጥንቃቄና እርቆ አስተዋይነት ባለው መልክ እንዲያከናውን የሚጠይቅ አስተያየት ያለበት ወረቀት፣ በሙሴ ራኦል በኩል ደረሰው። ሲናገርም የፊቱ ገፅታ አዲስ አመለካከት ነበረው።

ሐኪሙ ባለበት የጨለመ ቆሻሻ ጐጆ ውስጥ፣ አራት ሰዎች ይኖራሉ። ዕድሜዋን ለመለየት የምታስቸግር ሴት፣ ቡትት የለበሰችና ፀጉርዋ ያልተበጠረ፣ ከሁለት ሕፃናቶችዋና ከበሽተኛው ጋር በጥግ በኩል ተኮራምታ ትታያለች። የሰውዬው ስም ሞርቲየር ይባላል። በመጀመሪያ ላይ ከጋሪ ጋር ተጋጭቶ እንደነበረ ለመናገር ሞከረ። ይሁንና በቡቱ ላይ የደረሰበት ሁለት ቁስለት በቀስት ምክንያት መሆኑን ጆን ባፕቲስት ሲነግረው፣ ሰውዬውም እውነቱን ገለፀ። የመጣውም በሚዩክስ መግቢያ በኩል፣ ቀስተኞቹ ጠባቂዎች እያዩት በእህል ጭነት ላይ ተሣፍሮ ነው። ይሁን እንጂ ይህን ተደብቆ የገባ ሰው በሚመለከት፣ ጆን ባፕቲስት ለማንም ትንፍሽ እንደማይልበት አረጋገጠለት። ከዚያም በቁስሉ ላይ ሃይለኛ መድሃኒት አድርጐበት በፋሻ ጠቀለለለትና ሌላ ጠንካራ መድሃኒት ሰጠው። የሕመምተኛው አጥንቱ አልተነካም። የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር የቁስሉን ማመርቀዝ በቁጥጥር ስር ማድረግ ነው። በሚቀጥለው ዕለት ሕመምተኛው ከመጠን በላይ ቢያልበውም ግን እንደገና መመገብ ጀመረ።



# 11

ጆን ባፕቲስት፣ ከሕዝብ መካከል ከተመረጡ ዳኞች ጋር ክርክር በገጠመበት በሁለተኛው ችሎት ላይ ታዳሚዎች የነበሩ ሰዎች በሙሉ በመጀመሪያ ላይ ከነበራቸው አመለካከት በቅፅበት የተለየ ሃሣብ ያዙ። ከነዚህ ታዳሚዎች መካከል የተማሩ ናቸው የሚባሉት፣ ይህ ወደ አቢሲኒያ ተጉዟል የተባለው ሰው፣ ጥያቄዎቻቸውን ጥሩ አድርጐ አልመለሰውም በሚል በሙሉ ድምፅ ቢስማሙም፣ ተንገፍ ያቀረባቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች ብርታትና በዚህ ላይ እነርሱ ድክመቱን ሊያጋልጡበት የሚችሉበት ማስረጃ እንደሌላቸው ግንዛቤ ነበራቸው። በሁለቱ ችሎቶች መካከል የነበሩትን ቀናት በመጠቀም፣ ራሣቸውን ሰፋ ባሉ ጥናቶችና ትክክልም መጥፎም በሆኑ ጥያቄዎች ሲያዘጋጁ ሰነበቱ። ጆን ባፕቲስት በበኩሉ በቅርቡ በደረሰበት የግል ቁርጠኛ ውሣኔው ተደስቶ፣ ችሎቱ ወደሚሰማበት ቦታ በፈገግታ ደረሰ። ወደዚያ ያደረገው ጉዞም አስፈነደቀው። የታናሽና የታላቅ ልጆች የሆኑት ከፒካርዲ አካባቢ የመጡ ጠባቂዎቹ ጋር ያደረጋቸው ጭውውቶች ሁሉ አስደሣቾች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በሥራ ላይ ተረኛ ሲሆኑ አብረው እንዲመደቡ በማለት ከቅርብ አለቃቸው ጋር ፕሮግራማቸውን አስተካክለዋል።

ችሎቱ ሲሰየም እስከዛሬ ድረስ አፋቸውን ከፍተው በማያቁት ቁስ ጥያቄ ተጀመረ። ሰውዬው ግዙፍ፣በጣም ሩቅ ማየት የማይችሉ በመሆናቸው የፃፉትን ወረቀት እንኳ ለማንበብ አፍንጫቸው ሥር አቅርበው የሚይዙና ክፍሉን ሲቃኙት አይኖቻቸውን ጭጋግ መሠል ውሃ የሚሞላቸው ናቸው። ሰውዬው፣ አቢሲኒያውያን የሚመገቡትን የምግብ አይነት ማወቅ ስለፈለጉ ውስብስብነት ያላቸውን የቃላት ሃረጋት ትተው በጣም ቀላልና ተራ በሆነ መልክ ጠየቁት። ጆን ባፕቲስትም፣ ትህትና በተሞላበት ሳያስበው እንደመጣለት መልስ ሰጠ። ከዚህ በኋላ እነዚህ ምሁራን ሊያገኙ በቻሏቸው መረጃዎች ሁሉ ላይ ምን ያህል በትጋት ሲሰሩ እንደሰነበቱ የሚያመለክቱ ዝርዝር ጥያቄዎችን ማቅረብ ጀመሩ። አዳራሹ ውስጥ የነበረው ተመልካችና ተከታታይ፣ ደንዝዞት እያንቀላፋ ነበር። ይህን የመሰለው ድባብ፣ በንጉሡ ነገስቱ ግዛት የመዋቅር ሕግጋት ላይ በቀረበው ጥያቄ ሳቢያ እንደገና ተነቃቃ።

«በዚያ ያለው ሕግ፣ልክ እዚህ እንዳለው የብኩርና ወራሽነት ደንብ ነው። የንጉሡ ወንድሞች፣ የአጎት ወይም የአክስት ልጆች ምናልባት አመፅ ሊመሩ የሚችሉ ስለሚሆኑ፣

አስቀድሞውኑ አቅመ ቢስ እንዲሆኑ ይደረጋል። በሌሎች ቦታዎች እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች በወሲብ፣ በአልኮል መጠጦችና በአደንዛዥ ዕፆች ብላሾችና ሞራላቸው የወደቀ እንዲሆን አድርጉ ከመተው ይልቅ አቢሲኒያ ውስጥ በተራራ አምባ ላይ ያስሯቸዋል።» አለ ጆን ባፕቲስት

«እና ንጉሦች፣ ወንድሞቻቸውን በጠቀስካቸው የሞራል ውድቀት ውስጥ የሚጥሉበት ቦታ የት እንደሆነ ስለእግዚአብሔር ልትነግረን ትችላለህ?» ሲሉ ፕሬዝዳንቱ ጠየቁት።

የአርሲየንሱን መሰፍን በተዘዋዋሪ መንገድ መንካቱ በጣም ግልፅ ስለሆነ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ የማይጠይቅ ጥያቄ ነበረ። ጆን ባፕቲስት ግን ፈገግ አለ።

«እንዴት . . . በአዜቲኮች መካከል እንደሚሆን አስባለሁ»

እነዚህ ከህዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች በመደነጋገር እርስ በርሳቸው ተያዩ። ይህን የመሰለ ፀያፍ መገፋፋት በጭራሽ ደስ የማይል ቢሆንም፣ለነርሱ ግን ያልጠበቁት ነገር ነበር። እንዲህ ያለው ሁኔታ ከቀጠለ፣ ሣይንስና የቋንቋ ጥናት እየተቀየሩ ያሉበትን እውነታ ትተው፣በመንግስት ላይ መነጣጣትን የሚጋብዝ ጠንካራ የክስ ማስረጃ ለመፈለግ ሲነሱ ሆኑ። ስለዚህም ሁሉም ጥያቄዎች በፖሊስ ዳኝነት ሊቋጭ ስለሚችል ክትትል ያስፈልገዋል።

«ደስ የሚልህ ከሆነ ስለአቢሲኒያ ንጉሥ ጥቂት ተጨማሪ ጉዳዮችን ንገረን» አለው ተንኮለኛ ፈገግታ ያለው ከምሁራኑ አንዱ

«ስለ ንጉሡ ልናገር የሚገባኝን ብዙውን ነገር ተናግሬአለሁ። ከዚህ የበለጠ የማስታውሰው በእውነቱ የለኝም»

«ልብ ብለህ አስብበት። እንዴት ነው የሚኖሩት። በዙሪያቸው የሚደነቅ ነገር ምን ምን ይኖራል?»

«ሁሉንም በዝርዝር እንደነገርኳችሁ አምናለሁ። ዙፋኑን፣ ቤተመንግስቱን . . . አ ግን አንድ ታሪክ አለ። አሁን ትዝ አለኝ። በቤተመንግስቱ ውስጥ የንጉሡ ክፍል መስኮቶች በሁለት አቅጣጫ ወደ ግቢው ያሣያሉ። በአንደኛው ግቢ አንበሶች አሉበት»

«ይህንንማ ነግረኸናል»

«አዎ አውቃለሁ። ያልተገነዘባችሁት ከሁለተኛው ግቢ የማያቋርጥ ልቅሶ መሰማቱን ነው። ድምፁ በጭራሽ አይቋረጥም። አልፎ አልፎ፣ እንዲያውም ጉላ ስለሚል፣ ልቅሶና ዋይታ ለይታችሁ ትሰማላችሁ። ከዕለታት አንድ ቀን ይህን ድምፅ የሚያሰሙት በጦርነት ላይ



የተማረኩ እስረኞች ይሆኑ ወይ ብዬ ጠየቅሁ። የተነገረኝ መልስ ግን በተገላቢጦሽ፣ እነዚህ እሪታቸውን የሚያሰሙት በጥሩ ሁኔታ የሚከፈላቸውና ንጉሡ የሚወዷቸው አሽከሮች ናቸው ተባልኩ። እነዚህ ሰዎች የሚያሰሟቸው ድምፆች እንደ ንጉስ ነገስት ሁልጊዜም ሊሰማው ይገባዋል ብለው አቢሲኒያውያን የሚወዱትን የሙዚቃ ቅላፄ መያዝ ይኖርበታል። ያ ድምፅ፣ሕዝቡ በስቃይ ውስጥ ስለሆነ ንጉሡን ድረስልን፣ እርዳን እያሉ የሚጠሩበት ድምፅ ነው»

«እሺ፣ ታዲያ ከዚህ ምን ነገር ተገነዘብክ?» አሉት ፕሬዝዳንቱ

«እናንተ ለራሳችሁ ግንዛቤ ውሰዱ። ንጉሶች፣የሕዝባቸው መከራና ስቃይ ለጆሮአቸው እንዲደርስ መመከር አለባቸው ወይም የለባቸውም የማለቱ ጉዳይ የኔ ተግባር አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት።

«አሃ!» አሉ ፕሬዝዳንቱ፣ ባልደረባዎቻቸውን በደስታ እያማተሩ። «ፀሐፊው እነዚህን ነገሮች በሚገባ ከትቧቸዋል? ትክክል!»

ሰዎች ሊሰግዱለትና ጭራቸውንም ሊቆሉለት የሚገባቸውን ነገር የሚክድ ኩሩ ሰውን የማየት ያህል የክብር ባለሟሎችን ልብ የሚያሞቅ ነገር የለም።

ከዚህ በኋላ ሽንፈት በቅድሚያ የሚታወቅ ውጤት እንደሆነ በማመን፣ ሥልጣን ርህራሄ እንደሚያጣና የነርሱም ፍርሃት ትርጉም ባለው ምክንያት ሣቢያ መሆኑን ይመሰክታሉ።

«አ! አወቃለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት ወደ ችሎቱ የሂደት መንፈስ እየተመለሰ። «በንጉሡ ጉዳይ ላይ ከፍ ያለ ስሜት ስላላችሁ ሌላም ነገር ልጨምርላችሁ። በምሽት፣ ከንጉሡ ታላላቅ ሰዎች አንዱ ከመኝታ ክፍሉ በር ባሻገር በሚገኝ መስክ ላይ ይተኛል። ይህ ሰው በማግስቱ ጧት መሬቱን እየገረፈ ንጉሡን ከእንቅልፋቸው ይቀሰቅሣቸዋል? ታዲያ ጅራፉ ለምን ያስፈልጋል? ጅራፉማ የሚያስፈልግበት ምክንያት አለው። ንጉሡ አጠቃላይ ኀዛቸውን ይዘው በየዕለቱ በየጥሻው እየተጓዙ ስለሚሰፍሩ የዱር አውሬዎች፣ ሥጋ በል አውሬዎች፣ ብዙ ጊዜ ጅቦች በምሽት ተሾልከው ወደ ድንኳኖች ይደርሣሉ። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም እስከ ንጉሡ ድንኳን መግቢያ ይቀርባሉ። ስለዚህ ጅራፉን ማጮህ እንዲህ ያሉ አስፈሪ እራዊት በምሽት ወደርሣቸው አጠገብ እንዳይደርሱ ለማባረር ሲባል ነው። ንጉሡ፣ ቤተመንግስት መስርተውና ግንቦችን አንፀው በዚያው መኖርና ማደር ከጀመሩም በኋላ፣አሁንም በደን ውስጥ፣ዙሪያቸውን በአደገኛ አራዊት ተከብበው የሚኖሩ ይመስል ልምዱን ቀጥለውበት ይታያሉ። እውነቱን

ለመናገር፣ ክቡራን እንዲህ ያለው ድርጊት ጥሩ ምሣሌ ሊሆን ስለሚችል በሌሎች ቦታዎችስ ቢከረጅ ድንቅ አይመስላችሁም?»

«ጅቦችን ከቤተመንግስት ለማባረር ማለትህ ነው! ለምሣሌ ባለሟሎችን መግረፍ ማለትህ ነው? ያውም ንጉሡ ባሉበት ቦታ፣ ጎብቶኝ ይሆን ያልከው?» ሲሉ ፕሬዝዳንቱ ጠየቁት። «አዎን ልክ ነው። ፀሐፊ ይህንም ሃሣብ በፅሁፍ አስፍርልን እባክህ። ታሪኮችህ በጣም ድንቅ ናቸው። በነዚህ እፁብ ድንቅ ጉዳዮች ቀደም ብለህ እንድንደሰት አለማድረግህ ያሣዝናል»

ዳኞቹ አሁን ተዝናንተው በይፋ ፈገግ ይላሉ። አድማጋ ሕዝብ ፀጥ ብሏል።

«ምናልባት ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችንም ትነግረን ይሆን?» አሉት ፕሬዝዳንቱ በመጓጓት።

«አንድ የመጨረሻ ልንገራችሁ፣ በቆይታዬ ጊዜ በብዙ ግድያ ቦታዎች አገኝ ነበር። አሁን ልገልፅላችሁ የምወድደው አንድ የቅጣት ዓይነትን ነው። አንዱን እስረኛ አመጡትና ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በነጭ ጨርቅ ጠቀለሉት። ከዚያ በኋላ በትኩስ የፈላ የሰም ፈሣሽ ውስጥ ነከሩት። ሰሙ ከመድረቁ፣ ሰውዬው በተጠቀለለበት ጨርቅ ተመጠጠና በሕይወት ያለ ትልቅ ሟፍ ወይም ሻማ አደረጉት። ከዚያ በኋላ ልታደርጉት የምትችሉትን ያንን ነገር መለኮስ ብቻ ነው። እንደችቦ ይንቀለቀላል። የእሣቱ ነበልባል ድምፅ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ የሰውዬው እሪታ አይሰማም» አለ ፖንሴ ፈገግ ብሎ።

ዳኞቹ ፖንሴን በፍርሃት ተመለከቱት። የችሎት ፀሃፊው ብዕር በአየር ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ።

«ሁሉም ነገር ሲያበቃ፣ ጥቁር ቅርፅ ያለው ያረረ አስከሬን ይቀራል። ልባም ሆኖ ነገሩን መገንዘብ የሚገባው እዚህ ላይ ነው። አስከሬኑን ወደዚህና ወደዚያ እያገላበጣችሁ በጥንቃቄ ብትመለከቱት፣ አሁንም ነጭ ሆኖ ባለው ጨርቅ ስር የእስረኛው ያልፈሰሱ አይኖች ብዙውን ጊዜ በእንባዎቹ ተጠብቀው ታያላችሁ።»

ጆን ባፕቲስት ከመቀመጫው ላይ ብድግ አለ።

«የሚበቃችሁን ያህል ሰምታችኋል። በአሁኑ ሰዓት ከዚህ የበለጠ ልነግራችሁ የምችለው ይኖራል ብዬ አላስብም። ተስማሚ ነው በምትሉት መልክ ፍረዱኝ። በርግጥ አንድ ኑዛዜ አለኝ። ለኔም፣ እካሌን አጥፍቶ፣ በሚገባ ያገለገሉኝን ሁለቱን ዓይኖቼን ሊያተርፍልኝ



የሚችለውን ዓይነት ቅጣት እንዳገኝ ፍረዱብኝ። ስለንዝዬ የገለፅኳቸውን ታሪኮች ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ። ደህና ሁኑ ጌቶቼ» አለ።

ፀጥ ያለውና በረዶ የሆነው አየር፣ በጆን ባፕቲስት የጫማ ርምጃ ድምፅ ተሞላ። ሁለቱ የፒካርድ ሰዎችም ተከተሉት። ክፍሉን አቋርጠው ወደታላቁ በር የሚያደርሰውን የእንጨት ደረጃ ወጥተው እብስ አሉ።

«ወዳጄ ሆይ፣ የሰራኸው ስህተት ነበር። ሁሉንም ነገር በመልክ በመልኩ ለማድረግ እንችል ነበር። ከሁሉ በፊት የቻርትሬሱ መስፍን፣ አንተ ባሰባሰብካቸው ጉዳዮች ላይ ፍፁም ተመስጠው ነበር። በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው ያዘጋጇቸውን ድንቅ ጉዳዮች ሊያሣዩህ በመፈለግ፣ ሊያዩህም ወስነው ነበር። ይኸውልህ ይህንን አስር ሺህ ሊብሬ በመላክ ድርሰትህን ለማሣተም ይችሉ እንደሆን ጠይቀዋል። አየህ፣ ዳኞችን አጉል መገፋፋት እንዴት ስህተት እንደሆነስ ይታይሃል» አሉት ሣንግራይ

አማካሪው ከጆን ባፕቲስት ፊት ለፊት ቆመው ነበር። እንደተለመደው አዛውንቱ ምንም ዓይነት ሰው ሰራሽ ፀጉር አላጠለቁም። ገመምቡ ጭንቅላታቸው፣ አጭር ሆኖ ባልተበጠረው ሽበታቸው የተከበበ ነው። ክንዳቸውን ዘርግተው ሃኪሙን ጠበቅ አድርገው ያዙት።

«አ! አዎን ልክም ነህ፣ ልክም አይደለህም፣ እኔም ይህን በሚገባ አውቃለሁ። በሚገባ የማውቅልህ መሆኔን ለመግለፅ ይህንንም በመስፍኑ ወርቅ ላይ ጨምርበት፤ ከኔ የተሰጠህ ነው። ልለምንህ»

ትልቅ የሃር ከረጢት በጆን ባፕቲስት እጅ ውስጥ አስቀመጡ

«እናም ከእንግዲህ ጊዜ አታጥፋ። አንዳች ልዩ ስሜት ልትፈጥር ፈልገሃል። በዚህ ላይ እንዳትሞክረው ልመክርህ ባስብም፣ እዚህ ሁሉም ነገር የሚከናወነው በጥድፊያ ነው። ላ ሬይኒ ከዚህ በኋላ ዋናው ኃላፊ አይደለም። ከዚህ በኋላ እጅግ ሃይለኛው የፖሊሱ ክፍል ነው። ሌላው ቀርቶ፣ ዳኞቹ ውሣኔ ከማሣለፋቸው በፊት ንጉሡ ሁሉንም ነገር ያውቃሉ»

«ዛሬ ማታ የራሴን ትያትር መጫወት አስቤአለሁ።»

«ድንቅ፣ እንግዲያውስ እኔ ምን ልረዳህ እንደምችል ንገረኝ»

ጆን ባፕቲስት ነገራቸው::

«ያገር ያለህ!» አሉ አማካሪው:: «የቻርትሬሱ መስፍን ካንተ ጋር መገናኘት ባለመቻላቸው የሚያፅናናቸውም ነገር አይኖርም:: ሊጠይቁህ የሚፈልጉዋቸው ብዙ ነገሮች ነበሩዋቸው»

ከዚህ በኋላ፣ ሣንግራይ ዐይኖቻቸው በእንባ ተሞልተው፣ ወጣቱን ጓደኛቸውን አቀፉት::

«እኔም ልጄን ላጣው ነው» አሉ

«እያጡት አይደለም፣ እያዳኑት እንጂ»

«ይህም አንድ መፅናኛ ነው:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳ አንተ ከዳኞቹ ብታመልጥም፣በኔ ላይ የሚጣለው ቅጣት ግን ከባድ እንደሆነም እመን»

ይህ የስንብት ቃል ወጣቱን ሰው በጥልቀት ተሰማው:: ሙሴ ራኦል፣ ከአንድ ባላገር ጋር መጣና ሁለቱ ሰዎች ለመጨረሻ ጊዜ በሁለቱ ሃሣቦች ላይ የመወያየት መብታቸውን እንዲጠቀሙ በማሰብ አንድ ጠርሙስ ባርጋንዲ ለመግዛት ወጣ::

በሰባት ሰዓት ላይ፣ ጆን ባፕቲስት ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ:: ሁለቱ ፒካርዳውያን ፖሊሶች፣ በአክብሮት ክራሣቸው ዝቅ አሉለት:: ከግማሽ ሰዓት በኋላ በቤቱ ውስጥ የነበረው ሁሉ በእንቅልፍ ውስጥ ወደቀ::

ሣንግራይ የሚኖሩበት የከተማው ቤት ጓሮ፣ ወደ አንድ አነስተኛ የተነጠፈ ግቢ ያመራል:: በዚህ ግቢ ውስጥ ቢያንስ ስድስት ጫማ ያህል ርዝመት ባለው አጥር የተከበቡ የውሃ ጉድጓድና ሁለት የከብት ጋጣዎች አሉ:: የጆን ባፕቲስት የመኝታ ክፍል፣በተከፋፈለ የመስኮት መስተዋት ወደዚህ ወደቤቱ ጀርባ ያሣያል:: የእድል ይሁን የአጋጣሚ እንደሚሆን ሁሉ፣የጋጣው ጣሪያ ውቅር ስፊ አሸንዳ ያለው ሆኖ፣ ከዚህ መስኮት ስር ያልፋል:: ጆን ባፕቲስት የሚያሞቁ ልብሶቹን ለበሶ፣ በወፍራም ካቦርት ተጀቡኖ፣ በዚህ መስኮት በኩል በመውጣት የጋጣው ጣሪያ ላይ ሲረግጥ፣ የቅዱስ ኢዮስታቹ ቤተክርስቲያን ከምሽቱ አራት ሰዓት መሆኑን የሚያመለክተውን ደወል አሰማ:: ትክሻው ላይ ጆንያ ተሸክሟል:: በጣም በጥንቃቄ በጥቁሩ ድንጋይ ጠርዝ ተራምዶ ጣሪያው ላይ ወጣ:: ከዚያም በጉረቤቱ ግቢ ውስጥ ባለ የደቃቅ ጥራጊ ክምር ላይ ድምፅ ሳያሰማ ወረደ::



ጊዜው ጨለማና እጅግ ብርዳም ነበር:: ከዋክብት በጥቁሩ የሰማይ በረዶ ውስጥ ያበራሉ:: ጆን ባፕቲስት፣ ጥንቃቄ በተሞላው ሁኔታ አንድ ወይም ሁለት ርምጃ እንደተራመደ አንድ እጅ አፈፍ አደረገው::

«ሞርቲየር ነህ?» ሲል ደንግጦ ጠየቀው

«ሽሽ፣ ዝም ብለህ ተከተለኝ»

ኮንትሮባንዲስቱ፣ ሙሉ በሙሉ ባይድንም ትኩሣት የሚባል ነገር ጨርሶ የለበትም:: ቁስሉም ፀድቶ በሚገባ ከተበጀለት የመከላከያ ፋሻ ውስጥ እየዳነ ነው:: ለዚህ ሰው፣ ይህ የመጀመሪያው ቁስሉ አልነበረም:: አሁንም ድረስ የሚያነክስ ቢሆንም፣ ወደዚያ በሞኝነት ወደሚያከናውነው ተግባሩ መመለሱ አይቀርም:: ፖሪስን ደግሞ ከርሱ በተሻለ የሚያውቃትም የለም:: ከመተማመናቸው የተነሣ፣ ፖንሴ ሚስጥሩን ነገረው:: ሞርቲየር በበኩሉ፣ይህን ሕይወቱን ላተረፈለት ሰው ማንኛውንም ተግባር በመፈፀም ውለታ ለመክፈል በጣም ደስተኛ ነበር::

ጉዞቸውን በየጠመዝማዛው መንገድና አደባባይ እያደረጉ ሄዱ:: የክረምቱ ነፋስ በመንገድ ላይ የነበሩትን መብራቶች በሙሉ አጥፍቷቸዋል:: ነገር ግን ሞርቲየር፣ውሾች ያሉበትን ቦታና እንደመተላለፊያ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን የአደባባይ በሮች ጠንቅቆ ያውቃቸዋል:: የሌሊት ተረኛ ጠባቂዎች የሚዟዟሩባቸውን መንገዶች ስለሚያውቅ ከወሬ አቀባዮች በስተቀር የሚፈራው አንዳችም ነገር የለውም:: እርሱ አጥብቆ እንደሚያምነው፣ ቀደም ሲል ላጋጠመው አደጋ ተጠያቂዎቹ እነዚሁ ወሬ አቀባዮች ናቸው:: አንድ ባህረኛ ከፊት ለፊቱ የሚኖረውን ማዕበልና ሞገድ ለመለካት ባህሩን እንደሚመለከት ሁሉ ሞርቲየርም መንገዱን አሻግሮ ተመለከተው:: በግማሽ ሰዓት ውስጥ የቴምፕልን አውራ ጉዳና ደረሱ:: ይህ ጉዳና በየምስሶው ላይ በተንጠለጠሉ ትላልቅ የመዳብ መብራቶች ይንቦገቦጋል::

«ተጠንቀቅ፣ ከሃምሣ ያርድ ርቀት ላይ የዘብ ስንተራያ አለ:: የጨለማውን ጠርዝ ይዘህ ተጓዝ:: አንዳች የሆነ እሪታ ብታዳምጥ በሩጫ ማምለጥ ይኖርብሃል::» ሲል ሞርቲየር ሹክ አለው::

ሞርቲየር፣አስቀድሞ በሚገባ መብራት ባለው ሰፊ ጉዳና ላይ እያነከሰ ተሻገረ:: ወዲያውኑ በጥላዎች ውስጥ ገብቶ እንደተሰወረ፣ ጆን ባፕቲስትም እንዲሁ መንገዱን በፍጥነት ዘሎ በማቋረጥ ዱካው ሳይሰማ ደረሰበት:: ራቅ ባለው ጉን ረገፍ ዛፎችና ጥቂት ቤቶች

ያሉበት የመናፈሻ ስፍራ አለ። ከሆነ አጠር ያለ አጥር በስተጀርባ ይጮሁ የነበሩትን የጥበቃ ተረኞችን ውሾች፣ በጥንቃቄ አለፏቸው። ወዲያውኑ ይህን አጥር አልፈው ወደ ቻርኔ በመውጣት ባዶ፣ ነፃና ገላጣ በሆነው አካባቢ ውስጥ ገቡ። ጉዟቸውን በረባዳው የእግር መንገድ ላይ በማድረግ በደን ውስጥ በማቆራረጥ ግራና ቀኙን የደረቁ ቅጠሎች የተንዘገዘገባትን ትንሽ ምንጭ ዘልለው አብስ አሉ።

እስከአሁን ድረስ ጨረቃዋ ስላልወጣች ከሰማይ የሚመጣ ምንም ብርሃን አልነበረም። በአንድ ሰፊ መንገድ ውስጥ ገብተው ወደ አንድ አጥር ዘንድ ሲቃረቡ፣ በእንቅልፍ ላይ ያለች ላም አልፎ አልፎ ስትጮህ ይሰማሉ። የቻርኔን መንደር ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ወደ ቀኝ እጥፍ አሉ። እርጥበት አዘል ከሆነው አየርና ከሚንኮሻኮሸው የቅጠላቅጠል ድምፅ በመነሣት በደን ውስጥ እየተጓዙ መሆናቸውን፣ ጆን ባፕቲስት አወቀ። አንድ መስክ ላይ ፈረስ ሲያናፋ ተሰማቸው። ሞርቲየር ምልክት ሲያሰማ በጭለማው ውስጥ ያለ ሌላ ሰው በፉጨት መልስ ሰጠው።

«አንተ ወስላታ፣ አንተነህ እንዴ?»

«ሌላ ማን ይሆናል የኔ ወርበላ?»

የሰውዬው፣ ስልል ያለችና ቀጭን፣የምትንቀጠቀጥ፣ምናልባትም ሽማግሌ ማይሆን እንደማይቀር የምታጋልጠው ድምፁ፣ በቅርብ ካለው ጨለማ ውስጥ ትሰማለች።

«አውሬውንስ አምጥተኸዋል?»

«አውሬስ አንተው ነህ፣ ጆሮ የለህም እንዴ? እጅህን ወደዚህ አቅርብ። ይህ የምትዳስሰው ቆቅ ይመስልሃል እንዴ?»

«አንተ ቀልደኛ ሽማግሌ። ልጓሙን አቀብለኝ። ዶክተር፣ ይኸውልህ። ፈረሱ ተጭኖልሃል። መሄድ ትችላለህ።»

ጆን ባፕቲስት፣ የቆዳ ርካቡን በዳሰሳ ካስተካከለው በኋላ ኮርቻው ላይ ዘልሎ ወጣ። ሞርቲየር፣ ዱብ አግኝቶ ፈረሱ ላይ ሊወጣ እንዲችል በማለት መንገዱን ይዞ ወደፊት ሄድ አለ። ኮንትሮባንዲስቱ፣ ምንም ዓይነት ገንዘብ ላለመቀበል አሻፈረኝ ቢልም፣ ጆን ባፕቲስት የሙጢኝ ሳይለው፣ ነገር ግን ሰውዬው ሳያስተውል አንድ ገንዘብ ያለበት ቦርሣ በኮቱ ውስጥ በዘግታ ጣል አደረገለት።



ድምፅ ሳይለዋወጡ ተጨባበጡ። ከዚያም ከልብ በመነጨ ስሜት ተመሰጋገኑ። ፖንሴ፣ የፈረሱን ጉን በእርካቡ ኮረኮረውና መንገዱ ውስጥ ገባ። በመጀመሪያው መስቀልኛ መንገድ ላይ ሲደርስ፣ ከቀደሞው ውሣኔው ፈፅሞ ላለማፈንገጥ ሲል ወደ ደቡብ ታጠፈ። ገና ጉዞውን እንደጀመረ እጅግ ጨለማ ስለነበረ ግልቢያውን ቀዝቀዝ ሊያደርግ ዳድቶት ነበር። በኋላ ግን ብርማዋ ጨረቃ በሰማይ ላይ ብቅ ስትል፣ ከፊት ለፊቱ ያለውን የመሬት አቀማመጥ ልታሣየው በቂ ሃይል ነበራት። ፈረሱ፣ሬጋ ብሎ ደስ የሚያሰኝ ግልቢያ ያደርጋል። ጆን ባፕቲስት፣ ከዚህ በፊት እንዲህ ለእስር የተቃረበበት ጊዜ ፈፅሞ አልነበረውም። አሁን ግን የነገስታት ሁሉ ሃያል የሆኑትን ንጉሥ አሻፈረኝ ስላለ ይፈልጉታል፣ ያሣድዱታል። በአንፃሩ እርሱ ደግሞ በዛፍ ቅርንጫፍ ቢገረፍና ዓይኖቹም በእንባ ድረት ቢሞሉም፣ በዚህ ቀዝቃዛ ምሽት የተሰማውን ነፃነትና በራስ መተማመን ስሜት መቼውንም ቢሆን ተሰምቶት አያውቅም ነበር።

# 5

# የቁጥቋጦው ሠደድ

# 1

አሊስን ከምንም ነገር በላይ የሚያሳስባት፣ የርስዋ የራስዋ ውስጣዊ ንፅህና፣ የስሜቶችዋ መልካም ስምምነትና ሙሉ በሙሉና በታማኝነት ለማፍቀር የመቻልዋ ጉዳይ ነበር:: እነዚህን ግላዊ ስጦታዎችዋን መጠበቅ በራስዋ ፈቃድ ላይ ብቻ የተወሰኑ ናቸው:: አንዳች አጋጣሚ በሰውነቷ ላይ ቢደርስ እንደማይበላሽባት ስታስብ በውስጧ ጤነኛ ትምክህት ተሰማት:: በልቧም ውስጥ እውነተኛ ልጃገረድነትዋ ሃያልና ጠንካራ ሆኖ ቆየ::

ሕብረተሰብ፣ የራሱን ወጣት ትውልድ ነፃነት በመፍራት፣የሚያከብረውን ቁሣዊ ድንግልና ጠብቃ በማቆየት ራስዋን ባሪያ የምታደርግበት አስፈላጊነት የለም:: በአንፃሩ፣ እስከዛሬ ድረስ ጠብቃው ያቆየችውን ቅድስናዋን በረገኘርሞቹ የመሰንከያ ቀሚሰችና ቀፈትን መሰብሰቢያ ባለብረት ቀበቶ ሙታንታዎችን መልበስ፣ በእንግዳ ሰዎች ፊት አይኖችዋን መስበርና ሲመሽ እንደደነገጠች የምትታደን እንስሳ እንድትሮጥ የሚያደርጋት ያንን አሰቂኝ ነገር ለመከላከል ነው፣ ስትል በስጨት ብላ አሰበች::

አሁን ግን አግርጠኛነትን፣ ብርታትንና ክህሎትን፣ ጊዛ ውስጥ ተምራለች:: ስለዚህም ይህንን የሚያስራትን ገመድ ወዲያ ጥላ፣ራስዋን ነፃ ማድረግ ይኖርባታል:: በዚህ ረገድ፣ ጆን ባፕቲስት ያለ አንዳች ማወላወል መንገዱን እንዲቀድድላት ትመርጥ ነበር:: ይሁንና አሁን የሚቻል አይደለም:: ከዚህ ይልቅ በተቃራኒው፣ እርሱን ሳይዘገይ ነፃ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ለማከናወን ያለ የሌለ ሃይሏንና ጉልበትዋን ሁሉ ለማዋል እንድትችል፣ ያገኘችውን ማንኛ ውንም ወንድ ልትጠቀም ፈለገች:: ፈረሰኛው ሮውሌ፣ እንደተማረከችለትና የግሉም ሊያደርጋት እንደሚችል አምኗል:: እርሷ እራስዋ የቋመጠችለትን ጉዳይም፣ ለመፈፀም እያዘነ ፈቀደ:: ምንም እንኳ የረዥም ጊዜ ልምድ ቢኖረውም ይህ ቅንዝረኛ ፈራ:: ይህ የሆነው ምናልባት አብሯት ባሳለፈው ምሽት፣ የአሊስ ቅዝቅዝ ማለትና የውሣኔዋ ሁኔታ የፈጠረበት ይሆናል:: ለማንኛውም የዚህን ግጥሚያ አስፈሪ ውጤት ለማሳካት ፈረሠኛው ነፃ ሆኖ ሲያስብ ቆየ::

በመጀመሪያ ደረጃ ተፈጥሮአዊ ሁለንተናዋን ከወሲባዊ መስህብ፣ ከትልቅነት፣ ከጋለ ስሜትና ከነፃነት ጋር አደበላልቃ ማከናወን በቻለችው በዚህች ውብና ሃፍረተቢስ ልጃገረድ

ፍቅር ተማረከ። ሁሉንም ነገር ቀጥሎ ደግሞ፣ድል አድራጊነቱ፣ የሆኑ መብቶች የሰጡት መስሎት አመነ። ለምሳሌ ከርስዋ ጋር እንዳሻው ለመዳራት መብት እንዳለው አመነ። ይሁን እንጂ ቆየት ብሎ በርስዋ የምህረት ፈቃድ ሥር መሆኑን ተገነዘበ። በሁለተኛው ዕለት ምሽት አሣፍራ መለሰችው። መፍራት የጀመረውም ያን ጊዜ ነበር። ይህችን ደፋር ሴት እንዲህ ያንቃቃት ምን እንደነበረ ሊገባው አልቻለም። ራሱን ጠላ። ልጅቱም ምን ሊከተል እንደሚችል ሳታስብ የምትንቀሣቀስ ችኩል፣ በቀላሉ የምትረካ፣ ያልተገራ ተግባር የምታከናውን፣ ሌላው ቀርቶ ግንኙነታቸውን ይፋ የምታደርግ አድርጐ ገመታት። ለደስታ የነበረውን ፍላጐት ከተዘጋው መስመር እንዲወጣ እንዳደረገውም ተረዳ። ምንም እንኳ የከፋ ነገር ይመጣል ብሎ ቢፈራም፣ አሊስ ያሳደረችበት ስሜት ጠንካራ ስለነበረ ፀፀት አልገባውም። በሚቀጥሉት ምሽቶችም እሺ እንድትለው ለመናት። እርስዋም ቅዝቃዝ ባለው ስሜትዋ እምቢታዋን ገለፀችለት። እሺ እንድትለው እየተለማመጣት፣ በፍላጐት ሰክሮ፣ በመጀመሪያው ግንኙነታቸው ላይ አጭር ጊዜ የፈቀደችለትን ዳግመኛ፣ለዘለዓለም ላይቀምሰውና እስከ ዘለዓለም እንደቋመጠ መቅረቱን እያሰበ በረንዳው ደረጃ ላይ ብቻውን ቀረ።

ሁሉንም ታሪክ ለፍራንቾይዝ እንዳለ ተናዘዘችላት። በችሎታዋ የዕዳት ሠራተኛ የሆነችውም ሴት፣ ያጋጠማትን ነገር ሁሉ ደምስሳ አጠፋችላት። ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ተደርጐ ተነግሯት ቢሆን ኖሮ፣ ፍራንቾይዝ ምናልባት ጭራሽም እንዳትሞክረው በማለት ታግዳት ነበር። አሁን ግን ለማልቀስና ለማዝነት እጅግ በጣም የዘገየ ነው። አሊስ ከዚህ በኋላ ዕቅዷን ለፍራንቾይዝ በዝርዝር አስረዳቻት። ፍራንቾይዝም፣ አንድ ሺህ አንድ መቃወሚያ ነጥቦችን አነሣችባት። ምክንያቱም ወጣቷ ሴት ሊያጋጥሟትና ልትጋፈጣቸው የምትችላቸው ስፍር ቁጥር የሌላቸው መሰናክሎች በመንገዷ ላይ እንዳሉ ነግራታለች። በመጨረሻ ግን እያጉመተመተችም ቢሆን፣ አሊስ የነፃነትዋን ጕዳና ለመምረጥ የነበራትን ጥንካሬና ትጋት፣ሠራተኛዋ አደነቀች። በክርክሩ ከተሸነፈችና ሃሣቡንም ከተቀበለች በኋላ ወጣቷን ሴት በሁሉም መንገድ ለመርዳት ቃል ገባችላት።

በአራተኛው ቀን ማታ፣ ዱ ሮውሌ፣ የማዳምዜል ዴ ማይሊን በር እንደ ድመት ወይም እንደ ውሻ ሊቧጥጥ መጣ። ሊከተለው የሚችለውን አስፈሪ ቅሌት እያሰበ፣ በሩን ቢገፋው መሸጐሪያው ስላልተቆለፈ፣ ዱ ሮውሌ በጥፊ የተመታ ያህል ደነዘዘ። በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ ዘለቀ። አሊስ፣ ፊት ለፊቱ ተነተረች። የሚጠለቅ ረዥም ሸሚዝ፣ ከጥጥ የተሠራ ከጉልበት እስከ ዳሌ የሚደርስ ሱሪ፣ የቦት ጫማዎች፣ ጊዛ ውስጥ ፈረስ ስትለማመድ ትጠቀምበት



የነበረውን ልብስ ለብሣለች። እጅግ የተቆጣች ትመስል ስለነበረ ፈረሰኛው እጅግ ቢቋምጥም ሊስማት ግን ወኔ አልነበረውም።

«በሩን ልትቆልፈው ብትችል እባክህ?» አለችው

ታዘዛት። በዙ ገዜ ተቀምጣ ምኞቷንና ሕልሟን ወደምታሰላስልበት፣ ከቀጭኑ የጣውላ አግዳሚ ፊት ለፊት ያለውን ወንበር አመለከተችው። ወንበሩ እንክትክት የሚል ስለሚመስል፣ ዱ ሮውሌ በጥንቃቄ ተቀመጠበት።

«ጌታዬ፣ በየምሽቱ ወደ ክፍሌ በመምጣት የምታገኘው ምንም ነገር የለም። ዳግመኛ አልከፍትልህም። ደግሞም አንድ ሰው ምናልባት ሊያይህ ይችላል» አለችው

«ግን ምን አጠፋሁ?» ሲል በጥሞና ጠየቃት። «ምን አድርጌ አስቀየምኩሽ?»

«ጉዳዩካንተ ጋር አይደለም። ላረጋግጥልህ የምችለው፣ አንተ የተሰጠህን ተግባር በብቃት መግለፅ ችለሃል።»

«በብቃት? ተግባር! ወይኔ፣ ምነው ትቀልጅብኛለሽ» አለ፣ ዱ ሮውሌ በቀና መንፈስ፣ እዝን ብሎ

«በጭራሽ። ጥያቄው ነገሮችን እንዳሉ ወይም እንደነበሩ አድርጐ የማየት ጉዳይ ነው። አንተ ልታከናውነው የሚገባህ ሥራ አለህ። ይህንን ደግሞ በቅልጥፍና አከናውነኸዋል። ለዚህም አመሰግንሃለሁ።»

«ማዳምዜል፣ እያዋረድሽኝ ነው»

ሕይወቱን ሙሉ ውርደት የሚባለው ነገር ጫፉን ደርሶበት የማያውቀው ዱ ሮውሌ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ሊተኛት ባቀዳት ሴት ሃይል ስር ሙሉ በሙሉ መውደቁን አወቀ። የተሻለና መልካም ከሆነ፣ ከእግሯ ስር ወድቆ ሊለምናት ተዘጋጅቶ ነበር። ነገር ግን ራሱን ከዚህ ባለፈ ላለማራከስ ሞከረ። የመጀናን ትዕቢቷ የሚያመለክተው፣ እርሷም ከርሱ ትንሽ ክብር መፈለጓን ነው።

«ከፈለግህ አመዛዝነው። ያንተና የኔ ፍላጐቶች ፍፁም የተለያዩ ናቸው። አንተ ነውርን ስትሸሽ፣ እኔ እፈልገዋለሁ»

ስሙን ልታጠፋበት በርግጠኝነት የተዘጋጀች መስሎት፣ ዱ ሮውሌ በጣም ደነገጠ።

«ይሁን እንጂ አትስጋ። እኔ የራሴን ስምና ክብር ለማጉደፍ የምጥረውን ያህል፣ ያንተን የተከበረ ስምና ዝና ለመጠበቅ በቁርጠኛነት ወስኛለሁ። ስለዚህ ስጋት አይግባህ»

ሁኔታው ሁሉ፣ ዱ ሮውሴን አልገባህ አለው። ሊገባው የቻለው ነገር ቢኖር፣ ይህች ሴት፣ በሆነ ዘዴ ተስገብግባ ከተመገበችው በኋላ የወንድ ስሜቱ መጥፋቱን ነው።

«እባክሽ ግልፅ ሆነሽ ንገሪኝ» አላት በደከመ ድምፅ

«እሺ። ተግባብተን ልንዘልቅ እንደምንችል አስባለሁ። አንተም ባለፈው ጊዜ እንደጠየቅሁህ ከፍተኛ ፍላጐት እንዳለህ ሆነህ ትንቀሣቀሣለህ። በዚህ ሁኔታ፣ አባቴ፣ እጄን ላንተ በጋብቻ እንዲሰጥህ እንዲፈቅድ ነገ ትጠይቀዋለህ።»

ዱ ሮውሴ፣ ወዲያውኑ ይቆጣጠረው እንጂ፣ ከተቀመጠበት ላይ በደስታ አንርቶ ብድግ አለ።

«ማዳሞዚል፣ ከዚህ የበለጠ ቅንነት እንዳገኝ እምላለሁ አላስቸግረውም»

ይህ አባባሉ እውነት ነበር። በመጀመሪያ ላይ ጋብቻው በርሱ ፈቃድ እንዳልሆነ ያስብ ነበር። ነገር ግን፣ አሊስ ከጐበኘችው ምሽት ጀምሮ የወደፊት ሰጣ ፈንታውን የሚወስነበት በመሆኑ ሁሉም ነገር ተለዋወጠ። ለዚህም ሲል የሁለቱን በአንድነት መጣመር እውን ሊያደርግለት፣ ከርስዋም ጋር በመሆን ሊያገኘው የሚችለውን ደስታ ሊያስገኝለት ለሚችል ነገር ያለውን ሁሉ በዋጋነት ይከፍላል። በዚህ በኩል በርግጥ ታውሯል። ነገር ግን ስሜቱን ይበልጥ ያነደደው የአሊስ ነፃነት ነው። የሆነ ሆኖ፣ በዚህ ሰዓት ላይ ሙሉ በሙሉ ራሱን እየታለለ ይገኛል።

«አንተም ሆንክ እኔ፣ ይህ ጋብቻ እንዲፈፀም ቅንነት ያህል ፍላጐት አልነበረንምና ምንም አይነት ስህተት እንዳትፈፅም» ስትል ኮስተር ብላ ተናገረች።

«ለምን አይፈፀምም?» ሲል ተነጫነጨ

«ይህንንማ፣ አባቴ ገና ከመጀመሪያው፣ እኔን ላንተ ሲያቀርበኝ ራስህ ነበርክ የተናገርከው። አሁን ደግሞ ሃሣብህ ተቀይሮ ከሆነ፣ ስሜቶችህ የሚነጫነጉት እነርሱ ለቀመሱት ናሙና ምርጫ ሲሉ ነው። እምቢታዬ ሊያስቆጣህ ይችል ይሆናል። ነገር ግን አንተ እጅግ ሰፊ ተሞክሮ ያለህ ሰው ስለሆንክ፣ ስሜቶችህና ፍላጐትህ አይምታቱብህም»



«የለም፣ የለም፣ በጭራሽ፣ እመኚኝ» አለ ዱ ሮውሴ ለማልቀስ እየቃጣው።

«ይህን በተመለከተ ጊዜ አናጠፋም። እንደ ስሜትህ የተናገርከውን ቃል ጉዳዬም ባይሆን አምኜ እቀበልሃለሁ። በኔ በኩል ቢያንስ ቢያንስ ጋብቻ የሚባለው ጉዳይ ጨርሶ የለም። የምፈልገው፣ ጥያቄህን ለአባቴ እንድታቀርብለት ብቻ ነው። ይህን አሻፈረኝ የምትል ከሆነ ግን ሁሉንም ነገር አፍረጠርጠዋለሁ»

ዱ ሮውሴ ግራ ገብቶት ወንበሩ ላይ የመውደቅ ያህል ዘጭ አለበት

«እንዲህ ከሆነ ለአባትሽ ይህን የመሰለ ጥያቄ እንዳቀርብላቸው ለምን ፈለግሽ? ሊገባኝ አይችልም»

አሊስ ወደ በሩ ሄደችና መሸጐሪያውን በዝግታ ወደ ኋላ ሳበችው።

«ጌታዬ! የምታደርገውን ለምን እንደምታደርገው ሳትረዳው ስትፈፅመው ይህ የመጀመሪያህ አይደለም። የተስማማን መሰለኝ? ነገ፣ አባቴ እጄን እንዲሰጥህ እንደምትጠይቀው እጠብቃለሁ። ይህ ካልሆነ መናገሩ የኔ ተራ ይሆንና ውጤቱ እጅግ የከፋ ይሆናል»

«አሁን ጨክነሽ ልታባርሪኝ ነው?» ሲል ዱ ሮውሴ ጠየቃት

ይህች ሴት ፍፁም ድንግርግር የሚል ሁኔታ ውስጥ ጣለችው። ይህ ደግሞ በሁለት ምክንያት ነው። አንዱ በውበትዋ ሲሆን ሁለተኛው በሰጠችው ደስታ ትውስታ ነው።

በሩን ወለል አድርጋ ከፈተችው።

ዱ ሮውሴ፣ በጨለማው ውስጥ እግሩን የሚያሣርፍበትን መሬት በፍርሃት ተመለከተ። ሳይወድ በግዱ ከተቀመጠበት ላይ በመነሣት ወጣ። በሩ ዘንድ ሲደርስ፣ ምናልባት የከንፈር መሣም ለማግኘት ወይም የመጨረሻውን የፀፀት የፊት ገፅታ ለማሣየት ወይም ደግሞ ሴቶች በጭካኔያቸው የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚፈጥሩትን ሽንፈት ለመግለፅ ይሁን፣ መለስ ብሎ አያት። አሊስ ግን በሩን ፊቱ ላይ ዘጋጀበት።

በሚቀጥለው ዕለት ከሰዓት በኋላ ከመንገዱ መጨረሻ ላይ ወደሚገኘው የሕዝብ መናፈሻ በእግርዋ ተጓዘች። ወደዚህ ቦታ እንድትሄድ የተፈቀደላት በቅርቡ ነበር። ይህን ለማድረግም ራስዋን የምትሸፍንበትና ትከሻዋም ላይ ጣል የምታደርገው ስካርፕ መልበስና ከማንም ጋር ላለመነጋገር ቃል መግባት ይኖርባታል። በዚህ ጉዞ ላይ ፍራንቾይዝ አጀበቻት። ሁለቱ ሴቶች

ሲጓዙ ካዩቸዋው ከአንድ በላይ ኒጋዴዎች መካከል፣ ቆንሲሉ አባቷ በመሆኑና ዱ ሮውሌም በሁሉም ረገድ ደህንነታ በማግኘት የወደፊት አማቹ በመሆኑ ቀኑ፡፡

የዘንድሮው ክረምት እጅግም ቀዝቃዛ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ልክ እንደዛሬው ከሰዓት በኋላ ዓይነት የምሥራቅ ነፋስ ከአረቢያ ፔትሪያ በኩል ቀዝቃዛ አየር ያመጣል፡፡ በዚህም ውስጥ በመጠኑ ጨዋማ የሆነ ርጥበት ከስዊዝ ሸለቆ ስለሚኖር ተስማሚ ያደርገዋል፡፡

«ለመሆኑ ሚትር ዠረሚን አይተሽዋል?» ስትል በአይኑ ርግቧ ውስጥ ሆና አሊስ ጠየቀቻት፡፡

«አዎን፡፡ እንዲያውም ሁለት ጊዜ ነበር የሄድኩት፡፡ ስሄድ ሁሉ ከሰዎች ጋር ይወያያል፡፡ በተቻለው መጠን የሸሪኩን ቦታ ለመያዝ እየሞከረ ነው» ስትል ፍራንቸይዝ መለሰችላት፡፡

«የጠየቅነውን ነገር ተቀብሎ እሺ ብሏል?»

ይህንን የሴራ ጨዋታ በእግር በሚጓዙበት ሰዓት ተስማሚ ለማድረግ፣ የሆነ አበባ ወይም በርቀት ያለች ወፍ እያመለከተች አሊስ ቀዝቀዝ ብላ አጣፍጣ አቀረበች፡፡

«አንቺ አድርግ ብለሽ የምትጠይቂውን ሁሉ ያደርጋል፡፡» አለች ፍራንቸይዝ «እናም ደግሞ ጆን ባፕቲስትን እንደገና የማየት ሃሣብም . . »

«አደገኛ እንደሚሆን አልደበቅሽውም አይደል?»

«እንዲህ እንዲህ ያሉትን ነገሮች ሰውዬው በሚገባ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ለአደጋ የተጋለጠ ነው»

«ለመሆኑ . . . አነጋግሮሻል» ስትል አሊስ ጠየቀቻት

ፍራንቸይዝ ቀና ብላ ወደ ሰማይ ከተመለከተች በኋላ፣ውብ ጥርሶችዋን ሊያሣይ የሚችል መጠነኛ ሣቅ ሣቀች፡፡

«ለኔ ምን ይነግረኛል ብለሽ ነው? ሁለታችንም ብንሆን በሁኔታዎች ተገድደው በሚደረጉ ጉዳዮች ላይ፣ እኛን ለድርድር የማያደርሱን እስከሆኑ ድረስ ስንነጋገርባቸው መቆየት በራሱ ያስደስተናል፡፡ ታውቂያለሽ፣ ሁሉንም ነገር ተነጋግረናል . . . በኛ ዕድሜ እንደመታደል ሆኖ የጊዜው ማለፍ እምብዛም አይሰማንም፡፡ ሁለታችንም እንጠባበቃለን፡፡ ዘቃ ይኸው ነው»



«ይህን መረዳት እችላለሁ፡፡ ነገር ግን ያው፣ ያው ነው ቢባልም፣ ትንሽ ቅር ይለኛል፡፡ ሳለመለያየት ጥሩ ዕድል እያላችሁ . . . »

ጨዋታው ሁለቱንም እንዲያዝኑ አደረጋቸው፡፡ ጥቂት ርምጃዎችንም በፀጥታ ተራመዱ፡፡ ከዚህ በኋላ አሊስ ተግባራዊ የሚሆኑ ርዕሶችን ጀመረች፡፡ ሁለቱም በሙተጋገዝ ዝርዝሩን ሥራ አከናወኑ፡፡

ወደ ቆንስላው ጥቂት ቀደም ብለው እንደደረሱ፣ አንድ ዘበኛ መጥቶ፣ ክቡር ቆንሲሉ፣ ማዳሞዜል ዴ ማይሌን አሁኑኑ ሊያዩዋት እንደሚፈልጉት ነገራት፡፡ ምድር ቤት ወደሚገኘው ሰፊ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገባች፡፡ አባቷ፣ ጥቋቁር መስመሮች ያሉበት ቀይ ደማቅ ሙሉ ልብስ ለብሶ፣ ረዥሙን ሰው ሠራሽ ፀጉሩን አጥልቆ፣ በእግር ሹራቦቹ ላይ ጥብጣቦችን አስሮ ቆሟል፡፡ እርሷ ለራሷ፣ አባቷ በሽቶ የተነከረ ትልቅ አሻንጉሊት ይመስላል እያለች ታስባለች፡፡ አራት ማዕዘን ተረከዝ በሆነው ጫማው እየተሞናደሰ ወደርስዋ ተራመደ፡፡ ጀመረ እንግዲህ፣ እንደልማዱ ሁለቱንም እጆቼን በእጆቹ ውስጥ ሊይዛቸው ነው፡፡ ይኸው ብዬ የለ? ስትል አሰበች፡፡

«ውድ ልጄ . . . » ሲል ቆንሲሉ ጀመረ፡፡ ድምፁ በሕመም እንደሚንቀጠቀጥ እየተቆራረጠ፡፡

የጀመረውን አረፍተ ነገር የመጨረስ አቅም ስላጣ አቀፋት፡፡ ከኪሱ ውስጥ መሃረቡን አውጥቶ ፊቱን ጠረገና ቀጠለ፡፡

«የምነግርሽ ታላቅና ድንቅ ዜና አለ፡፡ ከዜናዎች ሁሉ የበለጠ ዜና ነው፡፡ እንደማምነው ሴት ልጅ በሕይወት ዘመኗ የምታገኘው ታላቅ ዜና ነው»

«ሁለመናዬ ጆሮ ሆኖ ይሰማሃል፣ አባዬ» አለች አሊስ፡፡

«እሺ እንግዲያውስ፡፡ ይህ እዚህ የምታይው የተከበረ ሰው አንቺን እንድሰጠው ጠይቆኛል፡፡»

በዚህ ጊዜ፣ በክፍሉ ውስጥ ጥላ ባለበት ቦታ፣ የሰበሰውን የሚመስል ጠባቃ ልብስ ከተሰቀለበት ፊት ለፊት ዱ ሮውሌ እስስት መስሎ ቆሟል፡፡ ወደ ክፍሉ ውስጥ ስትገባ ያላየችው አሊስ፣ አሁን ጭንቅላቷን ወደርሱ አዞረች፡፡ አንገቱን ከተቀላ በኋላ በሁለት እግሮቹ ቀጥ ብሎ የቆመውን ሰማዕቱን ቅዱስ ዴኒስን መስሏል፡፡ ደም የሌለውን የሰማዕቱን ፊት

የመሰለ ፊትና፣ መቅሰፍት ሲመጣ ለመስማት እንጂ እርሱ ላይ እንዳይወድቅበት የሚሻ ይመስል አይኖቹን ጨፍኗቸዋል። አሊስ እጅግ ሲበዛ ለዱ ሮውሴ አዘነችለት።

«አባዬ፣» አለች በርጋታ «ለብቻህ ልነግርህ የምፈልገው ነገር አለኝ»

በቅዕበት የሚከናወኑ ጥቂት የትዕዛዝ ዓይነቶች አሉ። ምልክት ይጠብቅ የነበረው ዱ ሮውሴ፣ ወዲያውኑ ተሰወረ። ብቻቸውን እንደሆኑ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ምናልባት ሆን ብላ ጥፋትና ጉዳት እንዲደርስ የመጨረሻውን እንቅስቃሴ ታደርግ ይሆናል እያለ እየፈራ ወደልጁ ዞረ።

«ስሜትሽ ተረብሿል። ነገሮችን ሁሉ በጣም ቀላልና ተራ አድርገን ለመያዝ በርግጥም ምስጢራዊ የሆነውን ነገር ውበት ሳለማደፍረስ እንሞክር። እናም፣ ታዲያ የወደፊቱ የትዳር ጓደኛሽ እንዳይሰማ በማለት ልትነግሪኝ የፈለግሽው ጉዳይ ምንድን ነው?»

«አባዬ፣ ነገሮችን ሁሉ ቀለል እንዳደርጋቸው ጠይቀኸኛል። እኔም ቀለል አደርጋቸዋለሁ። ይህ ሰው በፍፁም ባሌ አይሆንም»

«አንተው አድነኝ አምላኬ! አምላኬ! » አለ ሙሴ ዴ ማይሌ። ወደ ሰማይ እያንጋጠጠ። «ለምን ቢባል?»

«ምክንያቱም ለዘለዓለም አላገባምና»

«እንዲህ ነው። እንዴት እንዲህ በድንገትና ሳይታሰብ የሃሣብ ለውጥ ታደርጊያለሽ። ያውም ያለ በቂ ምክንያት?» አለ ቆንሲሉ በሃይለ ቃል

«ድንገትና ሳይታሰብ የተደረገ የሃሣብ ለውጥ አይደለም። በቂ ምክንያትም አለው። የማይቻል ስለሆነ ነው»

«ለምን እንደሆነ ሳውቀው እችላለሁ?»

«ከፈለግህ፣ አባዬ እነግርሃለሁ»

«ከፈለግህ አልሽኝ? አዎን እፈልጋለሁ እንጂ። በዚህም ላይ ጋብቻ የሚከለክል ነገር ምን እንደሆነ የማወቅ መብት ያለኝ ይመስለኛል።»

ስፖርተኛ ውድድሩን ከመጀመሩ በፊት እንደሚያደርገው፣ አሊስ አየር በሃይል ሣበች።

«ለዘለዓለም የማላገባው ክብሬ ስለተገሠሠ ነው»



«ክብሬ ተገሠሠ ስትይ ምን ማለትሽ ነው?» አለ ቆንሲሉ ትዕግስቱ እያለቀበት።

«ማለቴ ነዋ። በተፈጥሮ እንዳለሁት ከነክብረ ንፅህናዬ አይደለሁም። ወይም አንዲት ሴት ከባሏ ጋር ልትሆን በሚያስችላት ደረጃ ላይ አይደለሁም»

የከንች እንጨት አናቱ ላይ ቢወድቅ ኖሮ፣እንዲህ ሲያንገዳግደው አይታይም ነበር። ወደ ኋላው አንድ ርምጃ ከተራመደ በኋላ ጠረጴዛውን ጠንከር አድርጎ ይዞ ቆመ።

«ልጄ፣ ይህማ ቀልድ ነው . . .»

አሊስ፣ ርህራሄ ሳይሰማትና ዓይኖችዋን ሳትሰብር ቀጠለች

«ምናልባት ቄስ፣ወይም አንዲት አዋላጅ ካለች፣ወይም ይህን እኔ ያልኩትን የሚያረጋግጥና አፊሴል መግለጫ ሊያዘጋጅ የሚችል ማንኛውንም ሰው ከመረጥክ አሁንም ፈቃድህን ለመፈፀም ዝግጁ ነኝ»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ልጁን በጥፊ ለማጮል በጣም ቋምጦ ሳለ፣ በጥላቻ የተሞላው አተያይዋ ገታው። ራሱን ካረጋጋ በኋላ በያንዳንዱ ርምጃው ወለሉን በሃይል እየደቃ ክፍሉን በስፋው ዞረው። በንጉሡ ሥዕል ፊት ሲያልፍ አይኖቹን ለበራቸው። ከዚያም አንድ ሃሣብ ብልጭ ሲልለት፣ ወደ አሊስ ተመልሶ ዞረ።

«ይህ ሁሉ የሆነው ከዚህ መድሃኒተኛ፣ ከዚህ አስመሣይ፣ ያ ፖንሴ ከሚሉት ጋር እንደሆነ ብቻ እንዳትነግሪኝ» አላት አይኖቹን አጥብቦ እየተመለከታት

«የለም አባቴ፣ እርሱ አይደለም»

«እንግዲያው ማነው?» አለ ቆንሲሉ የሾላውን ጣውላ ጠረጴዛ በመዳፉ እጁ እየደበደበ።

«አንተ የምታውቀው አይደለም» አለች በትህትና

«እንዴት ሊሆን ይችላል? ከዚህ ወጥተሽ ሄደሽ አታውቂም። የሚመጣውም እንግዳ ሁሉ ይነግረኛል። የለም፣ የለም፣ እየተከላከልሺው ነው እንጂ፣ ሊሆን የሚችለው ፖንሴ ብቻ ነው»

«እውነተኛውን ቃሌን ነው የነገርኩህ»

«ምን ቀርቶታል? እንግዲያውስ ማነው?» አለ ቆንሲሉ ጥርሱን ነክሶ

«ቱርካዊ ነው»

«አምላኬ!» አለ ቆንሲሉ በዚህ የመጨረሻ ጦር ሲወጋ

«ምን ለውጥ ያመጣል፡፡» ስትል በትህትና ተከራከረችው

«ዋናው ነገር እውነታው ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ሃላፊ የሚሆነው ሰው ይህን ያህልም የሚያስጨንቅ አይደለም»

«ያው፣ ያው ነው! ቱርካዊ!»

አንድ አዳኝ፣የሞቱች ጥንቸልን በድን መሬት ለመሬት እንደሚጉትት ሁሉ፣ ቆንሲሉም፣ሰው ሰራሽ ፀጉሩን ስርዓት በሌለው ሁኔታ ካወለቀው በኋላ ወለሉ ላይ እያወዛወዘው ወደፊትና ወደኋላ መራመድ ጀመረ፡፡

«እንዲህ ያለው የተረገመ ሰው፣ የት ቦታ ነው አግኝቶ የለከፈሽ?»

«ጊዛ ውስጥ ነው»

«አውቄአለሁ! እዚያ እንድትሄጂ በጭራሽ አልፈለግሁም ነበር፡፡ ያቺ ሴት አገልጋይ ደግሞ አጃቢሽ ነበረች፣ ወይም አቃጣሪሽ ልትሆን ትችላለች»

«ስለዚህ ጉዳይ ፍራንቾይዝ የምታውቀው ነገር የላትም፡፡ የዚያን ዕለት እሷ ከፈረስ አጣቢው ከሚካኤል ጋር እንቁላላ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄዳ ነበር፡፡ አንድ ሰው ከወደ ወንዙ በኩል መጣ፡፡ እሣ አስጋሪ ነው፡፡ ወደ መድረኩ ወሰደኝ»

«ያለ ፈቃድሽ? ይህ የሃይል ስራ ነው? ወይኔ! ምርመራ እንዲደረግ ፓሻውን እጠይቀዋለሁ፡፡ ምርመራ የሚያከናውኑ ቡድኖችም ይኖራሉ፡፡ ያገኙታል!»

«አይሆንም አባዬ፣ አቅጄ ነው፡፡ ምናልባት ፀሐዩም ይሁን ወይም የቦታው ፍፁም ጭር ማለት፣ ብቻ ለወሲብ የሚያነሣሣ ነበር፡፡ ልጁ ገና ብቅ ሲል እኔ ፍላጉት አደረብኝ---»

«በቃኝ!» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ አቋረጣት፡፡

«ከዚህ በላይ መስማት አልፈልግም፡፡ ይህ የሚያስፈራ ነው! ይህ ርግማን ነው፡፡ ብቸኛዋ ልጄ፣ ብቸኛዋ ተስፋዬ፣ ብቸኛዋ ወራሼ!»

ከተበላሸችው ልጁ ሃሣብ ይልቅ፣ ልጁ የተጫወተቻቸውን ማለቂያ የሌላቸውን ትዝታዎቹን በደስታና በብልፅግና ራዕይ ተሞልቶ ሲያወጣና ሲያወርድ በርግጥም ቆንሲሉ ተረብሾ ነበር፡፡



«ፖንቻርትሬይን . . . ነፍስ ያለው ፖርቲ . . . አምባሣደር ሊሆን ምንም ያልቀረው . . . »

በወንበሩ ላይ እግሮቹን አመሣቅሎ ተቀምጦ፣ ጉንጉን በትልቁ ትከሻው ላይ አስደግፎ፣ ለራሱ ያወራ ነበር፡፡

«በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ከመግባታችን በፊት ይህን ጉዳይ ለምን ቀደም ብለሽ አልነገርሽኝም ነበር?» ሲል ጮኸባት

«ችግሩ ውስጥ ገብተህ ነበራ፡፡ ከዚያም በተጨማሪ አባዬ፣ ካንተና ከእማዬ ጋር ልኖር የምችለውን ያህል ጊዜ መኖር ስለምፈልግ ከመንገር ተቆጠብኩ፡፡ የኔ ሁኔታ እንዳሳሰበህ ወዲያውኑ . . . »

«ያንቺ ሁኔታ! ፀንሻለሁ ብለሽ ብቻ እንዳትነግሪኝ!»

«ዕድለኛ ነኝ፡፡ እንዳልፀነስኩ ማረጋገጫ አለኝ»

«ቢያንስ ይህ አንድ ስጋት ይቀንሳል»

«እንዳልኩህ፣ የተለወጠውን ሁኔታዬን አንተ ስትገነዘብ፣ ሁሉም ነገር ተለወጠ እንበል፡፡ ይህ ከሆነ፣ ላንተ ፈቃድ ተሸንፌ በፈረንሣይ ጠቅላይ ግዛት በአንድ ጨለማ ገዳም ውስጥ ቀሪውን ዘመኔን ራሴን ቀብሬ እኖራለሁ፡፡»

«ትክክል! ይኸው ነው፣ ሌላ አማራጭ የለም፣ ወይኔ ሰውዬው! »

«እኔም ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ፡፡ አባዬ» አለች

አሊስ፣ ትንሽ እንባ በጉንጮችዋ ላይ እንዲፈስስና ፊትዋን እንዲያርሰው በማድረግ፡፡ «ይህን ታዲያ በተቻለ ፍጥነት ማከናወን ይኖርብናል፡፡ ከዚህ በኋላ አንተ ባለህበት ይህን ውርደቴን ተሸክሜ ልኖር አልችልም፡፡ ይገድለኛል»

«እኔም አንቺን ማየቱ እንዲሁ ይገድለኛል» አለ ቆንሲሉ ትዕግስት አጥቶ

ይህ ሁሉ ሲሆን እርሱ ሌላ ሃሣብ ውስጥ ገብቷል፡፡ ፈረሰኛው ዱ ሮውሌ፣ ሊነገረው ይገባል፡፡

«ፀጉርሽን አሣምረው፡፡ ጉንጮችሽም ላይ አንዳንድ መዋቢያዎችን አድርጊ፡፡ ወጣቱን ሰው እጠራዋለሁ»

አሊስ በፍጥነት ራስዋን ሰብሰብ አደረገች። ዱ ሮውሌ፣ ጭንቅላቱን በትከሻዎቹ መሃል ቀብሮ እንደሚታደን አጋዘን በሁሉም አቅጣጫ በፍርሃት እየተቁለጨለጨ ገባ።

«ቀድሞውንም ባልሆነ ነበር፣ ውድ ጌታዬ» አለ ቆንሲሉ፣ ግርማ ባለው ቃና። «ልጄን አማክርኋት። በዚህ ዓለም ላይ በታላቅ ደስታ ልትቀበልህ የምትችለው አንተን ሆኖ ሳለ፣ ነገር ግን አንተ ልትታገለው የማትችለው ተፎካካሪ አለብህ። ሳትደብቅ የነገረችኝ፣ልጄ ለዚህ ሃያል ሕይወቷን ሁሉ ለመስጠት ተስላለች። የምናገረው ስለእግዚአብሔር አምላክ ነው። ልጄ አሊስ፣የመንፈሣዊ ሕይወት ጥሪ ደርሷታል። እኔም ይህን ለመከልከል ኩቶም አቅም የለኝም»

«አረ!» አለ ዱ ሮውሌ፣ በድንጋጤ አግራሞት። ዓይኖቹን ወደ ወጣቷ ሴት ወረወራቸው። ለአፍታ ያህል በዚህ በሚያስታውሰው ስጋዊ ውበትዋ ላይ፣ ሌላ ከላይ የተጫናት አንዳች መልክ ታየውና ቆንሲሉ የገለፃት አይነት እመምኔት አልታይህ አለችው።

«እናም» አለ ቆንሲሉ፣ በማዘን «እግዚአብሔር ይሰጣል፣ እግዚአብሔር ይነሣል። አንዳንድ ጊዜ ከመሃላችን እርሱ የፈለገውን ብቃት ያለውን ይጠራል። ይህ የርሱ ፈቃድ ስለሆነ እንደፈቃዱ ይሁን። አንተም ለአምባሳደርነቱ የመጨረሻውን ዝግጅትህን ስታደርግ፣ ልጄም የአሌክሳንደሪያን ጉዳና ትጀምረዋለች። በሚቀጥለው የሮያል መርከብ ላይ በመሣፈር ፈረንሣይ ውስጥ ወደ ሚገኘው ገዳሟ ታቀናለች።



# 2

አንዳንድ የመሬት ገፅታዎች ስምንታቸው ጠፍቶ፣ ሁለመናቸው በጭራሮና በእሾሃማ ዳዋ ተሞልቶ፣ ዕጣ ፈንታቸው በዚሁ የሚቀር ቢመስልም፣ የሰው ልጅ በሚያከናውነው ተግባር፣ በተፈጥሮ ላይ አንዳች ውበትና ሌላው ቀርቶ ብልፅግናን ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ይሣካሉታል። እዚህ አካባቢ ያለው የመሬት ገፅታ ፍፁም የተገላቢጦሽ ነው። ተፈጥሮ ራስዋ፣ መሬቱን፣ አየር እንደልቡ የሚመላለስበትና ምንም ዓይነት ማዳበሪያ ሳይሰጠው የፈለገው ነገር የሚበቅልበት ጥቁር ለም አፈር ነው። ከበላዩ የሚታየው ሰማይ በርህራሄ የተመላ በመሆኑ፣ ፀሃይንና ዝናብን በስምምነት እያፈራረቀ ይመግበዋል። ምድሩ እጅግ ንፁህ የምንጭ ውሃዎች፣ ተንጠባጥበው ከሚገኙት ኩሬብታዎች ውስጥ እየተንሳፈፉ የሚወርዱበት ነው። ተፋሰሱ እጅግም አቀበት በመሆን የእርሻን ሥራ የሚያውክ ሣይሆን፣ ይልቁንም ተስማሚና አመች ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህ ዓይነቱን የተፈጥሮ ስጦታ ሰዎች በሚችሉት ሁሉ አጥፍተውታል። እርስ በርሣቸው በሚያደርጓቸው ፀቦችና ጦርነቶች፣ ወንድም ወንድሙን እያጠፋው፣ ደካሞችንም በማስወገድ አገሩን ለረሃብ አጋልጠዋል። የባላገሩ አካባቢ፣ ወፍ ዘራሽ እሾማሃ ቁጥቋጦ የለበሰ ስለሆነ፣ አልፎ ተርፎ መንገዱን ይሸፍነዋል። በዚህ ውስጥ የሚጓዝ ፈረሰኛ መንገዱን እንዳይስት ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። ሰፋፊዎቹ ጉዳናዎችም፣ ተገልጋይ ችላ ስላላቸው በቁጥቋጦው ውስጥ ያሉ የእግር መንገድ መስለዋል። ከቤት ቤት ያለው ሁሉ ወድሟል። በጫካው ውስጥ የሚጓዝ ሰው ቀማኞችን ለመቅረፍ ሣይሆን፣ በደመነፍስ ሰውን ከሚተናኮሉ ልቅ ውሾች ራሱን ለመጠበቅ መሣሪያ መያዝ ይኖርበታል።

ፈረሰኛው፣ በአንድ ኮርብታ ላይ ከተመሠረቱት መንደር ድረስ ጋለበ። ከርቀት ሲያዩዋት ትልቅና ምናልባትም አዳጊ መንደር ትመስላለች።

እየተጠጋ ሲመጣ የተገለበጡ ጉተራዎችን፣ የተቃጠሉ የሣር ክዳን ቤት ጣሪያዎችንና የቤቶች ቅርፆች ብቻ ተርፈው ተመለከተ። እንደ ሸቦ የቀጠኑና ግራጫ የለበሱ፣ አጥንቶቻቸው የሚቆጠሩትን ፍየሎቻቸውን በፍርስራሹ ውስጥ የሚጠብቁ ጥቂት አሮጊቶች አሉ። ፈረሰኛው፣ በአንድ የወደቀ ግድግዳ አጠገብ የተቀለሰ ድንጋይ ያለበትና ሣር በየቦታው ከበቀለበት የመንደሩ አደባባይ ሲደርስ ቆመ።

«ማነህ እዚያ!» ሲል አንድ ወጣት አረኛን ተጣራ «እስቲ ወዲህ ቀረብ በል»

ሕፃኑ ልጅ የተጨማለቀ ፊቱን ወደ ሰውዬው ቀና በማድረግ፣ በባለማመን አተያይ ከተመለከተው በኋላ፣ በባዶ እግሩ በነዚያ ሹል ድንጋዮች ላይ እግሬ አውጭኝ ብሎ ተፈተለከ። ሰውዬው፣ ቀልማማው ክዳኑ መንገደኛው፣ ከዚህ በኋላ አንድ ሽማግሌ ሰው ተመለከተ። ሰውዬው፣ ቀልማማው ክዳኑ መንገደኛው፣ ከዚህ በኋላ አንድ ሽማግሌ ሰው ተመለከተ። ፈረሰኛው፣ ከፈረሱ ከተወነደበት ከአንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ የመሸሸግ ያህል ቆመዋል። ፈረሰኛው፣ ከፈረሱ ላይ ወረደና ልጓሙን በአንድ ክቡሩ ተንቀሎ በፍርስራሽ ላይ በወደቀ ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ አሰረ። የለበሰው ኮት ከመንገዱ ላይ የተነሣውን የአቧራ ብናኝ ዱቄት ለብሷል። ዓይኖቹ ጉድጓዳቸው ውስጥ የተቀረቀሩ ናቸው። ጉንጮቹ በማምንት የቆረን ለቀማ ምርት ተሸፍነዋል። አረማመዱ፣ ለጥቂት ጊዜያት በረጋ መሬት ላይ እንዳልቆመ መርከበኛ፣እርግጠኛነት የለውም። ዓይኖቹ ወዳቀኑበት ሽማግሌ ተራመደ።

«ሰዎች ሰውቢይራን ብለው የሚጠሩት መንደር ይህ እንደሆነ ሊነግሩኝ ይችላሉ?» አሳቸው የደከመውና ከጆን ባፕቲስት በስተቀር ሌላ ሊሆን የማይችለው ፈረሰኛ

ፊጣን ግልቢያ ያደርግ በነበረበት ጊዜ ባርኔጣውን ስለጣለው፣ ግንባሩ በላብ ወርዝቶና ፀጉሩም በአቧራ ብናኝ ተያይዟል።

«ለዚህ ቦታ ስም የሚሰጡት ብዙ ሰዎች የሉም» አሉ ሽማግሌው ሰውዬ

ድምፃቸው መጠነኛ የጉረምሣ ዓይነት ቀላዒ ቢሰማበትም ግልፅና ኮለል ያለ ነበር።

«ግን እውነትህን ነው» ሲሉ ቀጠሉ «ከሰውቤራይን የተረፈው ይህ ነው»

«እዚህ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ወዴት አሉ?» ሲል ዙሪያውን እየተመለከተ ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

የሰሜን ምስራቅ ነፋስ፣ ላለፉት ብዙ ቀናት እንደቢላዋ ጠርዝ ቀዝቅዞና ስሎ ሲነፍስ ሰንብቷል። በዚህም የተነሣ ከሰማዩ ላይ ደመናውን ሙልጭ አድርጎ ስለወሰደበት፣ ከክሰሉት የመንደሯ ድንጋዮች በላይ በጣም ግልፅ ሰማያዊ ሰማይ ብቻ ይታያል።

«መልሱን እያወቅህ ልታጠምደኝ የምትሞክር ከሆንክ ግን» አሉ ሽማግሌው ሰውዬው፣ «እኔንም ከምትፈልጋቸው ሰዎች አንዱ መሆኔ እርግጥ ስለሆነ፣ አሁኑኑ ልትወስደኝ ወይም እዚሁ ልትገድለኝ ትችላለህ። ነገር ግን እንደምትናገረው አገሩን የማታውቅ ሰው ከሆንክ ከሩቅ ቦታ የመጣህ መሆን አለበህ»



«እጅግ ከሩቅ ቦታ ነው የመጣሁት»

«እንግዲያው እዚህ ድረስ እንድትመጣ ያደረገህ፣ አንዳች የሆነ የምትፈልገው ነገር ወይም የምትፈልገው ሰው አለህ ማለት ነው። በየትኛውም መልክ ብትመጣም ልነግርህ የምችለው መጥፎ ዜና ነው»

«አንዲት ሴት እፈልጋለሁ»

«ወንድ ሰው የምትፈልግ ቢሆን ኖሮ ወዲያውኑ በቃህ እልህ ነበር። ምክንያቱም በሕይወት እንዳሉት አድርገህ እኔንም መቁጠር ከፈለግህ እዚህ ያለነው ሁለት ብቻ ነን። በርግጥ ጥቂት ሴቶች አሉ። አንተ የምትፈልጋት ማን ትባላለች?»

«ማሪኔ ትባላለች»

ሽማግሌው ሰውዬ ቀና አሉ።

«የቤተሰቧን ስምስ ታውቀዋለህ?»

«አግብታ፣ ቢበዛ አንድ ሣምንት የቆየች ነበረች። ባሏ አገር ጥሎ ጠፋ። ስሙ ሜትር ዠረሚ ይባላል»

«እህ! ዠረሚ! እውነት ነው። ጥሩ ቁመና የነበረው ጉብል ነበር። ለቅርብ ጎረቤቶቼ ሁለተኛው ልጃቸው ነበር። ይኸውልህ እዚያ ከጉተራው በስተጀርባ። ሰመሆኑ በህይወት አለ?»

«የሥራ ሸሪኬና ጓደኛዬ ነው። ካይሮ ውስጥ ይኖራል»

«ካይሮ ውስጥ፣ ግብፅ ማለት ነው። የመፅሐፍ ቅዱሱ ግብፅ። እግዚአብሔር ታላቅ ነው! ምን ዐይነት እድል ነው! እንዲህ ያለው ዜና በኔ እድሜ ምን ያህል ድንቅ እንደሆነ አይገባህም። አንተ ከዚህ ከሄድክም በኋላ ቢሆን ይህን ዜና ሳሰበው እኖራለሁ። እውነቱን ልንገርህ፣ ዠረሚ እስከአሁን በሕይወት በመኖሩ ደስተኛ ነኝ»

«ባለቤቱስ ማን?» ሲል ጆን ባፕቲስት ቀጠለ።

«አ! እንዲህ ባለ ነገርስ አታስቀየመው፣ ያለፈው አልፏል። እርሱ ብቻ ነፉ አይኝው በሰላም ይኑር»

«ግን እኮ አልተረዱኝም» አለ ጆን ባፕቲስት ጉልበቱን መሬቱ ላይ አሣርፎና ፊቱን ወደ ሽማግሌው ቀረብ አድርጐ:: «የላከኝ እሱ ራሱ ነው:: እስከዛሬ ድረስ ይህን ሁሉ አመት ለርስዋ ታማኝ ሆኖ ይኖራል:: ተደስቶ እንዲኖር የሚመኙለት ከሆነ እርሱም ይህን ማወቅ ይኖርበታል::»

«አዎን» አሉ ሽማግሌው በሃሣብ ሰጥመው «እርሱ እንዲህ አይነት ሰው ነው:: በቃ! እርሱ እንዲህ ዓይነት ሰው ነው:: የርሱ ቤተሰቦች የሆኑት ሁሉ የርሱ ዓይነቶች ነበሩ:: ምናልባትም የዚህች መንደር ሕዝብም በሙሉ እንደዚሁ እንደሆነ እስባለሁ:: ለዚህም ነው እንዳንተርፍ ያደረጉን»

ዓይኖቻውን ቀና አደረጉ:: የሆነ የፉጨት ድምፅ ከበላያቸው ላይ አስተጋባ::

«እርሱ የሄደ የዕለቱ ዕለት አረፈች»

በዚህ የባላገር አካባቢ የነበረው ፀጥታ ከጥቁር ድንጋይም ይከብዳል:: ሌላው ቀርቶ ነፋሱ ከድንጋዮች በላይ ድምፁን አጥፍቶ ይንቀሣቀሣል::

«እንዴት ሆነ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

«ወዳጄ» አሉ ሽማግሌው፣ ረጋ ባለ ሁኔታ አሻግረው ወደሀዋ እየተመለከቱ:: «ጠቃሜታ ባይኖረውም ታሪኩን ለመናገር ያህል ሁለት ብቻ ቀርተናል:: መከራዎችና አሣፋሪ ተግባራትን ለመቀበል የተፈጠረን ይመስላል:: ግን ይህን ታሪክ መናገር ምን ይጠቅማል? በርግጥ ይህ መጥፎ ስምና ታሪክ ለትውልድ ሲተላለፍ ይኖራል:: የለም፣ የለም፣ ስለጨካኝ ገዳዮቻችን ያለንን መጥፎ ትዝታ ከምንወዳቸው ሟቾቻችን ጋር በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ቀብረናቸዋል:: ይህን ያደረግነው ለፍቅር፣ ለሰላምና ለደስታ ስንል ነው:: ለዚህም ደግሞ የመታሰቢያ ሃውልት ልናቆምላቸው ይገባናል:: ምክንያቱም የነርሱም ታሪክ ካለኛ መኖር አይችልም::

«ቢሆንም ግን ይህቺ ሴት፣ ይህች ወጣት ሴት፣ ንፁሪሚ ያገባት ሙሽራ . . .»

«አዎን፣ ታፈቅረው ነበር:: ለርሱ የነበራትን ፍቅር፣ ጊዜ ወይም ሰው የሚያበላሽባት አልነበረችም:: ስሙን እየጠራች ነው የሞተችው»

ሽማግሌው ሰውዬ፣ በጣቶቻቸው በመፈተግ ያለሰለሱትን ትንሽ ጭራሮ ይዘው በሚያሣዝን ሁኔታ ተነስተው ቆሙ:: በከስማናው ሰውነታቸው ላይ የደረቡትን ያረጀ ወፍራም ካፖርት ጠራረጉ::



«ለጥቂት ጊዜ ትቆያለህ?» ሲሉ ጠየቁት

«የለም፣ አልቆይም:: በፍጥነት መሄድ ይኖርብኛል:: በርግጥ . . .»

ጆን ባፕቲስት፣ ሽማግሌው እንዲያጅቡት በመፈለግ ክንዱን ዘረጋላቸው::

«. . . ማንም ሰው ቢጠይቅዎ አላዩኝም»

«ከኛ አንዱ ነህ?»

«አይደለሁም፣ ነገር ግን የጋራ ጠላቶች ያሉን ነን»

«እንግዲያው ተጠንቀቅ::» አሉ ሽማግሌው

ሰውዬው፣ የወጣትነት ወኔአቸውን በተመሣሣይ ሁኔታ እየተሰለቡ፣ የቀሩትን ሁሉ እያሰቡ፣ ከጐናቸው ያለውን ጠንካራና የደስደስ ያለውን ወጣት ሰው መረመሩ::

«ለመሆኑ ከወዴት ነው የመጣኸው? ፈረስህም የደከመው ይመስላል»

«ይህኛው የመጣው በራይን ወንዝ አጠገብ ካለችው ከተርን መንደር ነው:: ከዚህ በኋላ ብዙ ሊጓዝ የሚችል ስለማይሆን እሰጋለሁ:: ፖሪስን ከለቀቅሁ በኋላ ስድስት ያህል ለውጫለሁ»

«ፖሪስ!» አሉ ሽማግሌው በመደነቅ «እና ወዴት ለመሄድ ነው አቅድህ?»

«ወደ ሲዮቴ፣ በዛሬው ምሽት እቀጥላለሁ»

«በዚህ አካባቢ ያሉት ወታደራዊ ቦታዎች በሙሉ በነዚያ ጭራቆች እየተጠበቁ ናቸው» አሉ ሽማግሌው::

ከዚያም ዘወር አሉና በፍርስራሾች መሃል የገደል ማሚቶ መፍጠር በቻለ ድምፅ ተጣሩ::

«ዳንኤል!»

ጆን ባፕቲስት፣ ቀደም ሲል አይቶት የነበረውና ፊቱን ሁሉ ጥላሸት ያጠቀረበት ልጅ፣በአቅራቢያው ካለው ግርግዳ ውስጥ ጭንቅላቱን ብቅ አደረገ::

«ወዲህ፡ ና» አሉ ሰውዬው::

ወደ መንገደኛው ዞሩ::

«ይህን ልጅ አፈናጥጠህ ውሰደው:: በቁጥቋጦዎች መሃል አድርጐ፣ የኛ ሰዎች ወዳሉበት አካባቢ እስከአሁን የሚኖሩ ከሆነ፣ ሳሰበው ግን ይኖራሉ፣ መርቶ ይወስድሃል::

በአሁኑ ጊዜ በየገደሉና በየሸንተረሩ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አለ። አንዳች ታላቅ ሁኔታም እየቀረበ እንደሆነ ይታየኛል። ሰዎቹን ስታገኛቸው ከሶውቤይራን እንደመጣህና ጆን እንደላከህ ንገራቸው። ጆን ማለት እኔ ነኝ»

ጆን ባፕቲስት ፈረሱ ላይ ወጥቶ፣ ሕፃኑን ልጅ ከኋላው ለማፈናጠጥ ይዞ አነሣው።

«ይህ ከመንገድህ ወጣ አድርጕህ ይወስድህ ይሆናል። ቢሆንም አትቆጭበትም። እዚያ ስትደርስ አዲስ ፈረስ ይሰጡህና ነገ ቧት ሲዮቴ ትገባለህ» አሉት ሽማግሌው

«እግዚአብሔር ይስጥልኝ» አለ ጆን ባፕቲስት

የገንዘብ ቦርሣውን ወዳስቀመጠበት ወደ አንደኛው የኮርቻ ኪስ እጁን ሰደደ።

«ትንሽ ዕርዳታ ባደርግልዎ?» ሲል እየፈራ ጠየቃቸው

ሽማግሌው የፊቱን ነፀታ ተመልክተው አስቆሙት

«ከኔ ይበልጥ አንተ ያስፈልግሃል። በነዚህ ቤቶች ሁሉ ውስጥ፣ ጭራቆቹ ሊያገኟቸው የማይችሏቸው የተቀበሩ ሣንቲሞች አሉ። ገንዘብ ይዘን ካዩን ተመልሰው ይመጣሉ»

«እንግዲያውስ ደህና ይሁኑ ጆን። ሰላምታዎን ለገርሬሚ አደርሳለሁ።» አለና ጆን ባፕቲስት ተንቀሳቀሰ።

ፈረሱን በእርካቡ ኮረኮረው። በሃረጋማው ቁጥቋጦ ውስጥ ጭንቅላቱን የተከለው ምስኪን ፈረስ ግን አልተንቀሣቀሰም። በመጨረሻ ግን በወደመው ቦታ ላይ፣ ወድቀው በቀሩ ስማዕታት አፅም ላይ፣ በጥንቃቄ በመራመድ ተጓዘ።

ጆን ባፕቲስትና ልጁ እየጋለቡ ሲሄዱ «ዝቅ ብለህ ተመልከት» አሉት ጆን። «ያቆሟቸውን የመታሰቢያ ሃውልቶች ታያቸዋለህ? ድላቸውን የሚዘክሩበት መስቀል! . . . ይህን ታምናለህ?»

ይህ ሁሉ ሲነገር ፈረሰኛው ግን ሊሰማ ከሚችልበት ርቋል።

ሶ

ከሶውቤይራን አልፎ ያለውን የቁልቁለት መንገድ ጥሰው ሲጓዙ፣ርጥበት ያለበትና ጥላ የሚያጠላበት ሸለቆ ውስጥ ገቡ። በምንገ ዳር ዳር፣ አልፎ አልፎ ዳገታማው መንገድ



በየቅጠሉና በየእንጨት ሽበቱ ተሸፍኖ ተዘርግቷል። ጊዜው እየመሸና ከበላይ ያለውም ጥላ ይበልጥ እየጨለመ መጣ። በፈረሱ ኮቴ ስር ጭራሮዎች ሲሰባበሩ በስተቀር ምንም ሳይሰሙ ዳገቱን ተያያዙት። በአረንጓዴ የድንጋይ ላይ ሣር የተሸፈነ የመጨረሻው ቋጥኝ ከፊት ለፊታቸው እንደተጋረጠባቸው፣ ልጁ ወደ ቀኝ አቅጣጫ አመለከተ። ልጁ፣ ሙሉ በሙሉ ግንኙነት የሚያደርገው በምልክት ብቻ ነው። አሁን ግን በድንገት በመጮሁ ቀደም ሲል ድምፁን ያልሰማው ጆን ባፕቲስት ደነገጠ። ጕኸቱ፣ ቃላት የሌሉበት የእንስሳ ዓይነት ድምፅ ነበር። እንዲያውም፣የሚቆራረጥ የጉጉት ወፍ ዓይነት ማቃሰት የመሰለ ሦስት ጊዜ አሰማ። ጉዟቸውን ግን በአንድ ወድቆ በተሰበረ ግዙፍ ያረጀ ዛፍ ስር በማለፍ ቀጠሉ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ አነስተኛ የቅጠላቅጠል መንኰሻኰሽ ተሰማ። ወዲያውም አምስት ሰዎች ከየቋጥኙና ከየዛፉ ላይ የበቀሉ ይመስል ብቅ አሉ። ሰዎቹ፣ ጥቁር ያሉ፣ የጥርጣሬ ስሜት ያለባቸውና እንደዲያብሎስ ፊታቸውን ያጨፈገጉ ነበሩ። ቀስቶቻቸውን በፈረሰኛው ላይ አነጣጠሩ።

«ከሶውቤይራን ጆን ናቸው የላኩኝ» አለ ጆን ባፕቲስት ረጋ ብሎ።

በባርኔጣዎችና ባጕፈሩ ፂሞች ኋላ ካሉት ከነዚህ ፊቶች ለየትኛው እየተናገረ እንደሆነ አላወቀም።

«እውነት ነው!» አለ ሕፃኑ

«ውረዱ!» ሲል ከሰዎቹ አንዱ ለስለስ ባለ አነጋገር አዘዘ።

ጆን ባፕቲስት፣ ከኮርቻው ላይ ወርዶ መሬት እንደረገጠ እጆቹን ወደ ላይ ሰቀላቸው። አስቀድሞ የተናገረው ሰው ወደ ፈረሱ ተጠግቶ ሻንጣዎቹን ተመለከታቸው።

«በኮርቻው የግራ ቦርሣ ውስጥ ሽጉጥ አለ። በታዘልኩት ሻንጣ ውስጥ ገቤና የምትመለከቱት ጥራጊ አለ። ይሁን እንጂ ወዳጆችህ ስለሆንኩ አንዳቸውንም የመጠቀም ሃሣብ በውስጤ የለም»

ሰውዬው የሆነ ነገር አጕተመተመና ከጓደኞቹ አንዱ የፈረሱን ልጓም እንዲይዝ ምልክት ሰጥቶ፣ ከኪሱ መሃረብ በማውጣት የጆን ባፕቲስትን ዐይኖች አሰራቸው። መንገዱን ይዘው ሽቅብ ተራመዱ። ልጁ ግን አሁንም ፈረሱ ላይ ሆኖ የኮርቻውን ቀዳማይ አጥብቆ ይዟል። ጆን ባፕቲስት፣አይኖቹን እንደታሰረ በአንደኛው ሽፍታ ትከሻ ላይ እጁን በማሳረፍ እየተመራ ይራመዳል። በዚህ ዓይነት በአይኖቹ ላይ የታሠረው መሃረብ ሳይፈታለት ለግማሽ ሰዓት ያህል ተጓዙ። መሃረቡ ከአይኖቹ ላይ ሲፈታለት፣ ጆን ባፕቲስት ዙሪያውን በቋጥኞችና በሰው ሰራሽ

ዋሻዎች መሃል መሆኑን ተመለከተ። ጊዜው መሸቶ ስለነበረ በደረሱበት ወታደራዊ ሠፈር ላይ ሰባት ወይም ስምንት በሚሆን ቦታ እሣት በርቶበታል። ጥላ የመሣሰሉ ሰዎች፣ ክስልስል ባሉት ባለሦስት እግር የማብሰያ ምንቸቶች ዙሪያ ተፍ ተፍ ይላሉ። ራቅ ብሎ ባለው አነስተኛ እሣት አጠገብ የተቀመጠው ሰው፣ ጆን ባፕቲስትን ከርሱ ፊት ለፊት ባለው ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ጋበዘው።

«እና» አለ ሰውዬው «ከሶውቢደራን መምጣትህ ነው? ለመሆኑ ከኛ አንዱ ነህ?»

ሰውዬው፣እየተናገረ፣ ጭራሮ አንስቶ በመሰባበር አንድ በአንድ ወደሚንጣጣው እሣት ይወረውራል። ሰውዬው፣ረዥምና አጥንታም ፊትና ብሩህ ዐይኖች አሉት። ከረሃብ፣ ከድካምና መከራን ከመሸከም ልማድና መልሰውም በሌሎች ላይ ጉዳት በማድረስ በዚህ አካባቢ ያሉት ሰዎች ሁሉ ተመሣሣይ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ሰዎቹ፣ እንደ ፍጡር መኖር ሲችሉ ነገር ግን እንደግለሰብ የመቆጠር ዕድል በመነፈጋቸው እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሕይወት ውስጥ ኖረዋል።

ወደዚህ አካባቢ ምን እንዳመጣው ጆን ባፕቲስት ገለፀላቸው። ምንም እንኳ የርሱ ታሪክ ረዥም ቢሆንም ከዚህ ሁሉ ውስጥ ዠረሚና እርሱ በቅርቡ ከካይሮ መመለሳቸውን የሚያመለክተውን ክፍል በአጭሩ ተረከላቸው።

«ስሜ ካቲናት ይባላል» አለ ሰውዬው

«በዚህ አካባቢ የምታወቀው ቢያንስ በዚህ ስም ነው። ዠረሚ ከኔ ይልቅ ትልቅ ስለሆነ አላውቀውም። ይሁን እንጂ ከረዥም ጊዜ በፊት ስለርሱ ሰምቻለሁ። እስከዛሬ በሕይወት በመኖሩ ዕድለኛ ነው። አባቶቻችን ምንም ምርጫ ስላልነበራቸው ሕይወታቸውን ማዳን ከፈለጉ ወደ ሩቅ ቦታ መሰደድ ግድ ነበረባቸው። እኛ ግን አሁን መዋጋቱን መርጠናል። ጊዜውም እየተለወጠ ነው። ንጉሡ እያረጀ ነው። አገሩም ሁሉ በርሱ ላይ እያተረመረመና እየተበታተነም ነው። በአሁኑ ጊዜ ከውጭ ሃይል ጋር ህብረት ለመፍጠር ጊዜው ስላይደለ ለነፃነታችን እዚሁ ሆነን እንታገላለን»

እንደ ጭሰማው ጥቁር ያለና ከአማፂያኑ አንዱ የሆነው ሰው፣ ለያንዳንዳቸው ቀጭን አጥሚት በእንጨት ወጭት አመጣላቸው።

የየድርሻቸውን ፉት እያሉ ስለካይሮና ስለሼርማይለስ ማውራት ጀመሩ። ላለፉት ሁለት ዓመታት እዚህ በጫካው ውስጥ በመኖሩ ከዓለም ዜናዎች ሁሉ መገለሉን ካቲናት ገለፀ። የርሱ



ትግል ዓለሞን ለማጥፋት ሣይሆን፣ በውስጧ እያንዳንዱ ሰው ሊኖርበት የሚችልበትን ቦታ ማዘጋጀት ነው። አስቸጋሪው ሕይወቱም ለሰው ዘር ፍፁም የሚስማማ አገልግሎት ማበርከት ነው።

«ነገ ጧት የግድ ሲየቴ ከተማ ውስጥ መድረስ ይገባኛል» አለ ጆን ባፕቲስት። ያለበትን ሁኔታና ያከናወነው ረዥም ጉዞ አሳሰቦት

«እዚያ ደርሰህ በመርከብ ለመሣፈር አቅደሃል?»

«አዎን። ወደ ጀኖአ የሚሄድ የእሣ አጥማጅ ጀልባ ላይ እሣፈራለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት

«አንተን በሚመለከት የንጉሡ መልዕክተኞች ለየአካባቢው ባለሥልጣኖች ሳያስታውቁ ይቀራሉ ትላለህ? እየፈለጉህ መሆን አለባቸው»

«መልዕክተኞቹ ከኔ በተሻለ ፍጥነት የሚጓዙ አይመስለኝም። የመጥፋቴም ነገር ወዲያውኑ የሚታወቅ አይሆንም። ከእንግዲህም በኋላ አራት ሰዓት ጊዜ አለኝ»

«እምም፣ ይህ አደጋ ያለበት ዕቅድ ነው። አሁን ከምትለው ቦታ ጀልባዎች በየቀኑ አይንቀሣቀሱም። እንበልና መርከበኞቹን በጉቦ ልትደልላቸው እየሞከርክ ሳለህ ትዕዛዙ ቢደርስስ? ወዲያውኑ ውግዘት ይደርስብሃል።»

«አውቃለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት በሃዘን፣ «ፖሪስን ከለቀቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ሳስብ የነበረው ይህንኑ ነበር። ዳሩ ግን ምንም ምርጫ የለኝም»

ካቲናት አጥሚቱን ጠጥቶ ከጨረሰ በኋላ፣ ወጭቱን በጣቱ መሩቅ ጀመረ።

«እኔ የምመክርህ ግን ጥቂት ሰዓታት እንድትተኛ ነው። እስቲ ራስህን ተመልከተው። በሚገባ ዕረፍት አላደረግህም። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ሰው ደግሞ ጥሩ አይሆንም። ከነዚያ ዋሻዎች ወደ አንደኛው ሂድና እጉዛ ደራርበህ ለብሰህ ጥቂት ተኛ። ሠፈራችንን የምናፈርሰው ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ላይ ነው። እስከዚያ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ አንዳች ነገር ላሰናዳልህ እችል ይሆናል።»

ትኩሱን ሾርባ ከጠጣና በእሣቱ ዳር ዕረፍት ካደረገ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት ከባድ የመጫጫን ሁኔታ አጋጠመው። ሽሽት ከጀመረ ወዲህ የተኛው በጣም ለአጭር ጊዜ ሲሆን፣ በዚያም ሁኔታ ላይ እንኳ ንቁ ስለነበረ እንቅልፉ በከፊል ነበር። የካቲናትን ምክር ለመቀበል

ወስኑ። ገና ጋደም ከማለቱ ካልተፋቀው አንዛ በሚወጣው የሚሰነፍጥ ሽታ በስተቀር፣ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጐ ወሰደው።

ካቲናት በገባለት ቃል መሠረት ከለሊቱ አሥር ሰዓት ላይ ቀሰቀሶ አነቃው። የሆኑ ልብሶች አመጣለትና የለበሰውን አውልቆ እንዲቀይር ነገረው። አሁንም ገና እንደተጫጫነውና ንቃቱ በከፊል ቢሆንም፣ መንገደኛው አሮጌ ልብሶቹን አውልቆ ከሃር የተሠራና እጅጌው በጥልፍ ያጌጠ ለርሱ ግን በሚገባ የተስማማው ልብስ ለበሰ። ከዚያም በትንሽ የሚሰሩበት ሁለት የቦት ጫማዎችን አጠለቀ። በዚህ ላይ ሰፊ የሱፍ ኮፍያና ባለ ሶስት ማዕዘን ባርኔጣ አደረገ። በዚህ በሚያንፀባርቅ አለባበሱ በቅርብ ባለው እሣት ዙሪያ ወደ ቆሙት የሰዎች አጀብ፣ ጆን ባፕቲስት ሄደ። በነዚያ ሰዎች መሃል ካቲናት አለ። የማለዳው ፀሎት አጭርና ክልብ ሲሆን፣ ሁሉም እናታቸው ባዶ ነበር። ከዚህ በኋላ እያንዳንዳቸው ከማታው ሾርባ አንዳንድ ወጭት ተቀበሉ። ሾርባው ዛሬ የባሰ ውሃ ሆኗል። ካቲናት፣ ፖንሴን ጠርቶት ከጐኑ እንዲቀመጥ ጠየቀው።

«ከሶስት ቀናት በፊት በአቪየስ ጐዳና ላይ ተዋጊዎቻችን አንድ ወጣት የመሣፍንት ዘር ተከትለው ጥለው ነበር። ሰውዬው፣ እሰ አንዳች አጀብ መጓዙ ትክክል አልነበረም። ሰዎቻችን እጅግ በጥንቃቄ የፈፀሙት ሥራ ስለነበረ በልብሶችህ ላይ አንዳችም የደም ምልክት የለበትም። የሰውዬው ሰነዶች እኒሁልህ»

አንዲት ትንሽ፣ቀይ፣ የሥራ ድርሻን የምትገልፅና ሀ. ብ የሚል የወርቅ ማህተም ያለባትን ወረቀት ለጆን ባፕቲስት ሰጠው።

«ሰውዬው፣ ጦር ሁራዊቱን በመቀላቀል መከራችንን የሚያሣየን ጀብደኛ ወጣት ነበር። የሃይማኖታቸውን ደህንነት በመጠበቅ ሽፋን ስም አንዳችም ነገር ሳይዙ፣ ለዘረፋና ለዝናቸው መገንቢያ ሃብት ለመሰብሰብ ይመጣሉ። ከነርሱ አንዱ ነህ ተብለህ ባለመጠርጠህም ዕድለኛ ነህ። እርግጥ ነው፣ አንተ ሁለመናህ በጭቃ ቦክቷል። እነርሱ ግን በአጠቃላይ ለልብሶቻቸው ይጨነቃሉ። እነዚህ ሰዎች ለኛ ታላቅ ክብር የሚያደርጉልን ይመስልሃል? ሊገድሉን ሲመጡ ውድና ያጌጡ የክት ልብሶቻቸውን ለብሰው ነው»

ጆን ባፕቲስት የቆዳውን እሽግ ከፈተው። በውስጡም የሟቹ ሰው ሰነዶች አሉበት። ስሙም ሁፌስ ዴ ቫውዴሶሬስ ይባላል። ሰውዬው፣ የልዑል ዴ ኮንቲ ቤተሰብ ሲሆን፣ ልዑሉም፣ የኒየም ጠቅላይ አገር ገዥ እንዲሆን የድጋፍ ደብዳቤ ዕፎለታል። ሰውዬው፣



ከፖንሴ ጋር ቢበዛ ጥቂት ወራት ታላቅ ወይም ታናሽ ቢሆን እንጂ ዕድሜው ተመሣሣይ ነበር።

«ፈረስህን ልትጠቀምበት ትችላለህ። እዚህ ያሉ ፈረሶች ጋሪ ጐታቾች ስለሆኑ ከአዲሱ ደረጃህና ሕይወትህ ጋር አይመጣጠኑም። በሌላ በኩል እነዚህ ሰነዶች እስካሉህ ድረስ ማንም ቢሆን ችግር አይፈጥርብህም። የመጀመሪያውን የጉዞ ምዕራፍህን፣ ከአቪየስ በስተምስራቅ በኩል ሄደህ አጭር ርቀት የተጓዝክ በማስመሰል ፈረስህን ቀይረው። ፈረሶቹ ተወዳዳሪዎችህ በዚህ መንገድ አይሄዱም፣ አንተንም ለመጠርጠር ምንም ምክንያት አይኖራቸውም። ከዚያም ወደ ማርሴይ ተሻገር። ማርሴይ ትልቅ ወደብ ነው። እዚያ ማንም ልብ ሳይልህ በርግጠኛነት ጀልባ ታገኛለህ። ጥይቶቻችን በጆሮ ግንዶቻቸው ላይ ማፏጨታቸውን ሲሰሙ፣ እነዚህ ትንንሾቹ ጀግኖች የመርከቦቻቸውን ፊት ወደ ምስራቅ ሜዲተራኒያን በማዞር፣ ዕድል ሃብታቸውን እዚያ ለመፈለግ መሞከራቸው የተለመደ ነገር ነው።»

ቀኑ እየደበዘዘ፣ ብርሃንም ጭራሯቸው ከሚታዩ ቅርንጫፎች ላይ እየነገሠ ነው። ሰዎቹ፣ እሣቶቹን ሁሉ በመረጋገጥ ካጠፉ በኋላ፣ ሻንጣዎቻቸውን በየትከሻዎቻቸው ላይ ተሸክመው፣ እንደደረጃቸው ቅደም ተከተል ተሰልፈው፣ መሣሪያዎቻቸውን አቀባብለው ተነሱ። ጆን ባፕቲስትም፣ ፈረሱን እየሣበ አንድ በተፈጥሮ እርከን መሰል ሰጥ ያለ ጉብታ እስኪደርሱ ድረስ አብሯቸው ተጓዘ። ከዚህ ጉብታ ላይ ሆኖ፣ ማንም ሰው ከርቀት የሚታየውን ትልቅ ጥቁር ደንና በስሱ የገረጣ የሚመስለውን የሸለቆውን መስመር ይመለከታል። በፖንሴና በካቲናት መካከል ረዘም ያለ መተቃቀፍ ከተከናወነ በኋላ የየራሣቸውን የተለያየ መንገድ ጀመሩ። ጆን ባፕቲስት፣ ፈረሱ ላይ ከወጣ በኋላ በለማያዊው የንጋት ብርሃን ውስጥ፣ ይህንን ወደፊት የሰው ልጅ የነፃነት ምልክት የሆነውን ቢማም፣ ጐስቋላና የሚንቀጠቀጥ ጓድ ለመጨረሻ ጊዜ ተመለከተው። ከእነዚህ የደፈጣ ተዋጊዎች ብዙዎቹ በነተቡት ልብሶቻቸው ላይ ዘርፋፍ ያለ ሸሚዝ ለብሰዋል። ይህ ደግሞ ምናልባት እርስ በርሣቸው ለመተዋወቅ እንዲረዳቸው ተብሎ ሣይሆን አይቀርም። ለሚለያቸው ጆን ባፕቲስት፣ ጦሮቻቸውንና ጐራዴዎቻቸውን ከፍ አድርገው በማንሣት ሰላምታ ሰጡት። የእግር መንገዱን ይዞ ቁልቁል ሲጓዝ፣ ከትናንት በስቲያ ገድለውት ዛሬ ደግሞ በሕይወት እንዲኖር ያመጡትን ሰው ቅርፅ የተዋጊዎቹ ዐይኖች ተከተሉት።

# 3

ወንድም ፖስኳልና ከኢጣሊያ በቅርቡ የመጣው ባርቶሎሚዎ የተባለው የተጠመቀ ክርስቲያን፣አጥር ግቢው ውስጥ ሆነው ይጠብቁ ነበር:: ከዚህ ባለፈ መዳፈር ግን አግባብነት አይኖረውም:: ቂማሙ ካፑቺን፣ ብቻውን እንደጀብራ በተገተረ አንድ የተምር ዛፍ ዙሪያ ዞሩ:: በዚህ ኦና የሆነ የተጠረገና የመታከሻ ቀዳዳዎች ካሉት ረዥም ግድግዳዎቹ አጠገብ ሆነው የሚገርም ነገር አሰቡ:: ይህ የወህኒ ቤት ያህል ነው:: በተለይም ወደ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን በኩል ያሉት መስኮቶቹ ሁሉ በጠንካራ የብረት ፍርግርግ የታጠሩ በመሆናቸው ይበልጥ እስር ቤት ያስመስላቸዋል፣ እያሉ ያስባሉ:: በከፊል በተከፈተው በር በኩል ባለፉ ቁጥር፣ በወፍራም ድምፅ የሚዜሙ የዳዊት መዝሙሮች ወደ ጆሮአቸው ሲደርሱ፣የለመዱት የእጣን ሽታ ወፍራሙን አፍንጫቸውን ይወጋዋል::

በካቶሊካውያን ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ድባብ ፍፁም የተለየ ዓይነት ነበር:: በእያንዳንዱ መስኮት ላይ ከዳር እስከ ዳር ለተገጠሙት የጣውላ መከለያዎች፣ ውስብስብ ሆነው ለተሠሩት የመስኮት መጋረጃዎች፣ መከለያዎችና ተካፋይ ግድግዳዎች ምስጋና ይድረሳቸውና የቤተክርስያኑ ቅድስተ ቅዱሳን ሙሉ በሙሉ በጨለማ ተውጧል:: ይሁን እንጂ ደብዛዛው ቀይ የሻማ መብራት፣ በሰላም ተሰብስበው እዚህም እዚያም በተቀመጡ ምዕመናንና ዕቃዎች ላይ እንዲሁም በጥላው ውስጥ በተንተን ብለው ባሉና በአዳኝ የሴባ አይኖች በሚታዩ የወርቅ የዝሆን ጥርሶችና የሉል ዕቃዎች ላይ በስስት ያበራሉ:: ኢብራሂም የሚባሉት ሶሪያዊ መነኩሴ ረዥም ሰዐት በሚፈጀው የቅብዓ ሜሮን ዝግጅት ላይ፣ ፖትርያርኩንና የተመረጡ ጥቂት ቀሣውስትን በመርዳት ላይ ናቸው:: ቅድመ ሁኔታ ከሚጠይቀ የተንዛዙ የፀሎት ሥነስርዓቶች በኋላ፣ ፖትርያርኩ ባለ ሁለት ጆሮ የእብነበረድ ገንቦውን ከፅላተ ሙሴው ላይ አነሱ:: ከዚህ ተከትሎ ትክክለኛው ቡራኬ ቀጠለ:: በመጨረሻም ከቅብዓ ሜሮኑ የተወሰነ መጠን እጀታ ባለው የሸክላ ብልቃጥ ውስጥ ተጨምሮ በቡሽ ታሸገ:: ሥራው ያበቃው አመሻሽ ላይ ነበር:: ፖትርያርኩ፣ የእምነበረዱን ገንቦ ይዘው፣ ወደዋናው ካቴድራል ወደ ሚያስገባው በታ ድረስ ሌሎቹ በሰልፍ ተከትለዋቸው ሄዱ:: እዚያ ሲደርሱ፣ ጭንቅላታቸው ማያቋርጥ የሚንቀጠቀጥባቸው የጥንታዊት ኮፕቲክ ካህን በሩን ከፈቱላቸው:: ብዙ እንዲጠብቁ የተደረጉት ወንድም ፖስኳል ቢናደዱም፣ ለኮፕቲኩ ጳጳስ ጥሩ ገፅታ አሳዩዋቸው:: እጅግ



ከፍተኛ የትህትና ታዛዥነት ባለው አገላለፅም ይህን የተከበረ ገንቦ ተቀብለው እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ በብራና ጠቅልለው አተሙብት:: ከዚያም በቁንጠኛ ዘዬ ተንበረከኩ::

«ይህ ቅብዓ ሜሮን በሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ወደ አቢሲኒያ ይጓዛል፣ ብፁዕ አባታችን» አሉ በአረቢኛ

ጳጳሱም፣ በደምበጃኑ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የቡራኬ የመስቀል ምልክት አሣረፉ:: ኢብራሂምም ከካፑቺኑ ጋር ትርጉም ያለው እተያይ ተለዋወጡ:: ወንድም ፖስኳል ኮንበስ አሉና፣ከባርቶሎሜዎ ጋር እየተንተቱ ግቢውን ቀስ ብለው በማቋረጥ ሁካታና ጫጫታ ወዳለበት ከተማ ዘልቀው ገቡ::

የኮፕቲኮች ቅዱስ ስፍራ በረዣዥም ቤቶች አዋሳኝ በሆነ ቀጭን መንገድ በኩል ያሣያል:: ከሞላ ጐደል በሁሉም ቤቶች ደጃፍ ፊት ለፊት፣ በነዳጅ የሚበሩ የፋኖሶች መስቀያዎች በአነስተኛ ነጋዴዎች ተሠርተው ቆመዋል:: መንገዱ እስከ አሁን ድረስ በሕዝብ የተጨናነቀ ሲሆን አላፊ አግዳሚው በጨለማው ምክንያት እርስ በእርሱ ይላተማል::

«ይህን ደምበጃን ያዘው:: ከኔ ይልቅ ያንተ ዓይኖች ይሻላሉ» አሉ ወንድም ፖስኳል ለአዲሱ ተጠማቂ::

ወጣቱ ወንድም፣ ይህን ብርቅ ጠርሙስ በፍርሃት ስሜት ተቀበለ:: በውሃ ከተከበበው ከኢስትሪያን የመጣው አገጫሙ ትልቅ ልጅ፣ ለመቀሰስ የመጣ ሲሆን፣ የአካል ጥንካሬ ግን አልነበረውም:: እጅግ አጥብቆ የሚፈራው ወላጅ አባቱ፣ ከልጆቹ አንዱን ለእግዚአብሔር አገልጋይነት ለመስጠት ፈልጐ ስለነበረ፣ ይህንኑ ልጁን መረጠው:: አባትዬው ይህን ልጁን የመረጠው ከልጆቹ ሁሉ ስስታም ስለሆነና ለመቀለብ ግን ብዙ የሚያስወጣው ስለነበረ ነው:: ከዚያም ወዲህ፣ ባርቶሎሚዎ፣የዕለቱ መቁነን የተትረፈረፈ በመሆኑ በጀግንነት እንደሚዋጋ ወታደር ጌታን በታማኝነት አገልግሏል::

«ልጄ፣ ያ መጥፎ ፖትርያርክ በወርቅ በተጠለፈው ካባው እንዴት ለመታየት እንደሚራመድ አየኸው!» ሲሉ እጆቻቸው ነፃ በመሆናቸው በሕዝቡ መሃል በትከሻቸው በዘፈቀደ እየተጋፉ ለመራመድና ቀልጠፍ ለማለት ያልቦዘኑት ካህን በመነጫነጭ ተናገሩ:: «ይህ ችጋራም፣ የቆንሲሉን የወርቅ ሣንቲም ልሰጠው ባልንቀሣቀስ ኖሮ . . .»

ባርቶሎሚዎ፣ ከሽማግሌው ዱካ ሳለመራቅ ከኋላቸው በቅርበት ሆኖ በመሮጥ ይከተላቸዋል::

«ስማኝ እስኪ» አሉ ወንድም ፖስኳል። «በርቶሎሚዎ? አንተ ወጣት ነህ። እነዚህ ኮፐቲኮች ዋጋ ቢሶች መሆናቸውን መማር አለብህ። ፍፁም ዋጋ ቢሶች ናቸው። አየህ? እነዚህን ሰዎች በልብሰ ተክህኗቸው ላይ ተመስርተህ የምትገምታቸው ከሆነ፣ በቀይ ክፋይ የማጠንት ዕቃዎቻቸው ላይ ተመስርተህ የምትመዝናቸው ከሆንክ፣ አንዳች ድንቅ ዕውቀትና ቁም ነገር ያላቸው ናቸው ብለህ ማመን ትጀምራለህ። በእውነቱ ይህ ስህተት ነው። የሁሉም ነገር ባለቤት ፓሻው ነው። እንዲጠቀሙበት እንኳ የሚፈቅድላቸው ፓሻው ነው። እነርሱ የለማኝ ያህል ምስኪን ድሆች ናቸው»

«እኛስ እንዲሁ ድሆች አይደለንም እንዴ?» ሲል ወጣቱ ካፑቹን እያስከለስ ጠየቀ። የምንኩስና ማዕረግ ለማግኘት ሲፈቀድለት፣ የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት እንደሚለምኑ ስዕለት ማድረጋቸውን ሲያውቅ በጣም ተደንቋል።

«ቢሆንም፣ እኛ እኮ ጳጳሣችን አሉልን። ይህ እንኳ አይታይህም?» አሉት ፖስኳል። «እውነት ነው፣ እኛም ድሆች ነን። ይሁን እንጂ፣ ይህ እኛ በአለም ውስጥ ላለን የተለየ ሥፍራ ዋናው መሣሪያችን ነው። እኛ እስካውቶች ነን። እኛን ተከትለው ፈረሰኞች፣ ባለ ጠመንጃዎችና ታላቁ ሠራዊት ይመጣሉ። ኮፕቶች ግን ከኋላቸው ምንም የላቸውም። እንዲያውም የቱርኮች ጉራዴ አንገቶቻቸውን ይቀላዋል። ይህ ሁሉ እያለ ለማስመሰል ሲሉ ቡራኬአቸውን እያቃሰቱ ሲያዝበንቡ ለአራት ረዥም ሰዓቶች እንድንጠብቃቸው ያደርጉናል»

ከመጀመሪያውም የባሰ ጠባብ የቁልቁለት መንገድ ውስጥ ገቡ። ጭለማው ድቅድቅ ሆኗል። ማንም ሌላ የሚጓዝ ሰው የለም። የከተማውን የጥበቃ ምሽግ ለማለፍና ወደ ገዳሙ በተቻለ ፍጥነት የሚያደርሣቸው አቋራጭ መንገድ ነው።

«አባቱ እባክዎ ይጠብቁኝ። ምንም ነገር አይታየኝም» አለ በርቶሎሚዎ።

«አንዱን እግርህን ከሌላው እያስቀደምክ በማፈራረቅ ተራመድ፣ አንተ ደደብ ዝሆን። ለመሆኑ በመንፈሣዊው ትምህርት ቤት ምንም አላስተማሩህም እንዴ?»

ወንድም በርቶሎሚዎ የሚችለውን ሁሉ አደረገ። ይሁን እንጂ በድንገት ቆም የመታፈን እሪታውን ለቀቀውና በፍርሃት መቀባጠር ጀመረ።

«ደጉ አምላኬ! አቤቱ ፈጣሪዬ! ምን በደል ፈፀምኩ። እኔስ ጠፋሁ። አቤቱ ይቅርታህን ስጠኝ። አምላኬ አድነኝ። አምላኬ፣ አምላኬ . . . »



ወንድም ፖስኳል በጭለማው ውስጥ እርምጃቸውን እንደገና ወደ ኋላ መለሱት

«አሁን እንግዲህ ምን ሆንክ?»

«ሰኔ ይዘኑልኝ፣ ስለክርስቶስ ሲሉ ይራሩልኝ!» አለ አዲሱ ተጠማቂ፣ በጉርበጥባጣው መሬት ላይ ተንበርክኮ። «ገንበው ወደቀብኝ»

«ታዲያ ተሰበረ እንዴ?»

«ወይኔ ጉዴ! አዎን፣ ወይኔ!እኔ በጠፋሁ»

ወንድም ፖስኳል በራሣቸው የቋንቋ ዘዬ ተራገሙ፡ ይህ ደግሞ ግልፅ ካልሆነውና ሲቋረጥ ካልቻለው መሃላው ጋር ሆኖ በርቶሎሚዎን ይበልጥ አስፈራው

«ለመሆኑ ከዚህ የባሰ ቀርፋፋና ጅላጅል ተፈጥሮ ያውቅ ይሆን?» ሲሉ ደመደሙ ።

ከቁጣ ይልቅ ይበልጥ ተናድደው

ልጁ ግን አሁንም ተንበርክኮ እየጮኸ ነው።

«እዚያው ላይ ተደፍተህ በመጮህህ አሁንም የበለጠ ጊዜ እያጠፋህ ነው። ይህን ያህል ቁም ነገር ስላልሆነ ተነስተህ ና። ለዚህ ይቅር ብልህ፣ ሰው አይደለሁም። አሁንም ሳስጠንቅቅህ፣ ለዕራት እንዳንደርስ ካዘገየኸን ደግሞ ከዚህ የባሰ እጣላሃለሁ»

«ግን እኮ ስለዚህ ቅዱስ ገንቦ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ» አለ የማታ እራት ነገር ሲነሣ እንባውን እየደረቀ በመበረታታት።

«እጅግ በጣም ቀላል ነው። ነገ ጧት ከገዳሙ ባሻገር ካለው መንገድ፣ ከአረብ ግሮሰሪ ሄደህ ከሁለት አብረቀራቂ አዝራር በላይ የማያወጣ የአጌሽ ዘይት ትገዛለህ»

«እናም እንዲባረክ ወደ ፖትርያርኩ እንወስደዋለን»

«እንዲባረክ!» አሉ ወንድም ፖስኳል የመንፈሣዊውን ተማሪ ጆሮ ለቀም አድርገው እየጠመዘዙት። «ለመሆኑ ይህን የመሰለ ደደብ ተፈጥሮ ያውቅ ይሆን እንዴ! እንዲባረክ ይለኛል! ጧት ወደ ማምለክ እየተሸጋገርክ ነው እንዴ?»

«የለም! የለም!» ሲል በርቶሎሚዎ ተነጫነጨ

«ታዲያ የነዚያ የተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ቡራኬ ምን ይፈይዳል ብለህ ነው? ንገረኝ እንጂ? ከነርሱ ጋር የምንጓዘው ወደ አቢሲኒያ ሠርገን ለመግባት ስንል ነው። በመሠረቱ

መለወጥ ያለብን እነርሱን ነው፡፡ የተነሳቢጦሽ አይደለም፡፡ ገባህ? ቅብዓ ሜሮኑን የተረጋገጠና እውነተኛ ነው ለማለት ብራናው አለን፣ የግሮሰሪውም ዘይት እያንዳንዷን ተፈላጊ ነገር ያሟላል» ይህን ተናግረው የቅብዓ ሜሮኑ መያዣ የነበረውን ገንቦ ስብረባሪ ለመበታተን ወንድም ፖስኳል በነጠላ ጫማቸው መሬቱን ጠራረጉት፡፡ ከዚህ በኋላ ስለበርቶሎሜዎ እምብዛም ሳይጨነቁ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ በርቶሎሜዎም አንድ እጁን ጀርባው ላይ አድርጎ እየተነፋረቀ ተከተላቸው፡፡

ጆን ባፕቲስት ከሄደ በኋላ መሰላቸት የሚገድል ቢሆን፣ ሙራድ ይሞት ነበር፡፡ በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ሰፈር መጨረሻ ጥግ ላይ ባለው ቤቱ በብቸኝነት ኖረ፡፡ ለመኖሪያው የሚሆነውን በአብዛኛው የሚያገኘው ከፈረንሣይ ቆንስላ ቢሆንም አቢሲኒያውያኑ ባሮቹ ስለተወሰዱበት፣ በግብፃውያንና በአውሮፖውያን ነጋዴዎችም ገሸሽ ስለተደረገ፣ ብቸኛው ጠያቂው ሜትር ዠረሚ ነበረ፡፡ በሜትር ዠረሚ በኩል አንዲት አረባዊት አገልጋይ መቅጠር ችሎ ነበር፡፡ ሴትዮዋ ከድጃ የምትባል በጣም አሮጊት፣ ከሞላ ጎደል ለመኖር ስትል በግድዋ የምትሠራ ነበረች፡፡ ሙራድ ዘንድ በተቀጠረች በሁለተኛው ቀን አንድ ወደል እጅ በሰፊው የናይለን ቀሚሷ ስር ሲነካት ተሰማት፡፡ እንዲህ ባለው ከስነስርዓት ውጭ በሆነ ድርጊት ለብዙ ሴኮንዶች ተገርማ ከቆየች በኋላ ወዲያውኑ ወደ ደፋሩ ሰው መለስ ብላ አይመቱ ምት ጥፊ ፊቱ ላይ አሳረፈችበት፡፡ ከዚያም ተፋችበትና የርግማን መዐት አከታትላ ወረወረችበት፡፡ ሰላም ከሰፈነ በኋላ፣ እሷም ዳግመኛ ትንኮሳ ሳይገጥማት ስራዋን ቀጠለች፡፡ በዚህ ጉዳይ የተነሣ ሙራድ በዚህች አሮጊት ሴት ላይ አንዳች የቅድስና ፍርሃት አደረበት፡፡ ከድጃን በተመለከተ ግን ይህን የመሰለ የሚያስቆጣ ተግባር ተፈፅሞባት ዝም ማለቷ ባለውለታ ያደርጋታል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን የሰውዬውን የመንካት ስሜት ከቁብ ሳትቆጥረው ቀረች፡፡ ይህ ምናልባት ሰውዬው፣ እርስዋን እንደሚፈልገው ዕቃ አይቶኝ ይሆናል በሚል ሙራድን ትታ ሳትሄድ ቀረች፡፡

በነዚህ ረዥም ጣምንታት አርመናዊው ሌላ ጓደኛ አልነበረውም፡፡ ብዙ ጊዜ በካይሮ ጠባብ ጉዳናዎች ላይ ሰርስ ሲባል ከሚደረግ ደስታ በኋላ በመዝናናት መልክ በከንቱ ሲራመድ ይታይ ነበር፡፡ ክረምት ሲገባ፣በቤቱ ውስጥ ታሽጉ፣በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተ



የእንጨት ደቃዎችን በጣቱ ሲቆጥር ይውላል፡፡ አልፎ አልፎ፣ ሜትር ዠረሚ ጥቂት ቴምር ያመጣለታል፡፡ ሙራድ፣ ቴምሮቹ የውስጥ ጠንካራ ፍሬአቸው እስኪለሰልስ ድረስ ሲመጣቸው ይቆይና በመጨረሻም በቅሬታ ስሜት ይውጣቸዋል፡፡

ሙራድ፣ ካይሮ ውስጥ ተስፋ ቆርጠው ከሚኖሩትና ስለ ፖንሴ ለመስማት ወሬ ከሚናፍቁ ቡድኖች ውስጥ ነበር፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ሦስቱ አቢሲኒያውያን ሲመለሱ እጅግ ተደንቆ ተመለከተ፡፡ አሌክሣንደሪያ ውስጥ የደረሰባቸውን መጥፎ ዕድል ሰምቶ ስለነበረ፣ ዳግመኛ እንደሚያያቸው ጨርሶ አስቦ አያውቅም፡፡ ነገር ግን ሦስቱ ምስኪን ጥቋቁር ሰዎች፣ አንድ ጊዜ ለእስልምና ሃይማኖት ቃለ መሃላ ከፈፀሙ በኋላ፣ ለነፍሣቸው ያን ያህል ክባድ ሃላፊነት አለብኝ ይል በነበረው ሕዝባዊ ቡድን እንደ ዕድላቸው ተብለው ተለቅቀዋል፡፡ ለብዙ ቀናት ምግባቸውን ለማግኘት እየለመኑ ሲንከራተቱ ከቆዩ በኋላ፣ ከሁሉም ታላቅ የነበረው ባረያ፣ ወደ ካይሮ ተመልሰው ሙራድን ለማግኘት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ያግባባቸዋል፡፡ ይህ የቀድሞው ጌታቸው ቢያንስ ቋንቋቸውን የሚናገርና በታማኝነትም የሚያስተዳድራቸው ነው፡፡ በመሆኑም ሥርዓት ባለው ሁኔታ ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ በቀን አምስት ጊዜ ፀሎት ስለሚያደርሱ ማንም ያስቸገራቸው አልነበረምና በአጭር ጉዞ ካይሮ ደረሱ፡፡ ከዚህ በኋላ በቀድሞው ቤታቸው የነበራቸውን ሥራ ቀጠሉ፡፡ አሮጊቷም እዚያው ለመቆየት ወሰኑ፡፡ ሜትር ዠረሚም ያገኛቸው እዚሁ ሲሆን እንዳያቸው በጣም ተደንቆ ነበር፡፡

«ቱርካውያን እንዲሆኑ ተገድደው ነበር ሲባል የሰማሁ መስሎኝ ነበር» አለው ለሙራድ

«ልክ ነው»

«ምስኪኖቹ እንስሶች ክፉኛ መበሳጨት አለባቸው»

«እንደ እውነቱ ግን አልተበሳጩም፡፡ ሙስሊም ሲሆኑ ይህ ሁለተኛ ጊዜያቸው ነው»

«ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?»

«እነዚህ ሰዎች የንጉሡ የጦር እስረኞች እንደነበሩ አትዘንጋ፡፡ በምርኮ የተያዙት ከአቢሲኒያ ነሉት ሃይማኖት የለሽ ጐሣዎች ነው፡፡ የሚያመልኩት ላሞችን፣ ዛፎችንና ተራሮችን ነው፡፡ ከውጭ የሚመጣ ሠራዊት ሲወርራቸው ሁልጊዜም የአሸናፊውን ወራሪ ሃይል ሃይማኖት ይቀበላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በመጀመሪያ ጊዜ የሲናር ሕዝቦች ነበሩ፡፡ የሲናሩ

ንጉስ፣ ለአላህ እንዲሰግዱ አስገደዳቸው፡፡ ከዚያ በኋላ በኛ ንጉሥ ነገስት ተያዙና የእየሱስ አማኞች ሆኑ፡፡ ይኸው አሁን ደግሞ ከመጀመሪያው እምነታቸው በፊት ወደነበሩበት ቦታ ተመልሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ በልባቸው እነዚያኑ ተራራዎቻቸውን ወይም እኛ ምንነታቸውን የማናውቃቸውን ነገሮች ማመናቸውን እንደቀጠሉበት ርግጠኛ ነኝ»

ሜትር ዠረሚ ሃሳቡን አቢሲኒያውያን ተመለከታቸው፡፡ በመመለሣቸው ደስተኞች ናቸው፡፡ በሩ አጠገብ ቁጢጥ ብለዋል፡፡ አሁንም ክስተር እንዳሉና ለመረዳት አዳጋች እንደሆኑ ናቸው፡፡ ትክክለኛውና ለራስ ከፍተኛ ክብር የመስጠትን ጉዳይ ልታስቶመው የማትችለው የተቃውሞ መግለጫ ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ እነርሱ ህያው ምስክሮች ናቸው፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ የፖንሴን የውርደትና በቅርቡ ለፍርድ እንደሚቀርብ የሚገልፅ ዜና ሙሴ ዶ ማይሴ ተቀበለ፡፡ ወዲያውም ከዚህ ወር መጨረሻ በኋላ የሚያደርግለትን ድጋማ ሁሉ እንደማያቋርጥበት ለሙራድ አስታወቀው፡፡ የዚህን ውሣኔ ለማስታወቅ፣ ሙሴ ማቼ ወደ አርመናዊው ዘንድ መጥቶ ጥቂት ተጨማሪ አስተያየቶችንም አክለበት፡፡ የዚህ ብልግና የተቀላቀለበት አስተያየት ዓላማም ሙራድ ወደ አገሩ ከመመለስ ሌላ ጥሩ ነገር እንደሌለው የሚገልፅና ከርሱ ባህርይ አኳያ ይህ መግለጫ አንዳች ትርጓሜ ይኖረዋል የሚል ነበር፡፡

ሙራድ፣ በቀጥታ ወደ ሜትር ዠረሚ ቤት ሲገሰግስ ደርሶ፣ አደጋ ላይ መውደቁን እያሰቀሰ ነገረው፡፡ የመጀመሪያው ሃሣቡም በማህበረሰቡ ውስጥ በሚገኝ አንድ ነጋዴ ዘንድ በምግብ አዘጋጅነት መቀጠር ሆነ፡፡ በዚህ ችሎታው አሌፖ ውስጥ ሠርቷልና ካይሮ ውስጥ ለምን አይሠራም?

ይህ አስተሣሰቡ ከንጉሠ ነገስቱ የተቀበለውን የአክብሮት ተልዕኮ እንደማንኳሰስ እንደሚሆንበት ዠረሚ አስረዳው፡፡ በሌላ በኩል ጆን ባፕቲስትን ማዳን የሚቻልበት ዕድል እንኳ ቢኖር፣ ይህ ሊሆን የሚችለው የታሪኩን እውነታ በተቻለ መጠን ጠብቆ በማቆየት ነው፡፡ ሲመለስ አምባሳደር ይዞ እንደሚመጣ ቃል ገብቷል፡፡ ስለሆነም የተባለው ሰው፣ወጥ ውስጥ ተዘፍቆ ሊገኝ አልቻለም ከማለት የተሻለ ይሆናል፡፡

በርግጥ ዠረሚ ለሙራድ ብልህ ምክር ለመስጠት የሚችል አይደለም፡፡ እርሱም ቢሆን ቬርሣይለስ ውስጥ በርግጥ ምን እንደተከናወነ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ አይደለም፡፡



በሌላ በኩል፣ ሁኔታዎች አዲስ መስመር የመያዛቸውን፣ ማለትም ዱ ሮውሌና ብዛት ያለው ህጋዊ ኤምባሲ መሄዱ እንደማይቀር በመግለፅ የሚረብሽ ዜና ፍራንቾይዝ ነግራዋለች፡፡ ምስኪኑ ዠረሚ ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም፡፡ ፖንሴን የሚከላከል ቢሆንም ጓደኛው ውርርዱን እንደተሸነፈ በፍፁም አምኗል፡፡ ሙራድ ክብር ያለው የንጉሡ መልዕክተኛ ሆኖ እንዲቆይ አደፋፍሮታል፡፡ በሌላ በኩል ቆንስላው ለአርመናዊው ምንም ተቀባይነትን ስላልሰጠው የራሱን ተልዕኮ እያደራጀበት ነው፡፡ በአጭሩ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ለመስጠት ያልቻለበት ትልቅ ፈተና ውስጥ ወድቋል፡፡

ይህ ሁሉ እየሆነ ግን የመድሃኒት ቅመማና ዝግጅት ሥራውን ባለማቋረጥ፣ በፖንሴ የተፃፉትን የህክምና ትዕዛዞች እየሞላ ይጠቀምባቸዋል፡፡ እንዲያውም ከሙፍቲዎች ፍላጐት ውጭ፣ አስፈሪው አዲሱ ፓሻ መሃመት ቤይ፣ ተቀብሎት በምስጢር የርሱ መድሃኒት አዘጋጅ አድርጐታል፡፡

ሌላው አስቸጋሪ ነገር ደግሞ ፍራንቾይዝ በርሱና በቆንስላው መካከል ባለማቋረጥ እንደ መልዕክተኛው ጥልቅ ትላለች፡፡ ስለርስዋ ያለው ስሜት ከቀን ወደ ቀን እያየለና እየበረታ ቢመጣም፣ ይህንኑ በግልፅና በታማኝት ሊገልፅላት መቻል አለመቻሉን ርግጠኛ አይደለም፡፡ አሊስ፣ ፖንሴን ለማግኘትና ለማዳን ስትል፣ ገዳም እገባለሁ በሚል ሰበብ ወደ ፈረንሣይ ለመሄድ ያቀደችውን ስትነግረው፣ ወጣቷን ሴት ነፃ በማድረጉ ጉዳይ ላይ እንዲረዳትና በጉዞዋም ላይ እንዲያጅባት ስትጠይቀው፣ ሊገጥም የሚችለውን ችግር ሁሉ ቢገምትም በመጨረሻ በሐይ የምትወጣ ያህል ስሜት ዠረሚ ተሰማው፡፡

በመጨረሻም ሲገነዘብ፣ ሲንቀሣቀስና ሲታገል ብቁ ሆነ፡፡ እንደርሱ በመከራ የተገረፈን ሰው ከዚህ ካለመንቀሣቀስና ከመደበቅ የባሰ የሚከፋና ሊስማማው የማይችል ነገር የለም፡፡ ከዚህ በኋላ ጫማዎቹን ወለወላቸው፣ ኮራዶውንና ሸጉጡንም አፀዳቸው፡፡ በደስታም ዘመረ፡፡

አዲሱ እቅድ፣ አንዱን ሰው ከጨዋታው ውጭ አደረገ፡፡ ይህም ሰው ሙራድ ነበር፡፡ ዠረሚ ትዕግስትን እንዳልሰበከው ሁሉ፣ በጣም በችኮላና ትህትና እንኳ በጐደለው ሁኔታ ሃሣቡን ቀይሮ፣ ልክ ቆንሲሉ እንዳደረገው ሁሉ ወደ አቢሲኒያ እንዲመለስ መከረው፡፡ ይህንንም ለማሣካት የሚያስችለውን ሁሉ ለማድረግ፣ ጥቂት የጭነት አጋሰሶችን ሊገዛለትና ጥቂት ገንዘብ ሊሰጠው እንደሚችል ሁሉ ሃሣብ አቀረበለት፡፡

ነገሮች ሁሉ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉና ሙራድም የቱን መንገድ መያዝ እንዳለበት ሳይወስን በፊት፣ ከዕለታት አንድ ቀን ማለዳ ሁለት እንግዶች ሰዎች ወደ ቤቱ መጡ።

ሁለቱም ሰዎች ፈረንሣውያን ሲሆኑ፣ ከዚህ በፊት ማንም ሰው በማህበረሰቡ ሰፈር አይቷቸው አያውቅም። ሰዎቹ ባለፈው ቀን መምጣታቸውን ይናገራሉ።

«ክቡር ወእም ክቡራን ጌታ ሙራድ፣ የኢትዮጵያ አምባሣደር እርስዎ ነዎትን?» ሲል ከሁለቱ ጐብኚዎች ረዥሙ ተናገረ። ሰውዬው፣ አርባ አመት የሚሆነው ቀጭንና ሴላው ቀርቶ ሲናገር እንኳ መልኩን ለይቶ ይህን ይመስላል ሊሉት የማይችሉት ነው።

«መቼም ሌላ ሰው የለም» አለ ሙራድ ከተቀመጠበት እየተነሣ። እንዲህ ባለ ደስ የሚል አክብሮት ማንም ሰው ሣይጠራው ረዥም ጊዜ አልፎታል። «እሺ የሆነ ሆኖ ምን ልርዳችሁ?»

«የመጣነው ከፖለስታይን፣ ማለትም በርግጥ ከእየሩሳሌም ነው። እኔ ሁብርት ዴ ሞኒሃውት ስባል ይህ የሥራ ባልደረባዬ ደግሞ ግራጕሪ ሪፋው ይባላል። ሁለታችንም የሣይንስ ሊቃውንት ነን። እርሱ ባልደረባዬ የጂኦግራፊ ሊቅ ሲሆን እኔ የስነ ሕንፃ ንድፍ ጠቢብ ነኝ» አለ ቀለል የሚለው ሰው በተረጋጋ ሁኔታ

ከመጀመሪያው ጐብኚ ይልቅ ወጣት የሚሆነው ሁለተኛው ሰው፣ በባልደረባው ንግግር መስማማቱን ለማሣወቅ ጭንቅላቱን በአዎንታ አነቃነቀ። ይህ ሰው እጅግ ያልተለመዱ ከሚመስሉት፣ የገረጡና ከሞላ ጐደል ነጭ ከሆነው በሙራድ ላይ እንደ ሁለት የሚያብረቀርቁ የሸክላ ዝርግ ሣህኖች ካነጣጠሩት አይኖቹ በስተቀር ሊታወስ የሚችል ምንም ነገር የለበትም።

«ከአቢሲኒያ ቤተመንግስት የተላኩት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሣደር መኖሪያቸውን ካይሮ ውስጥ መመስረታቸውን ሰማን። ስለዚህም የክቡርነትዎን ድጋፍ እናገኛለን በሚል ተስፋ ወደዚሁ መጣን»

«እቅሜ የፈቀደውን ሁሉ አደርጋለሁ» አለ ሙራድ፣ግብዝነቱ አንገሽቶበትና እውነት ተነግሮ ከሆነ በስብሰባ ላይ እንኳ ሳይቀር ጀርባውን ሲያዞርበትና አንገቱን ሲመልስበት የነበረውን የሙሴ ዴ ማይሌ ሁኔታ እየታሰበው።

«አስቀድመን ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን። በጣም እናመሰግናለን ክቡር ሆይ» አለና የቻይና ዓይን ያለው ሰውዬ እንዳደረገው ጥቂት ዘግየት ብሎ ጐንበስ ብሎ ተናገረ።



«በእስፖኝ የሮያል የሣይንስ አካዳሚ ድጋፍ ተሰባስበን የመጣን የአሣሽ ቡድን አባላት ነን» አለ ቃል አቀባዩ። «ከሣምንቱ ማብቂያ በፊት ሌሎች አራት ሳይንቲስቶች እዚህ ደርሰው ይቀላቀሉናል። እነርሱ የተነሱት ከአውሮፖ ነው። ሆኖም አሌክሣንደሪያ መድረሣቸውን የሚገልፅ መልዕክት ልከውልናል። ስድስታችንም እርስዎ ወደሚወክሏት አገርዎ ወደ አቢሲኒያ እንሄዳለን። ስለዚህም ክቡርነትዎ ስለአገርዎ ንጉሡ ነገስት ልናውቅ የሚገባንን ሁሉ እንዲያሣውቁን በአክብሮት እንጠይቃለን»

ሙራድ፣ በግራ እጁ ይዟት የነበረችውን የትንሽ አበባ አንጓ ጭምቅ አደረገ። አምላኬ ሆይ በመጨረሻ ደረሰክልኝ ሲል አሰበ።

«ጌቶቼ፣ በተልዕኳችሁ ላይ እናንተን መርዳት ለኔ ታላቅ ደስታ ነው» ሆኖም ዓላማችሁን ልትነግሩኝ ይገባል። ምናልባት ንጉሴ፣ ጌታዬ የውጭ አገር ሰዎች ወደ ግዛታቸው እንዲገቡ ያወጁትን እገዳ አታውቁም ይሆናል» አለ በሃዘን።

«ክቡር ሆይ እናውቃለን። የኛ ተልዕኮ ለዕውቀቱ ሲሉ በመጓጓት እንደሚጓዙ ሰዎች ዓይነት ብቻ ነው። ለምሳሌ የጂኦግራፊው ሊቅ፣የዋናዎቹን ወንዞች መነሻ ያገኛል፣ ዶክተሩ፣ ማለቴ በመሃከላችን አንድ ሃኪም አለን፣ እርሱ በዚያ አገር ያለውን እብይ የሕመም ዓይነት ይገልፃል። እያንዳንዳችን በተፈጥሮ በዕምሯችን ያለውን የማወቅ ጉጉት ለማርካት በአዲስ አገር ውስጥ የምናገኘውን ለመረዳት እንጥራለን»

«ወርቅ ፍለጋ መቼም አትሄዱም፣ አይደለም እንዴ?» ሲል ሙራድ ጉላ ባለ ድምፅ ጠየቀ።

«እውነቱን ለመናገር፣ ይህ የዘመቻ ጉዞ እኛ ልናገኝ ከምንፈልገው ነገር በላይ ወጭ ይጠይቀናል። ክቡር ሆይ። ስለዚህ ወርቅ አንፈልግም። ወርቅማ የራሣችን አለን»

ይህ የአነጋገር ቅላፄ ደስ የሚል ነው! ሲል ሙራድ አሰበ።

«ጌቶቼ፣ ወደ ንጉሡ መምጣታችሁን ብቻ ሣይሆን፣ ከዚያም በላይ ቢሆን አስታውቃለሁ።» አላቸው

«ድንቅ ነው፣ ክቡር ሆይ?»

«እንዲያውም አጅቤአችሁ አደርሣችኋለሁ»

«ይቻላል እንዴ?» ሲል ሞኒሀውት ጠየቀ

«በአጋጣሚ እኔ ልመለስ በተዘጋጀሁበት ዋዜማ ላይ ነው የመጣችሁት። አምን ነገ ወደ ጌታዬ የሚያደርሰኝን መንገድ እጀምራለሁ።»

«ነገ! ታዲያ እኛ በቀረን ጊዜ ውስጥ መዘጋጀት ፈፅሞ አንችልም። »

«ጉድ ነው! እኔ ደግሞ ልጠብቃችሁ አልችልም» አለ ሙራድ በግርማ ሞገስ አነጋገር::

«የሥራ ባልደረባዎቻችን ሁሉ እስኪሰበሰቡና ለዘመቻው የሚያስፈልጉንን ቁሣቁሶች በሙሉ እስክናዘጋጅ አንድ ሣምንት ያህል ጊዜ ይወስድብናል»

«ጌቶቼ ፣ ጉዞዬን ለማቆየት ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ልሆን ብችል እንኳ፣ እመኑኝ የሚሆን ነገር አይደለም»

«ምናልባት ምክንያቱን ብጠይቅዎትና እኛ ልንረዳ . . . »

«አ ጌቶቼ፣ ምክንያቱ ቀላል ነው:: ተልዕኮዬን እንድፈጽም ንጉሡ ነገስቱ የተወሰነ መጠን ገንዘብ ሰጥተውኝ ነበር:: ያ ገንዘብ አሁን ተሟጥጧል:: ከውጭ አገር ሃይል ደግሞ የመጨረሻዋን ትንሽ የገንዘብ መጠን የመቀበል ጥያቄ ላነሣ አልችልም:: የፈረንሣይ ቆንሲል ሊረዳኝ ፈቃደኛ ሆኖ ቀረበ ነበር:: ነገር ግን እንደ ዲፕሎማት ለክብሬ ስል እምቢ አልኳቸው:: ስለዚህም መሄድ ይኖብርኛል»

«ይገባናል» አለ ረጋ ያለው ጉብኚ:: «ነገር ግን ክቡርነትዎ ለኛ አገልግሎት ሲሉ ጥቂት ቢቆዩልን፣ ይህ እንዲሆን ያደረገው ቡድን ደግሞ የመስንበቻዎን ወጭዎች ለመደጐም ግዴታ ይኖርበታል:: እርስዎም ቢሆኑ በርስዎ ላይ የጣልንብዎትን ዕዳ እንደተካንልዎ አድርገው ሊወስዱት ይችላሉ::»

«እንዲህ ከሆነ ምንም ችግር የለም» አለ ሙራድ::

ቀለል የሚለው ስውዬ በጣም በሚገርም ፍጥነት፣ በራስ የመወሰን ነፃነትና ብልሀት ቀልጠፍጠፍ በማለት፣ እጁን ወደ ልብሱ በመላክ አንድ የቆዳ ቦርሣ በማውጣት በአምባሣደሩ እግር ስር አስቀመጠ::

ከዚህ በኋላ ተጨማሪ ቆይታ የሚደረግ ከሆነ ተጨማሪና እንደቆይታው መጠን ለረዥም ጊዜ የሚከፈል ክፍያ እንደሚኖር ስምምነት ተደረገ:: ይሁን እንጂ ማይንቲስቱ፣ዝግጅታቸውን ከአንድ ሣምንት በላይ ላለማቆየት ቃል ገባ::

«ክቡር ሆይ፣አንደ የመጨረሻ ጉዳይ ግን አለ:: ስለዝግጅታችንና ስለዕቅዳችን ቆንሲሉ በጭራሽ እንዲያውቅ ባይደረግ እንወዳለን:: ምንም እንኳ እስፖኝና ፈረንሣይ በአሁኑ ጊዜ ወዳጆች ቢሆኑም፣ ነገ ግን . . . »

«ስጋት አይግባችሁ» አለ ሙራድ

ሁለቱ ሰዎች በድጋሜ ጉንበስ በማለት፣ አንድ ሺህ አንድ ጊዜ አመሰገኑት:: ሰዎቹ ወዲያውኑ እንደሄዱ ሙራድ ቦርሣውን ለቀም አደረገው:: ሲቆጥረውም አሥራ ሁለት አቡኬል ኢኩስ ሆነለት:: በዚህም በደስታ ጮቤ ረገጠ::

የዚያን እለት ምሽት ራሱንም በአመፀኛነት እያዘናና በካራቫን ሴራይ ውስጥ ስድስቱን ጨረሰ::



# 4

ፈረሰኛው ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ በቆንስላው ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ ክፉኛ ተጨንቋል:: በመጀመሪያ ላይ በአንድ አሣፋሪ ነገር ውስጥ የገባ መስሎት ሰውነቱ ሁሉ ሽባ ሆኖበት ነበር:: በኋላ ምንም ነገር ሳይነገርበት መቅረቱን ሲያውቅ ጭንቀቱ ሁሉ እንደ ማዕበል ከላዩ ላይ ተጠርጐ ጠፋለት:: ነገር ግን፣ ለአሲስ ያለው ፍላጐት ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አሁንም ጠንካራ እንደሆነ መሆኑን አወቀ:: አሁንም እንኳ የወደፊቷ እመምኔት ፍቅሯን እንድትሰጠው ለመለመን፣እንዳለፈው ጊዜ የበሯን መዝጊያ ለመቧጠጥ አጉል የብልግና ድፍረት ይሰማዋል:: አዕምሮው ሙሉ በሙሉ በቆንሲሉ ሴት ልጅ ስለተያዘበት ወደ ውጭ መውጣት ተወ:: ራሱን ፣በርሷ ቦታ አድርጐ ለማሰብ ቢሞክርም ከንቱ ሆነበት:: ምክንያቱም እርሷ ክፍሏንም ገዳም አድርጋው ዘግታ ቀርታለች:: በአጭሩ፣ ምልክቶቹ የተለመዱ ዓይነቶች ነበሩ:: በፍቅር መያዙን ለጓደኞቹ በፈገግ መልክ እየሣቀ ነግሯቸዋል:: ሆኖም ግን የራሱ ድክመት አስጠላው:: ማንኛውም አይነት ድክመት ይቅር ሲባል እንደሚችል ቢያምንም፣ ይህኛው ግን እኩያህ ባልሆነ ሰው ላይ ጥገኛ የመሆን የደደብነት አባዜና፣ሌላው ቀርቶ የዚሁ ሰው ትግል ያንተን ፍላጐት ጨርሶ የማያግዝ ሲሆን ፣ይቅር የማይባል ነው::

ቆንሲሉ፣ ሴት ልጁን እንዲሰጠው የጠየቀውን ሰው ልመና ባለመቀበሉ፣ ለዱ ሮውሌ ቅሬታ በከፍተኛ ደረጃ ተጠያቂው ራሱ እንደሆነ ስለተሰማው፣ ለይስሙላ ያህል ለፈረሰኛው ወሰን የለሽ ወዳጅነትን ማሣየት ጀመረ:: ምስኪኑ ወጣት ግን ስለኤምባሲው ያለው ጉጉት እንኳ የጠፋበት መሰለ:: ቆንሲሉም፣ ስለቀባይ ዕቅዱ ከመግለፅ ራሱን ቆጠብ በማድረግ፣ ውስጥ ውስጡን ግን ለቅፍለቱ የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶችን ማሰናዳትና፣ በሚያቋርጧቸው መስመሮች ላይ ለሚገኙ ገዥዎች የሚሰጡ ገፀ በረከቶችን በመግዛት ማዘጋጀቱን ቀጠለ:: በአጭሩ፣ ዱ ሮውሌ ከትካዜው ሲመለስ ሁሉንም ነገር ተዘጋጅቶ እንዲጠብቀው በማድረግ እየሠራ ነው:: ይህ ሁሉ እየተከናወነ ወጣቱን ሰው ጠዋትና ማታ በቢሮው ውስጥ እየተቀበለ በማፅናናት ሁኔታ ያነጋግረዋል::

ማንኛውንም ሰው፣ ሃዘኑን ለሌሎች ሰዎች የማካፈልን ያህል የሚያፅናናው ነገር የለም:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ለልበ ስሱዎች የሚሳከውን ታላቁን የፍርድ ጉዳይ፣ ቆንሲሉ በየዕለቱ ባለማቋረጥ ሲናገር በመስማቱ፣ ዱ ሮውሌ ለራሱ ይበልጥ ማዘን ጀመረ:: የሙሴ

ዴ ማይሌ የተዋበ ንግግር የጥንቱን ጊዜ የሚመስል ነው:: በመጨረሻ ላይ ግን ይህ አማን ሊሆን ትንሽ ቀርቶት የነበረው ወጣት፣ ቆንሲሉ፣ አንድ ጨዋ ሰው ድክመት ይኖርበታል በሚል ስለሚያምን ብቻ፣ ስለተከበረው ፍቅር የሚናገራቸውን የክብሩና የጸድቅ ሰው ንግግሮች ለመስማት ትዕግስት እያጣ መጣ:: ዱ ሮውሌ በበኩሉ፣ የሰውዬውን ወጥመድ ለማክሸፍ ልጅህን በሚመለከት የምመኘው ሁለት ነገሮችን ብቻ ነው፤ አንድም ለአንድ ለሊት እንደገና አብራኝ እንድታድር፣ ሁለተኛም ከዚህ ለቅቆ የመሄዱ የኔ ቢሆን ብሎ ለመናገር እጅግ በጣም ተገፋፍቶ ነበር::

ይህን ሃሣቡን ግን የበላዩ ለሆነው ሰው አውጥቶ ከመግለፅ ተቆጠበ:: ይሁን እንጂ ለራስ ሲናገራቸው በመጀመሪያ ላይ እንዳሰበው የፍቅሩ ጉዳይ ይህን ያህል ተስፋ የሚያስቆርጥ ላይሆን ይችላል ሲል አሰበ:: ይልቁንም ቀደም ሲል የተጎዳው የርሱ ፍላጎትና የርሱ የራስ ማክበር ስሜቶች ናቸው:: የቆሰለ ሰው በመጀመሪያ የሚሰማው ስቃይ ያሰደነግጠዋል:: በኋላ ግን ስለደረሰበት ቁስል ቀላልነት ግልፅ የሆነ ግምት ለራሱ ሲሰጥ፣ በመበረታታት እኖራለሁ ብሎ ያምናል:: እንደዚሁም ሁሉ ዱ ሮውሌ ሙሉ በሙሉ በፍቅር እንዳልተሸነፈ ሲገነዘብ፣ ራሱን በማድነቅ ተፅናና:: በመቀጠልም ወደ ቀድሞው እርሱነቱ ለመመለስ ደፈረ:: በሚቀጥለው ዕለት በአንድ ነጋዴ ቤት የካርታ ቁማር ጨዋታውን ቀጥሎ ብዙ ተበላ:: በመበላት፣ ብዙ በመጠጣትና ሌሊቱን በቱርካውያን አገናኞቹ ሳቢያ ቤቱን ከሞሉ ወጣት ቆንጃጅት መካከል ከሁለቱ ዳንሰኞች ጋር አሣለፈ:: በአጭሩ ራሱን ወደ አልሆነ አቅጣጫ ከመውሰድ ገታው::

የግል አስተያየቱ ብዥ ባይልበት ኖሮ፣ ለአፍታ ያህል እንኳ ሣያያት ሊቆይ እንደማይሆንለት ሁሉ፣ አሊስን በሚገባ ሊያያት ይችል ነበር:: የግል አስተያየቱ ብዥ ስላለበት፣ ሲያያት በክፊል ያበደች፣ በሴቶች ገዳም ውስጥ ጥሩ ሆና መገኘት የምትችልና ዕድሜዋን በሙሉ ከርሱ ጋር በርህራሄ የተጋራችውን አጭር የደስታ ጊዜ በትዝታ እያስታወሰች የምትኖር ሴት አድርጐ አሰባት::

ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ የሚታይበትን የባህርይ ለውጥ፣ ሙሴ ማይሌ ወዲያውኑ እንዳያውቅ ዱ ሮውሌ ተጨነቀ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ጤንነቱ እንደሚመለስ ለማስመሰል ቢሞክርም፣ ቆንሲሉ ግን ከምን ጊዜውም በበለጠ መሻሻሉን ለማጠናከር ተጨነቀ:: የዱ ሮውሌን አምባሲ ወደ አቢሲኒያ መንዝ ያፀደቀው መሆኑን የሚያረጋግጥ የሚኒስትሩ ደብዳቤ ከፈረንሣይ ደረሰ:: ሙሴ ዴ ማይሌም፣ ከቆንስላው ሣጥን ውስጥ አስቀድሞ በገፍ ዝቆ



ለመውሰድና ተንገፍቹም ምንም ነገር እንዳማይቸግራቸው ለማድረግ ሥልጣን እንዳለው አመነ:: ይህ ተልዕኮ ደግሞ ይፋዊ ማንነቱን በማያወላውል መልክ ለሁሉም፣ በተለይም ለኢትዮጵያውያን ግልፅ ሊያደርገው ነው:: ይህ ተልዕኮ ቀደም ሲል በፖንሴ መሪነትና አገልጋዩ ናቸው ተብለው አብረውት ከተጓዙት ከዮሴፍ ከርፋፋ ዝግጅት ፍፁም የተለየ ይሆናል::

የዱ ሮውሌ ኤምባሲ ቅፍለት፣ የተንቆጠቆጠ ከርቻ የተጫኑ ሃያ ሰስት ምርጥ የግመል ዝርያዎች ያሉበት ይሆናል:: የቅፍለቱ መሪ በላክ ተብሎ የሚጠራና የሲናር ንጉስ ወኪል የሆነ ቱርካዊ ነው:: ቆንሲሉ ቅር ቢለውም፣ ዋናው አስተርጓሚም ይህን ዘመቻ በአስተርጓሚነት ለማገልገል እንዲችል እንዲቀላቀል ስለተደረገ ይለያያሉ:: ዱ ሮውሌ፣ ሙሉ በሙሉ ራሱን ከገዛ በኋላ፣ ቀሪዎቹን ተጓዦች የመምረጡ ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ ለርሱ እንዲተውለት ጠየቀ:: ለቆንሲሉ ሣይነግረው፣ ባለፈው ዓመት ካይሮ የገባና ራሱን በመጥፎ ምግባሮች ለይቶ ያሣወቀ አንድ ወጣት ፈረንሣዊን እንደ ዋና ረዳቱ አድርጐ መረጠ:: ዱ ሮውሌ፣ በካርታው መጫወቻ ቤት፣ ሩሚላክ ተብሎ የሚጠራ ሰውም ተዋውቋል:: ወጣቱ ሩሚላክ ተለማማጅ የሆኑትን የኬይሬኔ ሃብታሞችን በጫወታው ላይ በማታለል የሚበልጣቸው ነበር:: ማንም ሰው፣ ዱ ሮውሌ በቁማር ጨዋታው ላይ ማጭበርበር እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ብሎ የሚጠረጥረው ስለሌለ፣ ሩሚላክን ለይቶ አወቀው:: ከዚህ በኋላ የሩሚላክን ስም ከማጉደፍ ይልቅ በሽርክና ተወዳጀው:: እነዚህ በቅርብ የተሣሰሩ ሰዎች ስማቸውና ዝናቸው ተሰራጨ:: እንዲያውም በከንቱ ውዳሴ ይኩራሩ የነበሩት አንዷቸው፣ ጥንዶቹ ሊሸነፉ የማይችሉ ጠንካሮች ናቸው ተብሎ ተፈሩ:: ሩሚላክ ለመጠጥ ጠንከር ያለ ፍላጐት ያለው ከመሆኑ በስተቀር ገና ልጅነትም ያለው ስለሆነ ሸንቃጣና ደስ የሚያሰኝ ቁመና አለው:: በጉንጮቹ ላይ ግን ወደፊት ፊቱን የሚሸፍኑት ነገሮች እጅግ ጥቃቅን ቀያይ መስመሮች ብቅ ብቅ እያሉ ነው::

ዱ ሮውሌ፣ ከነዚህ በተጨማሪ ተመሣሣይ ዓይነት የሆኑ ሁለት ሌሎች ሰዎችንም መረጠ:: እነዚህኞቹ ያለባቸው ችግር ከበፊተኞቹ ይልቅ አነስ ያለ ነው:: አንደኛው፣ ቀደም ሲል ፖሪስ የነበረ ሲሆን፣ ሥራውን ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ለቅቆ በአሁኑ ግዜ ካይሮ ውስጥ ያለሥራ የተቀመጠ ሰው ነው:: ከአርሌስ የሆነው ወርቅና ብር አንጥረኛው፣ ምናልባትም የሻምላ ተዋጊና የሃሰት ሰነድ የሚያዘጋጅ ሆኖ በውጭ አገር መኖርን የመረጠ ነው:: እነዚህ ሰዎች በብላሽ ጠባያቸው ስማቸው የሚጠቀስ ናቸው:: ሁለቱም ሰዎች የሚጋሩት ጠባያቸው

ስድነትና እጅግ ሲበዛ ራሣቸውን ያለመቆጣጠር ባህርያቸው ነው። ከዚህ ቀደም ሁለቱን ሰዎች ፈፅሞ አግኝቷቸው የማያውቀው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በምርጫው ደስተኛ አልነበረም። ይሁን እንጂ ቁመናቸው የሚያምርና የሚያስደስት ስለሆነ አምኖ መቀበል ነበረበት። ዱ ሮውሴ፣ ለማሣመንና ራሱንም የበለጠ ነፃ ለማድረግ በማሰብ «እንዲህ ያለ ብዙ አደጋና ፈተና ባለበት ተግባር ውስጥ ፈቃደኛ ሆኖ የሚሣተፍ ንፁህ ሰው ማግኘት ፈፅሞ አስቸጋሪ ነው» ሲል ነገረው።

በዚህ ቡድን ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው ሹመት ባይኖረውም፣ ስም አለውና አሥር ወይም አስራ ሁለት የሚሆኑ ከማህበረሰቡ ውስጥ ዝቃጭ የሆኑት ምስኪኖች ተመረጡ። እነዚህ ከወታደራዊ ሙያ የከዱ፣ ከሕግ በመደበቅ የሚሸሹ፣ የሁሉም አይነት ቅጥረኞች የሆኑትን ሰዎች ዱ ሮውሴ ሲመርጣቸው እንደተዋጊ ጓድም አስቧቸው ነው።

የተንገፉ ሠራዊት ሁለት መሪዎች በመጀመሪያ ያጋጠማቸው ሥራ፣ ከቀንስላው የተሰጣቸውን ድጐማ ቅፍለቱ ተሸክም ሊያንገዛቸው በሚችላቸው ዕቃዎች ላይ ወጭ ማድረግ ነበር።

የዱ ሮውሴ ሃላፊነት በጣም ቀላል ነበር። ሽሪከቹም ይህንኑ ወዲያውኑ ተገነዘቡ። አምባሲው የማስመሰያ ሰበባቸው እንጅ እውነተኛ ተግባራቸው ንግድ ነበር። በተቻለ መጠን ገፀ በረከቶቹ በአነስተኛ መጠን ይሆኑና ጭነቱ ሊሸጡም ወይም ሊለወጡ በሚችሉ ሸቀጦች ይተካል። እግረ መንገዳቸውን ለመጠቀምና አቢሲኒያ ውስጥ እጅግ ከፍ ባለ ልዋጭ ሃብት ለማከማቸት የራሣቸውን ሸቀጦች በአንድ ላይ አደረጉ። በርግጥ እዚያ በሚሄዱበት ቦታ ሁኔታዎች አሳሰበዋቸው ሃብታቸው ሌላ ከፍ ያለ ምኞት ውስጥ በከትታቸውስ? የጦር ሠራዊት ቢገዙና፣ ከሌላ ሃይል ጋር የተሣካ ግንኙነት ፈጥረው ምናልባትም ሥልጣን መንጠቅ ቢችሉ? ለምን አይሆንም? በተንኸ ሠራዊቱ መሃል ጤናማ ወዳጅነት ዳበረ። ዱ ሮውሴም የአድናቆታቸው ማዕከል ሆነ። የመሪያቸው ከመጠን በላይ አስተዋይ የመሆን፣ የድፍረቱ፣ የተጠራጣሪነት ባህርይው ታክሎበት፣ እርሱን የምድር ገዥ፣ ራቸውን ደግሞ እስከ ግዛቱ ድረስ አጅበውት የሚጓዙ ሠራዊቱ መሆናቸውን አንድም የሚጠራጠር አልነበረም።

ዘመቻው የሚገጥመውን አደጋ በተመለከተ ሰዎቹ በመጠኑ ለየት ያለ አስተያየት ፈጥረዋል። እያንዳንዱ ባለፈው በጀብድ የተሞላ ሕይወቱ፣ የተለያየና ያልተመጣጠነ አደጋን አምልጧል። ረሃብንና ጥምን ለመከላከል፣ ማንም ሰው የሚያስፈልገው በበቂ መጠን ሥንቅ ሊሰጠው ይገባል። የአገሬውን ተወላጆች በሚመለከት፣ እነዚህ በምሥራቅ ሜዲተራኒያን



የሚገኙ ልምድ ያላቸው ሰዎች ከብዙዎቹ ነቢያውያን፣ ሱዳናውያንና፣ ሌሎች ከመካከለኛው አፍሪካ የመጡ አገልጋይ የአገሬውን ተወላጆች በተመለከተ የሚደራደሩባቸው ቀላል ፖሊሲዎች አሏቸው። ከነዚህ ሰዎች ጋር በጥሩ ብልጠት ሊፈታ የማይችል ምንም ዓይነት ችግር የለም። ሰዎቹ ብዙ ጕራዴዎች፣ ሽጉጦችና ቀስቶች ታድሏቸዋል። ይህ ሁሉ ላልሰለጠኑት ሕዝቦች ለመሸጥ ወይም ራሣቸውን እንዲከላከሉበት ተብሎ ሣይሆን፣ በየዋህ ስሜት አንድ ያልተለመደ ነገር በመውደድ፣ እርስ በርሣቸው እንዲጨራረሱ ሲባል መሆኑን በሚገባ ያውቃሉ።

ከዚህም ባሻገር ከአገሬው ተወላጆች ጋር በሚኖር ግንኙነት፣ ማንም ቢሆን አስቀድሞ መሥራት ያለበት ከሴቶች ጋር ነው። ምክንያቱም ሴቶቹ ከወንዶቹ ይልቅ ደፋሮችና በማይለዋወጥ ፅኑ አቋም ወሣኝ ሆነው የሚኖሩ ስለሆነ ነው። ስለዚህም ዘማቹ፣ ርካሽ የሆኑ ቀለማት የበዙባቸው ጨርቆችን፣ የሚንሿሹ ጌጣጌጦችና ሌላው ቀርቶ በአንድ ቬኔሲያዊ ነጋዴ በቅርቡ ወደ ካይሮ የገቡትና በአውሮፖ ትያትሮች የሚገኙት መልክን አጣምመው የሚያሣዩ መስተዋቶች ሳይቀሩ ተገዝተዋል።

እነዚህ ዝግጅቶች እየተከናወኑ ባሉበት ጊዜ ውስጥ፣ አሊስም የራስዋን መጠነኛና በጣም ጥንቃቄ የሌለባቸውን ዝግጅቶች ታደርግ ነበር። ከአባቷ ፊት ርቃ በክፍሏ ለመቆየት ስለለመነችው፣ እርሱም በአፎይታ ስሜት ፈቅዶላታል። በሌላ በኩል ባለፉት ቀናት ሥራዎቹን ሲያከብቡቸው የከረማቸውን የአርኪኦተስ ሣጥኖችን በማውጣጣት አፅምሮው ተይዟል። ይሁን እንጂ ምንም ማይጨነቅ ሁሉንም ለመቀበል በመቻሉ፣ ከሀመምናና ከሃፍረት እንደተገላገለ አመነ። በሌላ በኩል ይህ አስተያየቱ ጠንካራ አልነበረም። ስለዚህም ወደ በሩ በመሄድ በከዘራው መሬቱን እየደቀደቀ ሣጥኑን ያመነኝከዋል። ይህ ታዲያ ከመጥፎው ሁኔታ በኋላ በቶሎ ሊለቀቀው ያልቻለው ስሜት ጣጣ ነው። ሆኖም እርሱን በተመለከተ ከዚህ በኋላ ሴት ልጅ የምትባል የለችውም። ማዳም ዴ ማይሌም፣ የባሏን የወኔ ቁራጥነት አጥታብታለች ይሁን እንጂ በርሱ ብሶ ይወቀሳታል። እስከዚህ ሰዓት ግን ሙሴ ዴ ማይሌ፣ አሊስ የተናዘዘችውን አስቃቂ ወንጀል አልነገራትም። እናትየውም ልጇ ወደ መንፈሣዊው ሕይወት በመጠራቷ ብቻ እርር ኩምትር በማለት ላይ ነች። የልጇን ክብር ማጣት በማወቅ ብታለቅስስ ምን ሊመስል ይችል ይሆን? አሊስ፣ ምስኪኗን ሴትዮ፣ በየዕለቱ ቀትር ካለፈ በኋላ ትቀበላትና አንድ ጊዜ አሊስ ተቀምጣ ታነብበበት የነበረውንና በሀምራዊ ሃር የተሸፈነውን ባለመደገፊያ ወንበር እስኪርስ ድረስ አልቅሣ፣ በልቧ ያለውን ሁሉ እንድትተነፍሰው ታደርጋት ነበር። በተረፈ በቀሪው ጊዜዋ በሯን የምትከፍተው ለፍራንቾይዝ ብቻ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ምስጢረኛ

ዋና የልብስ አጣቢዋ በሆነችው ሴት ንፅህና ፈፅሞ እምነት ስለሌለው፣ እስከፈረንሣይ ድረስ ሴት ልጁን ተከትላ አጅባ እንዳትሄድ ከለከለ። ሆኖም ግን ልጁ እስከምትሄድበት ጊዜ ድረስ እንድታገለግላት ፈቀደ።

ሁለቱ ሴቶች ለአሊስ የገዳም ሕይወት የሚሆናትን ያልተለመደ ዕቃ አዘገጃጁ። አሊስ አገር ለቅቃ፣ ስትሄድ፣ረኝርም የጥቁር ቤዥ ቀለም ያለው፣ምቾት የማይሰጥና ለሴቶች ገዳም ተስማሚ ሆኖ ምንም ዓይነት ጥርጣሬን የማያጭር ቀሚስ እንደምትለብስ ተስማሙ። ከዚህ ከላይ ከሚታየው ልብሷ ሥር ግን ወፍራም የጥጥ ሱሪ፣ ሰፋ ያለ ሸሚዝ ትለብስና ለሸንጦችዋ መያዣ የሚሆን የቆዳ ቀበቶ ትታጠቃለች። በወገቧ ላይ ደብዘዝ ባለውና ለዕድሜ ሙሉ ፀሎት ተስማሚ በሆነው ልብሷ ስር፣በአረቦች ሰፈር ውስጥ ፍራንቾይዝ የሠራችላትን ጥንድና በቀላሉ እጥፍጥፍ የሚል የቆዳ ቦት ጫማ ሸሺጋ ትይዛለች። የልብስ አጣቢዋ እግር፣ በትክክል ከወጣቷ ሴት እግር ጋር እኩል ስለሆነ ጫማውን የሠራችው በራሷ እግር መጠን ነበር። ከነዚህ ቀጥሎ ጥንድ መኮርኮሪያዎችና የዝሆን ጥርስ እጀታ ያለው ጎቤ አለ። በመጨረሻም፣ዠረሚ ለዚሁ ሲል አሹሎና ስል አድርጐ ያዘጋጀውን ቀላል ሻምላ፣ ፍራንቾይዝ በቀሚሷ ስር ደብቃ አመጣች። ከዚህ በማስከተል መያዝ የነበረባቸው ሸንጦች፣ ባሩድና የጥይት እርሣሶች ሲሆኑ እነዚህም በነጭ የናይሰን ቅርጫት ውስጥ ተደርገው ደረሱ።

ሁለቱ ሴቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ ባለው ሁኔታ መስራት ስለነበረባቸው ዝግጅቱ አስር ቀን ያህል ጊዜ ወሰደ። በመጨረሻ ግን አሊስ ዝግጁ ሆነች። የወጥ ቤቱ ሠራተኛ፣ በትሬይ ላይ አድርጐ ያመጣላትን ምግብ እየተመገበች በመስኮቱ ወደ ውጭ በትካዜ ተመለከተች። ጉዞ የምትጀምረው መቼ ይሆን? ጀልባዋስ ምን እየሠራች ነው? ዓመቱ ቀስ እያለ መንጐድ ጀምሯል። የካቲት እየተገባደደና በግብፅ ውስጥ ሙቀት ቀስ በቀስ እየተመለሰ ነው። አፅዋት እየፋፉ ነው። ከዕለታት አንድ ቀን በአትክልቱ ሥፍራ ውስጥ በመድረቅ ላይ የነበረ ቁጥቋጦ፣እንደገና ትናንሽ ቀያይ ቅጠሎች አቆጥቁጦ ተመልክተዋል። ከዚያም ብዙ ሣይቆይ፣ ሙሉ በሙሉ አብቦና አበባዎቹም ተንዥርግገው፣ ሳር ቅጠሉን በተለያዩ ቀለማት አሸብርቋቸዋል። ይህን ትዕይንት፣ አሊስ፣ በቅርቡ ከጆን ባፕቲስት ጋር እንደምትሆን ምልክት እንደሆናት አድርጋ አነበበችው። የፈለጋትን ያህል ራሷን በጥልቀት ብትመለከተውም፣ከዚህ በበለጠ በቅሬታዋና በመከራዋ የተነሣ የምታፈስሰው እምባ ስለሌላት የሚታያት ሁሉ ትዕግስት ማጣት ነው።



በዚህን ጊዜ ካይሮ ውስጥ ራሣቸውን በሥራ የጠመዱ ብዙ መንገደኞች ቢኖሩም፣ ከከተማዋ ለመልቀቅ የመጀመሪያው ግን ሙራድ ነበር። አስቀድሞ ግን አክብሮቱን ለመግለፅ ወደ ሙሴ ዴ ማይሌ ሄደ። ሙሴ ዴ ማይሌም በደስታ ተቀበለው። የቆንሲሉ ሰላዮች በከተማው ውስጥ ስድስት እንግዳ መንገደኞች መግባታቸውን ሪፖርት አድርገውለት ስለነበረ፣ እነዚህ ፍሊሃውት የነገሩት ጀስዊቶች ናቸው፣ ሲል መርምሮ ውሣኔ ላይ ደረሰ። እነዚህን ሰዎች በተመለከተ ሚኒስትሩ የሰጠው መመሪያ፣ በጉዳዩ ላይ ዝምታ እንዲጠበቅ ስለነበረ፣ ሙሴ ዴ ማይሌም በጣም በጥንቃቄ ይከታተላቸዋል። በማንኛውም መልኩ የርሱ ኤምባሲ ከሃይማኖታዊው ዘመቻ ተለይቶ እንዲቆይ ይፈልጋል። ሙራድ፣ ጉዞው በድል ተሣክቶለት በጥሳቻ ሰላየው ከሆነ፣ የፈረንሣይን ንጉሥ ሰላምታ ለአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት በቃል እንዲያስተላልፍለት ተመኘ።

«ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ በየትኛው መንገድ ትሄዳለህ?» ሲል ቆንሲሉ ሙራድን ጠየቀው

«ከቡር ሆይ አስቀድመን ወደ ጂዳ እንሄዳለን። ከዚያም ወደ ምፅዋ እናመራለን። ከዚያ ተነስተን የጐንደርን መንገድ እንይዛለን»

«ይህ ማለት በባህር ላይ ለመጓዝ ወስነሃል ማለት ነው»

ይህ ጥሩ ዜና ነው። ምክንያቱም ቢያንስ በዱ ሮውሌ መንገድ ላይ አይሆኑም። ከዚህም በላይ ትንሽ ዕድል ኖሯቸው ከተሳካላቸው ከርሱ በኋላ ይደርሣሉ።

ሜትር ዠረሚ ሙራድን ከልብ በመነጨ ሰላምታ ተሰናበተው። ይህ ማለት ቢያንስ በአስቸጋሪና በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ ጥሎት ስላልሄደ የሚሰጋው ነገር የለውም። በመጨረሻ ላይ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እየደረሰ ነው። ለአፍታ ያህል የጥርጣሬ ስሜት በአዕምሮው ብልጭ ቢልበትም፣ ፕሮቴስታንቱ፣ ሙራድን የሚያጅቡትን የካፑቺን ሰዎች እያውቃቸውም። የዚህን ምስጢር በግልፅ እንዲነገረው ሜትር ዠረሚ ምንም ጥረት አላደረገም። በአርመናዊው ሁኔታ እፎይታን ከማግኘቱም በላይ፣ አሊስ በሰጠችውና የባሰ ውስብስብነት የሌለውን ተልዕኮ ለማሣካት በሥራ በጣም ተይዟል። ሙራድ፣ በገንዘብና በሌላም ነገር ድጋፍ ከሚያደርጉለት ሰዎች ጋር በፈረስ ላይ ሆነው በአንድ ውብ ፀሐያማ ማለዳ ወደ ስዊዝ ተነሱ። ሦስቱ አቢሲኒያውያን አሁንም እንደና በሰረገላ ውስጥ ሆነው ተከተሉት።

ከሁለት ቀናት በኋላ የአሊስን ዕቅድ የሚያበላሽ ድንገተኛ ነገር አጋጠመ። ከቬርሣይለስ የመጣ መልዕክተኛ ቆንስላው ግቢ ደርሶ፣ አንዲት መርከብ ጥቂት ቀደም ብላ አሌክሣንደሪያ ላይ ማረፍዋን በመግለፁ የአሊስ መንዝ የማይቀር ሆነ። በመጨረሻው ሰዓት ላይ ጥርጣሬ ያደረባት አሊስ፣ ይህ በቅርቡ የመጣው ፖስታ የጆን ባፕቲስትን ጉዳይ የሚናገር ነገር እንዳለበት ለማወቅ ፈለገች። እንዲህ ተለያይተው ሣሉ ለተመሣሣይ ግብ እየሠሩ፣ ነገር ግን እንዳቸው የሌላውን ዕቅድ ባለመገንዘብ ለነገሮች መፍትሔ በማግኘት ፈንታ ውስብስብ እንዳያደርጋቸው ሰጋች።

እንደተለመደው ሙሴ ማቼ ደብዳቤውን ለቆንሲሉ አመጣለት። እርሱም ደብዳቤውን ለማንበብ ቢሮውን በላዩ ላይ ዘጋ። ለምሣ በመጣበት ጊዜ ፀሐፊው በገበታ ላይ አብሮት እንዲሆን ጠየቀው። አሊስና ፍራንቾይዝም ቀልጠፍ ብለው ቆንሲሉ ከምሣ በኋላ ወደ ፎቅ በመውጣት አጭር ሽለብታ በሚያደርግበት ጊዜ፣ ዕድሉን በመጠቀም ታላቂቱ ሴት ወደ ቢሮው በፍጥነት ገብታ ደብዳቤዎችን ታያቸዋለች። ይህን ዕቅድ በድፍረት በመከወን የመጀመያውን ደብዳቤ ማንበብ ጀመረች። ምስኪኗ ሴት የሚንስትሩን የእጅ ፅሁፍ ለማንበብ ይቸግራታል። አልፎ አልፎም እየቸገራት ማንበቡዋን ቀም ታደርገዋለች። የእያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር መልዕክት በመጀመሪያው ንባቧ ላይ አትረዳውም። በዚህ የተነሣ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፣ ስለጆን ባፕቲስት ግን አንዳችም ነገር አላገኘችም።

በአዳራሹ መተላለፊያ በኩል እንግዳ መምጣቱን የሚያስታውቅ የሚመስል ድምፅ በድንገት ሰማች። በፊት ለፊቱ የመግቢያ በር በኩል ምንም ዓይነት የሠረገላ ድምፅ ስላልተሰማ እንግዳው በእግሩ ተጉዞ የመጣ ሣይሆን አይቀርም። ፍራንቾይዝ ስታነብበው የነበረውን ወረቀት ጥላ ወደ ትንሿ የሙዚቃ ክፍል ሮጠች። በሩን ከፍታ ስትገባም፣ ማዳም ዱ ማይሉ ጀርባዋን ለርስዋ ሰጥታት ብቻዋን ተቀምጣ ስታለቅስ አየቻት። ፍራንቾይዝ በሩን ስትዘጋውና የሙሴ ማቼን ድምፅ ስትሰማ አንድ ሆነ። ከመደንገጥዋ የተነሣ ከአንድ መጋረጃ ጀርባ ውሽቅ ብላ ተደበቀች። ፀሐፊው፣ ቋንቋውን በባዕድ አገር ሰው ቅላፄ የሚናገር አንድ ሰው አስከትሎ ገባ።

«አባቴ፣ ቅር ባይልዎ እዚሁ ይጠብቁ። ሙሴ ዱ ማይሌ በአጭር ጊዜ ውስጥ አብሮዎት ይሆናሉ» አለ ማቼ



ሙሴ ማቼ፣ እንግዳውን በክፍሉ ውስጥ እንዲጎራደዱ በመተው ወደ ፎቁ ሲወጣ ፍራንቾይዝ ሰማች። ወዲያውኑም ቆንሲሉ መጣ። በሐሩር ምድር አረፍት በመነሣቱ በመበሣጨት እየተናገረ ደረሰ።

«እሺ ወንድም ፖስኳል፣ ምን አይነት አስቸኳይ ጉዳይ ነው ባጣዳፊ እንዲመጡ ያደረገዎ?»

«እ፣ ይቅርታ ክቡር ቆንሲሉ። በእንቅልፍ ላይ መሆንዎን አላወቅሁም። የመጣሁት ዜና ልነግርዎ ነው። ዘይቱን አገኘነው»

«ዘይቱን?»

«ምነው? አዎን ዘይቱን፣ የነግስናውን ዘይት»

«አ! ዘይቱ» አለ ቆንሲሉ እንደመመራመር «እናስ?»

«መቼም ፖትርያርኩ በጣም ገቢጋባ ናቸው። እርስዎ የሰጡንን ሁሉ ልንሰጣቸው ተገደድን»

«ይህማ የራሣችሁ ጉዳይ ነው ወንድም ፖስኳል። የተስማማነው በተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው፡ ከዚህ በኋላ ምንም ነገር አልጨምርበትም»

«ግን እኮ ወንድሞቻችን ነገ ስለሚሄዱ እለምንዎታለሁ ቆንሲል ሆይ። ሌላው ቀርቶ የሚንንዙባቸው በቅሎዎች የላቸውም። በእግራቸው! ወደ አቢሲኒያ በእግራቸው ሊሄዱ ነው?»

«እባክዎን፣ ወንድም፣ ግድ አይበሉኝ። ቀደም ሲልም ተናግሬአለሁ። ይህ የናንተው ጉዳይ ነው»

ካፑቺኑ ለአፍታ ያህል ዝም አለ። ፍራንቾይዝ በተደበቀችበት ቦታ ሆና ትንፋሽ አጥታለች።

«በአምባሳደርዎ ቅፍለት ውስጥ ያሉትን ግመሎች ሁሉ ሳስባቸው ...»

«ያ ከዚህ ርዕስ ውጭ ነው»

«ወይኔ! እነርሱም ቢሆኑ በሲናር ውስጥ ነው አቋርጠው የሚያልፉት። ወንድሞቻችንንና ዘይቱን ይዘው ሊሄዱ ይችላሉ።»

«ይህ ከጥያቄ ውጪ ነው። ሁለቱ ጉዞዎች እንደተለያዩ መቆየት ይኖርባቸዋል። ይህ የንጉሡ ትዕዛዝ ነው።»

«የፈረንሣይ ንጉሥ ማለትዎ ይሆናል። መቼም የሲናር ንጉሥ አያደርጉትም»

«ምን ማለትዎ ነው?»

«ምንም! የሲናርን ንጉስ በሚገባ እናውቃቸዋለን፣ ይኸው ነው»

በነዚህ ቃላት ውስጥ ምንም የለባቸውም። ይሁን እንጂ ከቃላቱ ጥልቅ ፍቺ ውስጥ፣ አንድ ሰው ኩል በመሰለ ውሃ ሥር ሆነ ብሎ ለማስፈራራት ፈልጎ እንደሚዋኝ አባብ የመሰለ አሣ፣ በግልፅ እንደሚመለከት ሁሉ፣ አነጋገሩም በአዕምሮ ውስጥ የተጠነሰሰ ነገር እንዳለ ያሣያል። ሙሴ ዱ ማይሌም ይህን ስሜት ወዲያውኑ ተረዳው። ምንም ዓይነት አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር አይወስድም። የፈለገው እንኳ ቢሆን መነኮሣቱ ምንም ንዝ ስለሌላቸው ጉዟቸውን ይጀምራሉ። ሌባም ስለሆኑ ፈጥነው መጓዝ ይችላሉ። ስለዚህ ዱ ሮውሌ ሌላው ቀርቶ ሲናር እንኳ ሣይደርስ በፊት ማንኛውንም ዋጋ ተከፍሎ ምንም ዓይነት የፖለቲካ የበላይነትን እንዳይዘብት መታገድ ይኖርባቸዋል።

«እሺ፣ ታዲያ ምን ይፈልጋሉ?»

ወደፊትና ወደ ኋላ ሲወዛወዙ ከቆዩ በኋላ፣ ካፑቺኑ ተገቢነት በሌለው ዘዴ አንድ ግመል ሁለት በቅሎዎችና ጥቂት መጠን ወርቅ አገኙ። ለቆንሲሉ ዝቅ ብለው ሰላምታ በማቅረብ አመስግነው ሄዱ።

«መቼም በዚህ ድርጊታችን ተሸናፊ አንሆንም። ቢያንስ አሁን ባለዕዳዬ ናቸው» አለ ቆንሲሉ ለሙሴ ማቼ፣ የእጅ መስጠቱን ተገቢነት ለማሣመን እየጣረ። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ቢሮውን ለቅቀው ሄዱ። ቆንሲሉ ወደ መኝታ ክፍሉ ለመሄድ ፎቁን ሲወጣና ሙሴ ማቼም በመጥረጊያ ማስቀመጫ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ በራሱ ላይ በሩን እስኪዘጋ ድረስ ጠበቀችና ፍራንቾይዝ፣ ከተደበቀችበት ወጥታ ወደ አሊስ ክፍል ተመለሰች።



# 5

ሙራድና ሙሴ ዱ ማይሊ፣ ደማቅ በዓል አድርገው ከተለያዩ ከአንድ ሣምንት በኋላ የኤምባሲው ቅፍለት ለጉዞው ተነሣ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ የተከበሩ ሰዎች፣ የዱ ሮውሌ ሠራዊት ሲንቀሣቀስ ለማየት በዝርዝር ተጠርተዋል። ብዙዎቹ ሸኚዎች ለዚህ ጉዞ የሚሰጡት ምንም ዓይነት ስም አልነበራቸውም። ቆንሲሉ፣ ባለፈው ዘመቻ ጊዜ የባከነውን ገንዘብ በከፊል ለማካካስና ክብሩን ለመጠቀም ችሏል። ፓሻው፣ ለዚህ ተጓዥ ቡድን አስፈላጊ የሚሆኑትን መብቶች ፈቅዶ ለመስጠት ችግር የፈጠረ ቢሆንም፣ ቆንሲሉ ግን ጉዞውን በጥንቃቄና በስልት ለመያዝ ሃሣብ አላደረበትም። ይልቁንም ለዚህ እጅግ ከባድና ሊሆን ለማይችል ዕቅድ፣ ፈረንሣይ የሰጠችውን ከፍተኛ ግምት ለማሣየት ፈለገ። ምንም እንኳ፣ ቱርኮች እዚህ ጌቶች ነን በማለት ለማስመሰል ቢሞክሩም፣ መቼም ሁልጊዜም ለነርሱ ሲሰግድ የሚኖር የለም ይላል።

ፈረሰኛው ዱ ሮውሌና በኩራት የሚወጣጠሩት አጭበርባሪዎቹ የቡድን አባላቱ፣ በግመሎቻቸው ላይ ተቀምጠው ሲታዩ ድንቅ ናቸው። ቤላክ፣ ብቃት ያለው የቅፍለት መሪ ነው። ግመሎቹንም በአንድ ላይ አስደሳች እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ አሰልጥኗቸዋል። እንዲያውም በእግሮቻቸው ላይ የብር ቃጭል አንጠልጥሎላቸዋል።

ይህ አነስተኛ የቅፍለት ጓዝ ቀደም ሲል ፖንሴ፣ አስዩት ውስጥ የተቀላቀለውን ትልቅ ቅፍለት መገናኘት አልቻለም። በመጨረሻም ተጓዦቹ ቁጥራቸው ብዙ ስላልሆነና በበቂም ስለታጠቁ፣ ቤላክ ደህና አድርጎ የሚያውቀውንና በአባይ ሰሰተኛው ፏፏቴ ላይ ሲያደርሣቸው የሚችለውን መንገድ ለመከተል ወሰነ።

ይህ የተንቆጠቆጠ ሰልፍ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሲያቀና፣ ካይሮ ውስጥ የሚገኙ ፈረንሣውያን ባለሥልጣናትና ሃብታሞች ከርቀት ሲያዩት እያነሰባቸው ሲሄድ ልበ ሙሉ ሆኑ። ይህ በዚህ እንዳለ ሌላ ተጓዥ ደግሞ ከቆንስላው ለመልቀቅ ሽር ጉድ እያለ ነው።

ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ሴት ልጁ በዚህ ጊዜ ለቅቃ እንድትሄድ ይፈልጋል። ምክንያቱም የመታየቷና የመሄዷ አሰባልታ አይገልፃም። ስለዚህም፣ አንድ እርማ እንኳ በሌለበት ጥቁር ሰረገላ ውስጥ ሆና፣ ሁለት ዘበኞች በፈረስ ላይ ተቀምጠው አጅበዋት ብቻዋን ጉዞዋን ጀመረች። ማዳም ዱ ማይሌ፣ ለእግዚአብሔር አገልጋይነት የሰጠቻትን መነኩሲት በመሳም ፣ደህና ሁኚ